www.nesiha.com

ጥር 2009 JAN 2017

ተጓበሪካት

«ዕውቀትን ለመፈለግ መንገድ የጀመረ አላህ ወደ ጀነት የሚያስገባውን መንገድ ያገራለታል ! » (ሙስሊም ዘግበውታል)





ታላቅ ምክር ለልባሞች !

ቀደምቶቻችን ሶሃቦችም ሆኑ እነሱን በመልካሙ የተከተሉት ተተኪ ትውልዶች አንደበታቸውና ተግባራቸው እኩል እንዲራመድ እጅግ ይጥራሉ። እንደ ጥንቃቄያቸውና ልፋታቸውም ተሳክቶላቸዋል።

ዙበይድ አልያሚ የታላቁን ሰሃቢይ የኢብደላህ ኢብን መስዑድን የማስጠንቀቂያ ንግግር በመጥቀስና የራሰቸውን ጥንቃቄ በማውሳት ይመክሩናል። አላህ ይዘንላቸው ስራቸውንም ይውደድላቸው።

እንዲህም ይላሉ

{ የኢብኑ መስዑድ ንግግር ለሀያ አመታት ዝም አሰኝችኝ። እሷም

"ንግግሮቹ ከተግባሩ የማይስማማ ሰው ራሱን ያስጠንቅቅ!"
የምትለዋ ናት። }

【ዑዩኑል - አኽባር : 2/179】

እኛም የአንድ እለት ተግባርና ንግግራችንን እንኳ ብንመረምር ምን ያህሉ እንደሚለያይ እንረዳ ይሆናል። ከዚያም እድሜ ልካችንን በዝምታ ማሳለፍን እንመርጥ ይሆናልና በራሳችን ላይ እንዝመት!

አንዋሽ ፣ አንቅጠፍ ፣ አንሰደብ ፣ ቃላችንን እንጠብቅ

ቀጠሮዎችን እናክብር ፣ የማንተገብረውን አውራእኛ የማንችለውን


በሌሎች አንጫን : :

አላህ ልቦናችንን ያፅዳልን፣ አንደበታችንንም ይጠብቅልን፣ ከተግባሮቻችንም ያስማማልን።

ነብያችን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በጁምዓ ዥጥባ መግቢያ ላይ የሚከተለውን ይሉ እንደነበር ከጃቢር ኢብኑ ዐብዲላህ ተዘግቧል፦

<<ከንግግር ሁሉ የተሻለው የአላህ መፅሀፍ ነው ከመመሪያ ሁሉ በላጩ የሙሐመድ መመሪያ ነው። የነገሮች ሁሉ መጥፎ መጤ ነገሮች ናቸው። ሁሉም መጤ ተግባር ጥመት ነው>>

[ሙስሊም (867) ዘግበውታል]



የ2009 የትምህርት ዓመት የአንደኛ ሴሚስተር መጠናቀቅን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀ።

የደስታ መንገድ ...

ደስታ የሁሉም ህልም ነው፤ ሁሉም ሠው ከሐሳብና ጭንቀት ነጻ የሆነ ህይወትን ይመኛል። ሁሉም ግን የተመኘውን አያገኝም። ደስታን ለመፈለግ የጭንቀትና የዕድል ንፍግነትን መንገድ የሚከተልም አለ። ፍለጋው ተቃራኒ ውጤት ያስገኝለታል።

ደስታ ዝም ብሎ በፍላጎት ብቻ የሚገኝ ሀብት አይደለም። የሚመነጭባቸው እምነታዊና ድርጊታዊ መሠረቶች አሉት። ደስታን ለማግኘት እነዚሁ መሠረቶች ማወቅና መተግበር ያስፈልጋል።

ትልቁና ዋነኛው የደስታ መሠረት በመልካም ስራዎች የተደገፈ እውነተኛ ኢማን ነው። የውሸት ካባ የደረበ ኢማን፣ ከመልካም ስራዎች ራሱን ያራቀ ኢማን ፣ የአንደበት ብቻ ኢማን፣ ከጥቅም ጋር ሙቀትና ቅዝቃዜው ከፍና ዝቅ የሚል ኢማን ፣ በዚህ ውስጥ አይካተትም።

“ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን። ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን። ” «ነህል 97»

የማይለወጥ የአላህ ቃልኪዳን ነው። ንፁህ እምነትን ከመልካም ስራዎች ጋር ያቀናጀ የደስተኛ ህይወት ቃል አለው። በመጨረሻም ዓለም መልካም ስራ ውጤትን ያገኛል።

መልካም ስራዎችን ማፍራት የቻለ ንፁህ ኢማን ያለው ሠው ልቦናውና ተግባሩ በመልካም ባህሪያት የታጨቁ በመሆናቸው እነዚህ መልካም ባህሪያት በሚለግሱት የነጻነት ፣ የበጎ ሐሳቢነት ፣ የብሩህነት ዕይታ ምክንያት ደስታን ይጎናፀፋል። ሐሳብና ጭንቀት ወደ አጠገቡ የመድረስ ኃይል አይኖራቸውም። የንፁህ ኢማን ባለቤቶች ደስታና ስኬት ሲያጋጥማቸው ይህን ሁሉ ላደረገላቸው አላህ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ። የአላህ ቸርነት ባይሆን ህልማቸው የሚሳካ እንዳልነበረ በሙሉ ልብ ያምናሉ። ለዓለማቱ ጌታ ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ። አላህ የለገሳቸውን ችሮታም እርሱ በሚወደው ነገር ላይ ያደርጋሉ። ደስታቸው ሌላን ደስታ ይወልዳል፤ ስኬታቸው ሌላ ስኬትን ይጨምራል።

ችግርም ሲያጋጥማቸው በሠፊ ትዕግስት ያስተናግዱታል። በመከራ ፊት ጥንካሬያቸው አይሳሳም፤ በቁርጠኝነት ይጋፈጡታል። ከችግራቸው ለመውጣት በአላህ ታገዛለሉ። በትክክለኛ ሠነድ በተላለፈ ሐዲስ ነብዩ (የአላህ ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ ብለዋል *“የሙዕሚን ሁኔታ እጅግ የሚያስገርም ነው፤ ሁሉም ጉዳዩቹ መልካም ናቸው፤ ደስታ ሲያጋጥመው አላህን ያመሰግናል፤ (የነገሩ ፍፃሜም) መልካም ይሆንለታል። መከራ ሲያጋጥመው ትዕግስትን ይላበሳል፤ (የነገሩ ፍፃሜም) መልካም ይሆንለታል። ይህ የሚሆነው ለሙዕሚን ብቻ ነው። ”*

ንፁህ ኢማንን የታደለ ልብ እና ኢማንን የተነፈገ ልብ ክስተቶችን የሚያስተናግዱበት ሁኔታ በጣም የተለያየ ነው። ንፁህ ኢማን ክስተቶችን በምስጋናና በትዕግስት ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ሲያስተናግድ ኢማን የተነፈገ ልብ መስተንግዶው ከዚህ ይርቃል። ስኬት ካጋጥመው ኩራቱ አፍንጫውን ይሸገራል። ትህምክት እና ማን አለብኝነት ይጠናወተዋል። ስነ - ምግባሩ ይዘቅጣል። ከርሱ በላይ ደስተኛ እንደሌለ ለማሳየት ይሞክራል፤ ሆኖም ግን ደስታዎቹ አካላዊና ቁሳዊ ብቻ ናቸው፤ ወደ ውስጥ የጠለቀና ልብን በእርካታ የሚዳስሱ «መንፈሳዊ» አይደሉም። ከዚህ ጀብደኝነት በተቃራኒ ደግሞ መከራን በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ያስተናግዳል። በችግሩ ፊት በጥንካሬ ለመቆም አይችሉም፤ ፍርሃት ያንዘፈዝፈዋል። በችግሩ ወቅት አላህን ማስታወስ ስለማይችል የሚደርስበት ስቃይ ብዛትና ክብደት አይጠየቅም። ስነ - ልቦናው ይደቃል፤ መንፈሱ ይናወጣል። ራሱን መምራት ይሳነዋል።

وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَىٰ [٢٠:١٢٤]

«ከምሣዬም የዞረ ሰው ለእርሱ ጠባብ ኑሮ አለው። በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን። (ጣሃ - 124)

አላህ ሁሌም እርሱን የምናስታውስበት ንፁህ ኢማን ይለግሠን፤ እንደ ምስጉኖችና ምዕራብ በእኛና በኢማን ባዶነት መካከል መራራቅን ያድርግ !

ይዘት

- ቁርአን
- ይህ ነው ኢስላም
- እምነትሽን ጠብቂ !
- እጹብ ድንቆች
- ቤተሰባዊ ጉዳይ
- ነፍስን ማጥራት
- ካውንስሊንግ
- የኑሕ መርከብ
- ለ እህቶች
- ሸሪዓዊ ፈውስ
- የሴቶች ውርስ

تنبيهات

ተንቢሃት

ጠግቢያ

بسم الله الرحمن الرحيم

إنّ الحمد لله نحمده و نستعينه و نستغفره و نعوذ بالله من شرور أنفسنا و من سيئات أعمالنا من يهده الله فلا مضل له و من يضلل فلا هادي له و أشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له و أشهد أن محمدا عبده و رسوله صلى الله عليه و على آله و سلم.

أما بعد

ምስጋና ለዚያ ሁለቱን ተጣማሪ ወንድና ሴቶችን ለፈጠረ ፍቅርና ውዴታን በመሀከላቸው ላደረገው ጌታ ይሁን። ከርሱ ውጪ በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለው አንድና አጋር የሌለው ነው። ሙሀመድም የዕርሱ ባርያና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው በቤተሰቦቻቸው በባልደረቦቻቸውና እንዲሁም ፈለጋቸውን እስከ መጨረሻው በተከተሉ ሁሉ ላይ ይሁን።

ይህ በተለያዩ ጊዜያት በተንቢሃት የፌስቡክና ዋትሳፕ ግሩፕ ፖስት ሲደረጉ የነበሩ ትምህርቶች ጥንቅር ነው። ዳሰሳ የሚያደርገውም አማኝ ሴቶችን በተመለከቱ የተለያዩ ኢስላማዊ ህግጋት ላይ ሲሆን ሙስሊሟ ሴት ኢስላም የሰጣትን ክብር ፀጋ እና ልዕቅና በተወሰነ መልኩም ቢሆን እንድትረዳና ኢስላማዊ ግዴታዎቿን እውቀትን መሰረት ባደረገ መልኩ ትወጣ ዘንድ አስተዋፅዖ ለማበርከት ነው። ሙስሊሟ ሴትም ለዱንያዋም ይሁን ለአኼራዋ የሚጠቅማትን ትምህርቶች ትቀስምበታለች ፤ ኢስላም ለሴቶች የሰጠውንም ታላቅ ደረጃ ትረዳበታለች ብለን እናምናለን። የሙስሊም እህቶችንም ህይወት በመልካም የሚለውጥ እንዲያደርገው አላህን እንማፀነዋለን።

በኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር የዳሩል ሀዲስ የዓረብኛ ቋንቋ እና የሸሪዓ ትምህርቶች ኢንስቲትዩት ይህንን ስብስብ ከተወሰነ እርምትና ጭማሪዎች ጋር ማህበራዊ ሚዲያዎች ካላቸው የጎንዮሽ ጉዳት አንፃር ፌስቡክና መሰል ሚዲያዎችን ለማይጠቀሙ እህቶች ባሉበት ተደራሽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በዚህ መልኩ 2ኛውን **ጥንቅር** ለአንባቢያን ሲያቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል።

ለተንቢሃት ፔጅ አድሚኖችም በዚሁ አጋጣሚ ላቅ ያለ ምስጋና እናቀርባለን አንባቢያንም በቀጣይ ከፔጁ ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ አደራ እንላለን። በእውነትም መልካም ማበረታቻ ያሻዋል። በአላህ ፍቃድ ይህን ስራ ቀጣይ ለማድረግ እንሞክራለን ለዚህም የአንባቢንን ድጋፍ ያሻልና ተሳትትፏችሁ አይለየን እንላለን ! !

በመጨረሻም አላህ በስራችን ጥራት በንያችን ኢኽላስ እንዲሰጠን እንለምነዋለን።

ኢልያስ አወል

የኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር ስራ አስኪያጅ

ጥር 2009 / ጃንዋሪ 2017

በኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር
ዳሩል ሀዲስ የዓረብኛ ቋንቋ እና የሸሪዓ ትምህርቶች ኢንስቲትዩት

ቁርአን

በቁርአን ማመንና መለያዎቹ

ቁርአን የአላህ ንግግር ሲሆን ቃሉም ትርጉሙም ከአላህ የመነጨና ጂብሪል ከአላህ በመስማት ወደ ነቢዩ ﷺ ያስተላለፈው ከብረዛና ከመዛባት የተጠበቀ መፅሐፍ ነው።

የቁርአን መለያዎች

በአላህ መፃህፍት ማመን ከኢማን ማፅዘናት አንዱ ነው። ይሁንና ቁርአን ሌሎችን መፃህፍት የሚሰርዝ የሁሉም የበላይ ፈራጅና ነቢዩ ﷺ ከተላኩ በኃላ የሁሉም ሰውና ጋኔን መመሪያ በመሆኑ ከአላህ ዘንድ በወረዱና ከመበረዛቸው በፊት ባሉበት ሁኔታ በሁሉም መፃህፍት ማመን እንዳለ ሆኖ ተጨማሪ ቁርአንን ከሌሎች የምንለይባቸው እምነቶች አሉ። ከነዚህ መለያዎቹ

የቁርአን ጥሪና ህግጋቶቹ ሁሉንም ሰውና ጋኔን የሚያካትትና ማንም ቢሆን ቁርአንን መመሪያ ሳያደርግ አላህን በሌላ ህግጋት ማምለክ እንደማይፈቀድለት ማመን። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

{ تَبَارَكَ الَّذِي نَزَّلَ الْفُرْقَانَ عَلَى عَبْدِهِ لِيَكُونَ لِلْعَالَمِينَ نَذِيرًا }

(الفرقان : 1)

<<ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስጠንቃቂ ይሆን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ዋራት ተገባው።>> ፉርቃን 1

በሌላም የቁርአን አያት ለነብያችን ﷺ እንዲህ እንዲሉ አዟቸዋል፡-

{ وَأُوحِيَ إِلَيَّ هَذَا الْقُرْآنُ لِأُنْذِرَكُمْ بِهِ وَمَنْ بَلَغَ } (الأنعام : 19)

<<ይህም ቁርአን እናንተንና የደረሰውን ሰው ሁሉ በርሱ ላስጠነቅቅበት ወደኔ ተወረደ (በላቸው)>> አል አንዓም 19

ስለጋኔኖችም ሲናገር እንዲህ ይላል

{ إِنَّا سَمِعْنَا قُرْآنًا عَجَبًا }{ يَهْدِي إِلَى الرُّشْدِ فَآمَنَّا بِهِ } (الجن : 1، 2)

<እኛ አስደናቂ የኾነን ቁርአን ሰማንም፤ ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን)። በእርሱም አመንን።>> አል ጂን 1-2

ከፊቱ የነበሩትን መፃህፍት የሰረዘ መሆኑን ማመን። የመፅሐፍ ባለቤቶችም ሆኑ ሌሎች ቁርአን ከወረደ በኃላ በሌላ መመሪያ አላህን ማምለክ እንደማይችሉ፣ ቁርአን ሀላል ያደረገው እንጂ ሀላል እንደሌለ ቁርአን ሀራም ካደረገው ውጭ ሀራም እንደሌለ ማመን። አላህ እንዲህ ብሏል

{ وَمَنْ يَبْتَغِ غَيْرَ الْإِسْلَامِ دِينًا فَلَنْ يُقْبَلَ مِنْهُ } (آل عمران : 85)

<<ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም>> አል ዒምራን 85

{ إِنَّا أَنْزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ لِتَحْكُمَ بَيْنَ النَّاسِ بِمَا أَرَاكَ اللَّهُ }

(النساء : 105)

<<እኛ በሰዎች መካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት አወረድን።>> አል ኒሳእ 105

ቀደም ብሎ በተጠቀሰውም የአህመድ ኪታቦችን መፅሐፍ ማንበብ በሚከለክለው የጀቢር ሀዲስ ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል

(. . . » والذي نفسي بيده لو أن موسى

كان حيًّا ما وسعه إلا أن يتبعني » واه الإمام أحمد في

المسند : 3 / 387 ، وغيره

"ነፍሴ በእጁ ባለው ጌታ እምላለሁ ሙሳ እንኳን ሀያው ቢሆን እኔን ከመከተል ውጭ አማራጭ የለውም።" (ሙስነድ አህመድ 3/387)

"ነፍሴ በእጁ ባለው ጌታ እምላለሁ ሙሳ እንኳን ሀያው ቢሆን እኔን ከመከተል ውጭ አማራጭ የለውም።"

ቁርአን ያመጣው ህግጋት ከሌሎች መፅሐፍት በተቃራኒ ገርና ቀላል ነው። በአንፃሩ የቀድሞ መፅሐፎች ብዙ ከባድ ሸክም ነበረባቸው። አላህ እንዲህ ብሏል

{ الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ الرَّسُولَ النَّبِيَّ الْأُمِّيَّ الَّذِي يَجِدُونَهُ مَكْتُوبًا عِنْدَهُمْ فِي التَّوْرَاةِ وَالْإِنْجِيلِ يَأْمُرُهُمْ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَاهُمْ عَنِ الْمُنْكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ الطَّيِّبَاتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ الْخَبَائِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَالْأَغْلَالَ الَّتِي كَانَتْ عَلَيْهِمْ } (الأعراف : 157)

<<ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነቢይ የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለኾኑት (በእርግጥ እጽፍለታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዛቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል። መጥፎ ነገሮችንም በእነርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) ያነሳላቸዋል።>> አል አዕራፍ 157

ቁርአን አላህ ለመጠበቅ ኃላፊነት የወሰደለት ብቸኛው መፅሐፍ ሲሆን ይህ ዋቢቃ ቃሉንም ትርጉሙንም የሚያካትት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል

{ إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ } (الحجر : 9)

<<እኛ ቁርአንን እኛው አወረድነው። እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን።>> ሂጅር 9

{ لَا يَأْتِيهِ الْبَاطِلُ مِنْ بَيْنِ يَدَيْهِ وَلَا مِنْ خَلْفِهِ تَنْزِيلٌ مِنْ حَكِيمٍ حَمِيدٍ } (فصلت : 42)

<<ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም። ጥበበኛ ምስጉን ከኾነው ጌታ የተወረደ ው።>> ፉሲለት 42

{ إِنَّ عَلَيْنَا جَمْعَهُ وَقُرْآنَهُ }{ فَإِذَا قَرَأْنَاهُ فَاتَّبِعْ قُرْآنَهُ } ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا بَيَانَهُ } (القيامة : 17–19)

<<(በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡና ማንበቡ በእኛ ላይ ነውና። ባነበብነውም ጊዜ (ካለቀ በኋላ) ንባቡን ተከተል። ከዚያም ማብራራቱ በእኛ ላይ ነው።>> አል ቂያማህ 17-19

በመጨረሻው አንቀፅ ትርጉም ዙሪያ ኢብን ከሲር እንዲህ ይላሉ

"ቁርአን ከተነበበና ከተሸመደደ በኃላ እናብራራልሃለን ትርጉሙንም በምንፈልገው መልኩ እናሳውቅሃለን።"

አላህ ከነቢዩ ﷺ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ቁርአንን በመሸምደድ፣ በመጠበቅ፣ ትርጉሙን በመረዳትና በቁርአን በመስራት ኃላፊነትን በሚገባ የሚወጡ ምሁራንን አመቻችቷል። እነዚህ ዑለማዎች ቁርአንን ለመንከባከብ የሚያስችሉ መድረኮችን ሁሉ በመጠቀም በቁርአን የተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ የተለያዩ መፅሐፎችን ደርሰዋል። አንዳንዱ በትርጉሙ ዙሪያ ሌላው በንባቡ ዙሪያ፣ ስለመህከምና ሙተሻቢህ፣ መክና መዲና ስለወረዱ ምዕራፎች፣ ስለሀግታቶቹ፣ ስለስራቹና ተሰራዢ፣ አንቀፆቹ ስለወረዱባቸው ምክንያቶች፣ ስለቁርአን ምሳሌዎች፣ ስለቁርአን ተአምራት፣ ስለቃላት ትርጉሞች፣ ስለ ሰዋሰውና ሌሎችም የቁርአን ትምህርቶች በተለያየ መልኩ በመፃፍ አላህ በነዚህ ዑለማዎች ምክንያት ቁርአን የተጠበቀ ሆኖ እንዲቆይ አድርጓል።

ቁርአን በማንኛውም ፍጡር አምሳያ ሊመጣ የማይቻል በአገላለፅ ብቃቱ ጣሪያ የነካ በመሆኑ ሰዎችና ጋኔን በአጠቃላይ የቁርአንን አምሳያ ወይም ከፊሉን ከቻሉ እንዲያመጡ በሶስት ደረጃ ሞከራቸው።

በመጀመሪያ

{ أَمْ يَقُولُونَ تَقَوَّلَهُ بَلْ لَا يُؤْمِنُونَ }{ فَلْيَأْتُوا بِحَدِيثٍ مِثْلِهِ إِنْ كَانُوا صَادِقِينَ } (الطور : 33 ، 34)


ወይም «ቀጠፈው ይላሉን?» አይደለም፤ በእውነቱ አያምኑም። እውነተኞችም ቢኾኑ መሰሉ የኾነን ንግግር ያምጡ።>> ጡር 33-34

በፍፁም የማይችሉት ነገር መሆኑን ደግሞ እንዲህ በማለት አፀና።

{ قُلْ لَئِنِ اجْتَمَعَتِ الْإِنْسُ وَالْجِنُّ عَلَى أَنْ يَأْتُوا بِمِثْلِ هَذَا الْقُرْآنِ لَا يَأْتُونَ بِمِثْلِهِ وَلَوْ كَانَ بَعْضُهُمْ لِبَعْضٍ ظَهِيرًا }

(الإسراء : 88)

«ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርአን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆንም እንኳ ብጤውን አያመጡም» በላቸው።>> (አል ኢስራእ 88)



ቁርአን

{ كَذَلِكَ نَقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنْبَاءِ مَا قَدْ سَبَقَ وَقَدْ آتَيْنَاكَ مِنْ لَدُنَّا ذِكْرًا } (طه : 99)

<<እንደዚሁ በእርግጥ ካለፉት ወሬዎች ባንተ ላይ እንተርክለን። ከእኛም ዘንድ ቁርኣንን በእርግጥ ሰጠንህ።>> ጣሃ 99

ቁርአን ከመጨረሻው የመጀምያሚያው ላለፉት መስካሪ የሆነ መፅሐፍ ነው።

{ نَزَّلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِمَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَأَنْزَلَ التَّوْرَاةَ وَالْإِنْجِيلَ } { مِنْ قَبْلُ هُدًى لِلنَّاسِ وَأَنْزَلَ الْفُرْقَانَ } (آل عمران : 3 ، 4)

<<ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን (ቁርኣንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ። ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል። (ከቁርኣን) በፊት ለሰዎች መሪ አድርጎ (አወረዳቸው)። ፉርቃንንም አወረደ።>> (አል ዒምራን 3-4)

{ وَأَنْزَلْنَا إِلَيْكَ الْكِتَابَ بِالْحَقِّ مُصَدِّقًا لِمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ الْكِتَابِ وَمُهَيْمِنًا عَلَيْهِ } (المائدة : 48)

<<ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን።>> አል ማኢዳህ 48

{ شَرَعَ لَكُمْ مِنَ الدِّينِ مَا وَصَّى بِهِ نُوحًا وَالَّذِي أَوْحَيْنَا إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِ إِبْرَاهِيمَ وَمُوسَى وَعِيسَى أَنْ أَقِيمُوا الدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا فِيهِ } (الشورى : 13)

<<ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በእርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገላችሁ። ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን ያንንም በእርሱ ኢብራሂምን ሙሳንና ዒሳንም ያዘዘንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም አትለያዩ ማለትን (ደነገግን)።>> ሹራ 13

ቁርአን የቀድሞዎችን ነቢያትና ህዝቦቻቸውን ታሪክ ባለተለመደ ልዩ ሁኔታ የሚተርክ ነው።

{ وَكُلًّا نَقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنْبَاءِ الرُّسُلِ مَا نُثَبِّتُ بِهِ فُؤَادَكَ } (هود : 120)

<<ከመልክተኞቹም ዜናዎች (ተፈላጊውን) ሁሉንም ልብህን በርሱ የምናረካበትን እንተርክልሃለን።>> ሁድ 120

{ ذَلِكَ مِنْ أَنْبَاءِ الْقُرَى نَقُصُّهُ عَلَيْكَ مِنْهَا قَائِمٌ وَحَصِيدٌ } (هود : 100)

<<ይህ (የተነገረው) ከነተሞቹ ወሬዎች ነው። ባንተ ላይ እንተርከዋለን። ከእርሷ ፋናው የቀረና ሙሉ በሙሉ የተደመሰሰ አለ።>> ሁድ 100

በማስከተል አምሳያው የሆኑ አስር ምዕራፎችን እንዲያመጡም ቢሞክራቸው አልቻሉም።

{ أَمْ يَقُولُونَ افْتَرَاهُ قُلْ فَأْتُوا بِعَشْرِ سُوَرٍ مِثْلِهِ مُفْتَرَيَاتٍ وَادْعُوا مَنِ اسْتَطَعْتُمْ مِنْ دُونِ اللَّهِ إِنْ كُنْتُمْ صَادِقِينَ } (هود : 13)

ይልቁንም «(ቁርኣንን) ቀጣጠፈው» ይላሉን? «እውነተኞች እንደሆናችሁ ብጤው የሆኑን ዐስር የተቀጣጠፉ ሱራዎች አምጡ። ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን (ረዳት) ጥሩ» በላቸው። (ሁድ 13)

ከዚያም በሶስተኛው አምሳያው የሆነ አንድ ምዕራፍ እንኳን እንዲያመጡ ቢሞክራቸውም አልቻሉም።

{ أَمْ يَقُولُونَ افْتَرَاهُ قُلْ فَأْتُوا بِسُورَةٍ مِثْلِهِ وَادْعُوا مَنِ اسْتَطَعْتُمْ مِنْ دُونِ اللَّهِ إِنْ كُنْتُمْ صَادِقِينَ } (يونس : 38)

በእውነትም «(ሙሐመድ) ቀጣጠፈው» ይላሉን= «ይህ ከሆነ መሰሉን (እንዲት) ሱራ አምጡ። ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን ሁሉ (ረዳት) ጥሩ። እውነተኞች እንደሆናችሁ (ተጋግዛችሁ አምጡ)» በላቸው። (ዩኑስ 38)

ከቁርአን ትንሹ ምዕራፍ ባለሶስት አንቀፅ ምዕራፍ ሲሆን ይህንን እንኳን ተመሳሳዩን ማምጣት የማይችሉ መሆናቸው የቁርአንን ኃያልነት ያረጋግጣል።

አላህ በቁርአን አማካኝነት ለሰዎች ለሃይማኖታቸውም ሆነ ለአለማዊ ህይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ገልጿል።

{ وَنَزَّلْنَا عَلَيْكَ الْكِتَابَ تِبْيَانًا لِكُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَى لِلْمُسْلِمِينَ } (النحل : 89)

<<መጽሐፉንም ለሁሉ ነገር አብራሪ፣ መሪም፣ እዝነትም፣ ለሙስሊሞችም አብሳሪ ኾኖ ባንተ ላይ አወረድነው።>> ነህል 89

{ مَا فَرَّطْنَا فِي الْكِتَابِ مِنْ شَيْءٍ } (الأنعام : 38)

<<በመጽሐፉ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም >> አል አንዓም 38

ኢብን መስዑድ እንዲህ ይላሉ "በቁርአን ሁሉም እውቀቶች ወርደዋል ማንኛውም ነገር ቁርአን ውስጥ ተዘርዝሮልናል።"

አላህ ይህን ቁርአን ለአስተንታኞች ገር በማድረግ አቅሎታል። ይህ ደግሞ ከጕሉ የቁርአን መለያዎች አንዱ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል

{ وَلَقَدْ يَسَّرْنَا الْقُرْآنَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِنْ مُدَّكِرٍ } (القمر : 17)

<<ቁርኣንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው። ተገንዛቢም አልለን?>> አል ቀመር 17

{ كِتَابٌ أَنْزَلْنَاهُ إِلَيْكَ مُبَارَكٌ لِيَدَّبَّرُوا آيَاتِهِ وَلِيَتَذَكَّرَ أُولُو الْأَلْبَابِ } (ص : 29)

<<(ይህ) ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው። አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑትና የአእምሮዎች ባለቤቶችም እንዲገሰጹ (አወረድነው)።>> ሷድ 29



ይህ ነው ኢስላም

ብቀላ ወይስ ምህረት...?

ኢስላም ስንሰጥም ሆነ ስንነሳ ለአላህ ብቻ እንዲሆን ይፈልግብናል። ይህ ስሜትን ማስደሰትን መሰረት ያደረገ ሳይሆን አላህን መታዘዝን ብቻ ኢላማ ያደረገ ነው። መልካም ለዋለልን መልካምን መዋል ልንመጻደቅበት የሚገባን ነገር ሳይሆን እርሱ በኛ ላይ ያለው ሀቅ ነዉና ተገቢ ነው። መልካም ለማይዉል ሰው መልካም መዋል ግን ከባድ ጀግንነት የሚጠይቅ በመሆኑ አላህ እንዲህ አይነቱን ግንኙነት በመልካም እንድንቀጥል አዞናል። እራሱን አሸንፎ ለበደለው ይቅር የሚል ሰው በዱንያም ይሁን በአኼራ አላህ ደረጃውን ከፍ ያደርገዋል፤ ስሜቱን፣ ቁጭቱን አሸንፏል እና ድልን ያቀዳጀዋል።

قال رَسُولُ اللهِ ﷺ : (وَمَا زَادَ اللهُ عَبْداً بِعَفْوٍ إِلاَّ عِزّاً) رواه مسلم من حديثَ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፤ "አንድ ባሪያ ይቅር በማለቱ አላህ አሸናፊነትን እንጂ አይጨምርለትም" ሙስሊም ዘግበዉታል

ይቅርታ ለሚል ሰው አላህ ታላላቅ ሽልማቶችን ቃል ገብቶለታል። አላህ እንዲህ ብሏል፤

(وَسَارِعُوا إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ * الَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي السَّرَّاءِ وَالضَّرَّاءِ وَالْكَاظِمِينَ الْغَيْظَ وَالْعَافِينَ عَنِ النَّاسِ ۗ وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُحْسِنِينَ) آل عمران/ 133،134

(ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ሆነች ገነት፥ አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትሆን ተቻኮሉ። ለነዚያ፤ በድሎትም ኾነ በችግር ለሚለግሱት፥ ቁጭትንም ገቺዎች፥ ከሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለሆኑት (ተደግሳለች) ፤ አላህም በጐ ሠሪዎችን ይወዳል።) آل ዒምራን 133 - 134

መረጃዎችን ስናጤን ይቅር ባይነትን የሚያበረታቱ ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለዚህም ኡለማዎች በቀልን ከማይወደዱ ባህሪያት ይመድቡታል። ይሁንና ሰዎች ይለያያሉ፤ አንዳንዱ በቀልን መፈጸም ቁጭቱን መወጣቱ አይቀርምና ይህ ተግባር ገደብ ባለው ሁኔታ ተፈቅዶ እናገኛለን። ተበዳይ ሀቁን የማስመለስ ብሎም የደረሰበትን በደል የመበቀል ጉዳይ እንደ መብት ቢፈቀድም ይህ እርምጃ ግን ብዙ ገደቦች ያሉበት እና አስቸጋሪ ነው። በደልን በከፋ በደል መመለስ ፍጹም የተከለከለ ነው። ወሰን ሳያልፉ መበቀልም እጅግ አስቸጋሪ ነው። ይህ ጠንቃቃነትን የሚሻ በመሆኑ ብዙዉን ጊዜ አይሳካም። በመሆኑም ተበዳይ ዞሮ በዳይ ይሆናል። ስለዚህም ይህ ርዕስ በቁርዓን ዉስጥ ባብዘኛው ከይቅር ባይነት ጋር ተያይዞ እናገኘዋለን። አላህ እንዲህ ብሏል፤

فقال الله تعالى : (وَإِنْ عَاقَبْتُمْ فَعَاقِبُوا بِمِثْلِ مَا عُوقِبْتُم بِهِ ۖ وَلَئِن صَبَرْتُمْ لَهُوَ خَيْرٌ لِّلصَّابِرِينَ) **النحل 126**

(ብትበቀሉም፣ በርሱ በተቀጣችሁበት ብጤ ተበቀሉ፤ ብትታገሡም፣ እርሱ ለታጋሾች በእርግጥ በላጭ ነው።) አነህል 126

قال تعالى:(فَمَنِ اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ فَاعْتَدُوا عَلَيْهِ بِمِثْلِ مَا اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ وَاعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ مَعَ الْمُتَّقِينَ) **البقرة: 194**

(በእናንተም ላይ (በተከበረው ወር) ወሰን ያለፈባችሁን ሰው በናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በርሱ ላይ ወሰን እለፉበት። አላህንም ፍሩ አላህ ከሚፈሩት ጋር መኾኑንም ዕወቁ።) አል በቀራህ 194

قال تعالى: وَجَزَاءُ سَيِّئَةٍ سَيِّئَةٌ مِّثْلُهَا ۖ فَمَنْ عَفَا وَأَصْلَحَ فَأَجْرُهُ عَلَى اللَّهِ ۚ إِنَّهُ لَا يُحِبُّ الظَّالِمِينَ) الشُّورى: 40

(የመጥፎም ነገር ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት፤ ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው። እርሱ በደለኞችን አይወድም።) ሹራ 40

ይህ ከመሆኑ ጋር፤ የበዳይን ሰው ጥፋት ይቅር ማለት ከመበቀል የተሻለ መሆኑን በዛው አንቀጽ ላይ ተናግሮአል። (ይቅርም ያለና ያሳመረ ሰው ምንዳው በአላህ ላይ ነው።) ጠንካራነት እና ጀግንነት የሚለካዉም መጉዳት እየቻሉ ለአላህ ሲሉ በመተው ይቅርታ ማድረግ ላይ ነዉና አላህ እጅግ ከባድ ምንዳን አዘጋጅቶለታል።

ይህ በግለሰቦች መካከል እንደሚከሰቱ ጠቦች፣ መጎዳዳቶች እና መሰል ድንበር ማለፎችን የሚመለከት ነው። በቀል ለሁሉም በደሎች አይፈቀድም፤ አንዳንዱ ጉዳይ ለፍርድ የሚቀርብ እንጂ እራሱ ማስፈጸም የማይፈቀድለት ነው። እንደዚሁ፤ ከበቀል ምህረት የሚቀደመው መልካም ሆኑ ሲገኝ ብቻ ነው። ድንበር ማለፉ የተከሰተው በአላህ ሀቅ ላይ ከሆነ ወንጀል እንዲፈጸም መፍቀድን ይቅር ባይነት አድርጎ መቁጠር ተገቢ አይደለም።

ለምሳሌ፤ ተደጋጋሚ ጾታዊ ጥቃቶች የሚደርሱባት ሴት ይቅር ማለት የሻለል ብላ ወንጀሎች እንዲደጋገሙ መንገድ ከከፈተች ትክክል አይሆንም። የትዳር ጓደኛውን ቢያማግጥበት ወይም ፍርደ ገምድልነትን ቢያሳይ፤ የእሱን ባለቤት ለማማገጥ በመሞከር ወይም ፍትህን በማጓደል መበቀል ፍጹም የተከለከለ ነው። (ወሰን ባለፈው ብጤ በርሱ ላይ ወሰን እለፉበት) የተባለው ወንጀል መፈጸምን አያካትትም ማለት ነው።

ነገር ግን የተበደለው ግለሰ በደል ከሆነ ይቅር ማለት እና መማር ተገቢና የተሻለ ነው።

فعن عائشة -رضي الله عنها- أنَّها قالت

(وما انتقم رسول الله صلى الله عليه وسلم لنفسه) رواه البخاري ومسلم

እናታችን አዒሻ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ እንዲህ ብለዋል፡ (የአላህ መልዕክተኛ ለራሳቸው ሲሉ መቼም ቢሆን ተበቀለው አያውቁም . . .)

ታላቁ የቁርዓን ሙፈሲር አል ኢማም አልቁርጡቢ እንዲህ ብለዋል፤

" (የመጥፎም ነገር ዋጋ ብጤዋ መጥፎ ናት፤) ሹራ 40 ኡለማዎች እንዲህ ብለዋል፤ አላህ ምዕመናንን ሁለት አይነት አድርጓቸዋል።

ከፊሎቹ በደልን ይቀር የሚሉ ሲሆኑ ከአንቀጹ ቀደም ብሎ 37ኛ አንቀጽ

وَإِذَا مَا غَضِبُوا هُمْ يَغْفِرُونَ

(በተቆጡም ጊዜ እነሱ የሚምሩ ለሆኑት።) ሹራ 37 በማለት እነሱን አውስቶ ጉዳዩን ጀምሮታል። ከፊሎቹ ደግሞ በደልን የሚበቀሉ ናቸው። አስከትሎ የመበቀልን ወሰን ገለጸ። ወሰን ማለፍ እንደማይገባ ተናገረ።" አልጃሚዕ ሊአህካሚል ቁርዓን

አላህ የበደልን ወሰን ከገለጸበት አንቀጽ በፊት 39ኛው አንቀጽ በፊት የምዕመናን በደልን መመለስን መግለጹ በቀልን የሚያበረታታ አይደለም። ምክኒያቱም፤ በቀጣዩ አንቀጽ የተሻለዉና በላጩ ምህረት ማድረግ መሆኑ ከመገለጹም ባሻገር፤ ቀጣዩ አንቀጽ ላይ የተገለሰውን አፈጻጸም ሚተገብሩትን ነው። ኢብኑ ረጀብ እንዲህ ብለዋል፤ "አላህ

وَالَّذِينَ إِذَا أَصَابَهُمُ الْبَغْيُ هُمْ يَنتَصِرُونَ الشُّورى: 39

(ለነዚያም በደል በደረሰባቸው ጊዜ እነሱ (በመሰሉ) የሚመልሱ ለሆኑት (በላጭና ኗሪ ነው)።) ሹራ 39

"ይህ ይቀር ከማለት ጋር የሚጋጭ አይደለም። በደልን መመለስ መቻልን በማሳየት መጀመሪያው በደልን የሚመልሱ ሲሆን መበቀል እንደሚችሉ አሳይተው ይቅርታ ማድረግን ማስከተላቸው የተሟላና የተሻለ ያደርገዋል።" ጃሚዑል ዑሉም ወልሂከም 1/450

ምንም እንኳን ሰዎች በሚደርስባቸው በደል ምክኒያት ለበቀል ቢነሳሱም ለጥፋት ከሚዳርጓቸው ነገሮች መካከል መናደድ፣ ስሜታዊነት፣ በቀልን እንደ ዝና እና ጀግንነት መቁጠር፣ ትዕግስት እና ይቅር ባይነትን እንደ ባህሪ አለመላበስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከላይ መግቢያዬ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፤ ይቅር ባይነት ከአላህ ከፍተኛ ምንዳን የሚያስገኝ መልካም ባህሪ ነውና በብቀላ ቁጭትን ከመወጣት ብሎም ድንበር በማለፍ ጸጸት ዉስጥ ከመዉደቅ ከአላህ የሚያገኘውን ምንዳ በማሰብ በቀልን መራቅ ብልህነት ነው።



የአላህ መልክተኛ(ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦

"ሦስት ሴት ልጆች ወይም ሦስት እህቶች ወይም ሁለት ሴት ልጆች ወይም ሁለት እህቶች ያሉት ከነሱ ጋር ያለውን አኗኗር ያሳመረና የነሱን ሐቅ በመጠጣት ያላህን የፊት ጀነትን ይገባል ::"

[ሰሒሑ ሲብኑ ሒባን(446)]

እምነትሽን ጠብቂ!



ላለመደናገር ንቃትን እናዳብር!!

በተለያዩ ቢድዓዎች ውስጥ የተዘፈቁና ሽርክን ለማስፋፋት የሚሯሯጡ አንጃዎችን ለሚፈፅሙት የቀብር አምልኮ የሽርክ ተግባራት ሁሉ ደጋፊ የሚሆን መረጃ ለማቅረብ ዘወትር ደኢፍና መውዱእ የሆኑ ዘገባዎችን ሲቀባበሉና በከንቱ ሲዳክሩ ይስተዋላሉ። ይሁንና አህሉሱና ህቅን ከመረጃው ጋር ግልፅ በማድረግ አንገት እንዲደፋ አድርገዋቸዋል።

أَلَا لِلَّهِ الدِّينُ الْخَالِصُ ۚ وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مِن دُونِهِ أَوْلِيَاءَ مَا نَعْبُدُهُمْ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَا إِلَى اللَّهِ زُلْفَىٰ إِنَّ اللَّهَ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ فِي مَا هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ۗ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي مَنْ هُوَ كَاذِبٌ كَفَّارٌ[الزمر : 3]

«ንቁ! ፍጹም ከማጋራት የፀዳና ምርጥ የኾነው ሃይማኖት የአላህ ብቻ ነው። እነዚያም ከእርሱ ሌላ (አማልክትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አናመልካቸውም» (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚወዛገቡበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም።» ዙመር 3

የኢስላም መገለጫ አላህን ብቻ ማምለክ 'ተውሂድ' እንደሆነ የሚያስረዱ፤ ባእድ አምልኮን የሚኮንኑ፣ ለቀብር አምልኮ የሚያበቁ መንገዶችን ሁሉ ከወዲሁ የሚዘጉ የቁርአን እና የሱና መረጃዎች እጅግ በርካታ ናቸው።

አለሀምዱሊላህ! ቁቡሪዮች ለሚያነሷቸው ውዥንብሮች ሁሉ አህሉሱና ከበቂ በላይ በሆኑ መረጃዎችና ማብራሪያዎች ምላሽ በመስጠት ህቅን ግልፅ አድርገዋል። ሹቡሀቶቻቸውን ያንኮታኮቱ መሀይምነታቸውንም ያሳዩ ጥናቶች ቀርበዋል፤ በመቅረብም ላይ ናቸው!!

እነዚህ የቢድዓ አራማጆች እንደሸረሪት ድር የደከሙ መረጃዎቻቸው ሁሉ ተበጣጥሰው ከወደቁባቸው በኃላ፤ ከአመታት በፊት የመልእክተኛው ቀብር ምስል ነው በማለት የተሰራጨ የቀብር ፎቶግራፍ በአማርኛ "የነብዩ ﷺ ቀብር" የሚል መግለጫ ፅፈውበት በማህበራዊ ድረገፆች በተደጋጋሚ ሲለጥፉ አስተውያለው። ነገሩ አዲስ ነውና አንዳንድ ውንድሞችና እህቶችም በግል ፎቶዉን በመላክ ትክክለኛነቱን ጠይቀውኛል።

ስለዚህም በፎቶው ዙሪያ የተባሉ ነገሮችን ከቃኘው በኃላ በፎቶው ዙርያ ጥቂት ነጥቦችን ለመጠቆም ብእሬን አንስቻለው።

ይህ ፅሁፍ ለምን አስፈለገ? የነብዩ ﷺ ቀብር ነው ቢሉስ ምን የሚጨምርላቸው መረጃ አለ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ምንም እንኳ ቀብርን በዚህ መልኩ ከፍ አድርጎ መገንባት በማያጠራጥር መልኩ የተከለከለ በመሆኑ ይህ ፎቶ መረጃዎችን ሊሸር እንደማይችል የታወቀ ቢሆንም፤ ለአንዳንድ የዋሆች ግን "የመልእክተኛው ቀብር እንደዚህ ከሆነ፤ የሸኾቻችንን ዶሪህ ለምን አንገነባም? አናሸበርቅም?? የሚል ብዥታን ሊፈጥርባቸው ይችላል። ስለዚህም አላህ በመታገዝ ተከታዮቹን አጠር ያሉ ማስገንዘቢያዎች ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

[1] የቁቡርዮች ቅጥፈት፦

ተከታዮቹ ነጥቦች ፎቶው የመልእክተኛው ቀብር ምስል እንዳልሆነና ቅጥፈት መሆኑን ያመላክታሉ፤

1.1) በፎቶው ላይ ቀብሩ በአንድ ክፍል ውስጥ ለብቻው ተነጥሎ ይታያል። ይህ ደግሞ ከእውነታው በእጅጉ የራቀ ነው። ማንኛውም ቀብራቸውን በአካል የጎበኘ ሰው ለመመልከት እንደሚችለው በመካከላቸው ምንም አይነት ርቀት የለም በሚያስብል መልኩ የመልእክተኛውን ቀጥሎ የአቡበክርን ቀጥሎም የዑመርን ቀብር ያገኛል። ይህ ፎቶ ከነብዩ ቀብር ጋር አንድ ሜትር የማይሞላ ርቀት ከንናቸው ያረፉትን የሁለቱን ምትኮች ቀብር አለማካተቱ ትክክኛ ላለመሆኑ አይነተኛ ማሳያ ነው።

1.2) በፎቶው ላይ ቀብሩ ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ እንደሆነ ይታያል። ይህም ከእውነታው የራቀ ነው። በታሪክ እንደሚታወቀው መልእክተኛው የተቀበሩት ከመስጂዳቸው ጋር ግድግዳ በሚለየው የአዒሻ ቤት ውስጥ ሲሆን ይህ ቤት ደግሞ በጣም ጠባብ ነበር። እርዝመቱ በሰው ቁምት ያክል ሲሆን ስፋቱ ደግሞ ከበር እስከ ግድግዳ ከስድስት እስከ ሰባት ክንድ ያክል ጎኑም ከስምንት እስከ ዘጠኝ ክንድ ብቻ ነበር። ፎቶው ከቀብሩ ውጪ ሰፊ መንቀሳቀሻ ቦታ እንዳለውና ብዙ ቁሳቁሶች እንደተቀመጡበት ማሳየቱ ትክክለኛ ላለመሆኑ ግልፅ ማሳያ ነው።

1.3) ቤቱ እራሱ ሆኖ የቀድሞ ይዞታው ትንሽ ሲሆን አሁን ግን ሰፍቷል የሚል መከራከሪያ ቢቀርብ፤ ይህ የቤቱ ይዞታና ስፋት እንዳልተቀየረ የሚያሳየን፤ ታዋቂው ፍትሀዊ መሪ ኡመር ኢብኑ አብዲልአዚዝ በ86 አመተ ሂጅራ የመልእክተኛው ቀብር ያለበትን ይህንን ክፍል ምንም ክፍተት ሳይተው በጠንካራ ግንብ መድፈኑ ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ቀብሩ ላይ ጥቃት የመፈፀም ሙከራዎች በመስተዋላቸው ምክኒያት በ557ዓ.ሂ የወቅቱ መሪ ኑረዲን ዚንኪ ረሂመሁላህ የቤቱን ዙሪያ አስስቆፈሮ የእርሳስ ማእድን በማቅለጥ በጠንካራ መሰረት ላይ ገንብቶታል።

ለተጨማሪ ዝርዝሩር በ911ዓ.ሂ ያለፉት አሊ አብዲላህ አስምሁዲይ የፃፉትን «ወፋኡል ወፋ ቢአኽባሪ ዳሪል ሙስጠፋ» 2/648-650 ይመልከቱ። ከዚህ በኃላ ቤቱ ሰፍቷል የሚል መከራከሪያ ሊቀርብ አይችልም።

1.4) በፎቶው ላይ ቀብሩ ተለቅ ያለ ሳጥን ይመስላል። የመልእክተኛው አካል ደግሞ ለህድ ተቀፍሮ በክብር ቀብር ውስጥ አረፈ እንጂ በሳጥን አልተቀመጠም።

በመዲና እና በጀዚረተል አረብ ቅድመ ኢስላምም ይሁን አሁን በሳጥን የመቅበር ልመድ የለም። ይህም ሌላኛው የፎቶዉን ትክክለኛ አለመሆን የሚያሳይ መረጃ ነው።

1.5) በሳጥን ተቀብረው ሳይሆን ቀብሩ ከፍ ያለ ስለሆነ ነው ከተባለ፤ መልእክተኛው በህይወት ሳሉ ቀብርን ከፍ አድርጎ ከመገንባት ባልደረቦቻቸውን ሲያሳስቡና ሲያስጠነቅቁ ኖረዋል።

عَنْ أَبِي الْهَيَّاجِ الْأَسَدِيِّ، قَالَ : قَالَ لِي عَلِيُّ بْنُ أَبِي طَالِبٍ : أَلَا أَبْعَثُكَ عَلَى مَا بَعَثَنِي عَلَيْهِ رَسُولُ اللهِ ﷺ ؟ أَنْ لَا تَدَعَ تِمْثَالًا إِلَّا طَمَسْتَهُ ، وَلَا قَبْرًا مُشْرِفًا إِلَّا سَوَّيْتَهُ

رواه مسلم

አቢልሀያጅ አል አስዲይ በተዘገበ ሀዲስ አሊይ ኢብኑ አሊ ሧሊብ እንዲህ ብለዋቸዋል፤ «የአላህ መልእክተኛ የሰጡኝን ተልእኮ ላስተላልፍልህን? "የሚመለክ ሀውልት አግኝተህ ሳትሰባብረው፤ ከመሬት ከፍ ያለ ቀብርም አግኝተህ ከመሬት ጋር ሳታስተካክለው አትተው» ሙስሊም ዘግበውታል

የኢስላም ሊቃውንት እንዳስገንዘቡን ቀብር መሆኑን ለማሳወቅ ያክል በአንድ ስንዝር ከፍታ ከመሬት ጋር ማስተካከል ተገቢ ነው።

ይህ ሀዲስ ብቻ ሳይሆን በርካታ ሀዲሶች ይህንን መልእክት ያጠናክራሉ። ታዲያ ሰሀቦች በዚህ መልኩ አደራ የሚባባሉበትን ጉዳይ ቸል በማለት የመልእክተኛውን ቀብር በዚህ ከፍታ የሚገነባ ማን አለ?? በፍፁም!! ይህ ፎቶ የቁቡሪዮች ማጭበርበሪያ መሆኑ አያጠረጥርም!!



እምነትሽን ጠብቂ!



ስንዲት ዝሙተኛ የተጠማ ውሻን ውሃ በማጠጣቷ የተነሳ ጀነት ገባች

ደህቺ ሴት በጥም የተነሳ ሞት ስፋፍ ላይ የደረሰን ውሻ ጥሙን እንዲያረካ እና ዳግም ህይወት ስመዝራት ምክንያት በመሆኗ ስላህ ወንጀሏን ማራት!

ሰዎችን ተውሒድ የሚያጠጣ
ዱዒ ምን ያህል ምንዳ ያገኝ ይሆን!

ሸይኽ ዐብዱረዛቅ ዐብዱል ሙህሲን ዓባድ(ሐፊዘሁላህ)



1.6) ቀብሩ ያለበት ቤት እጅግ ያሸበረቀ መሆኑ ቀብርን ማሸብረቅ ከሚከለክሉ መረጃዎች ጋር የሚጣረስ ሲሆን የጃሂሎች ተግባር መሆኑንም ያሳያል። በተለይም በቀብሩ አናት ላይ የሚታየውን ጥምጣም ስንመለከት ለቱሪስት መስህብ በጥንቃቄ ተጠምጥሞ የተሰናዳ ይመስላል። የመልእክተኛው ባልደረቦችም ይሁን ከነሱ ቢኃላ እስካለንበት ዘመን መዲናን ያስተዳደሩ መሪዎች ሁሉ የመልእክተኛውን ቀብር በሙዚየም መልክ አሳምረው ለጉብኚዎች ክፍት አድርገውት አያውቁም። ሰላምታን የሚያቀርቡትም ከግድግዳው ባሻገር ነው።በእነዚህ ምክኒያቶች ይህ ፎቶ የመልእክተኛውን ቀብር እንደማይወክል፤ ቀብር አምላኪዎች የሸይኾቻቸውን ቀብር የሚገነቡበት እና የሚያሸበርቁበት አካሄድ የመልእክተኛው ቀብርን አርአያ አድርገው ለማቅረብ ያሰራጩት መሆኑ አያጠራጥርም!!

[2] ይህ ፎቶ የማን ነው? ለሚለው ጥያቄ፡-

በዚህ ፎቶ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ሁሉ እንደሚስማሙት ይህ ቀብር በቱርክ አልመውለዊያህ በመባል የሚታወቀውን የሱፊያ ጦሪቃ የመሰረተው ገጣሚ ጀላሉዲን አሩሚይ ቀብር ነው።

ጀላሉዲን አሩሚይ (እ.ኤ.አ 1207-1272) ከባፋቸው የግጥም መድብሎች እና አጫጭር ፅሁፎች በመነሳት የኢብኑ አረቢን የአላህ መለኮታዊ ሀይል ሁሉም ነገር ውስጥ እንደሚሰርፅ የሚሰብከው የ"ሁሉል ወል ኢቲሀድ" አስተሳሰብ አቀንቃኝ እንደሆነ ግልፅ ነው። (ዲራሳት ፊተሰውፍ) ሷሊህ አረቂብ ገፅ 195 ይመልከቱ

ጀላሉዲን አሩሚ የመውለዊ ጦሪቃ ተከታዮች የታወቁበትን ለረጅም ሰአታት ክብ ሰርቶ በዝግታ መደነስን ያዘለ 'መንፈሳዊ' የሙዚቃ ስርአት የቀረፀ ሲሆን፤ በእነሱ አስተሳሰብ ሸይኻቸውን መሀል አድርገው ክብ እየሰሩ በለስላሳ ሙዚቃ ታጅበው መደነሳቸው ከአለማዊነት አውጥቶ መንፈሳቸውን የሚያጠራ በረከትንም የሚያወርድ ተግባር ነው።

እነዚህ ሰዎችና ሸይኻቸው የሚዝዙበት የተሰውፍ አካሄድ ባጢል መሆኑን የሚያሳይ እውነታ ነው።

አላህ የመካ የሙሽሪኮችን አምልኮ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፤

وَمَا كَانَ صَلَاتُهُمْ عِندَ الْبَيْتِ إِلَّا مُكَاءً وَتَصْدِيَةً﴾ [الأنفال : 35]

«በቤቱ (በካዕባ) ዘንድም ስግደታቸው ማፏጨትና ማጨብጨብ እንጂ ሌላ አልነበረም!» አል አንፋል 35

የዚህ ፅሁፍ አላማ ስለ ጀላሉዲን እና ስለጦሪቃው መውለዊያህ ማሳወቅ ስላልሆነ የአላህ ፍቃድ ከሆነ በሌላ ፅሁፍ የምለው ይኖረኛል።

∴ ሳጠቃልለው፤ ለዘብተኝነትን የማስፋፋት እቅድ አካል አድርገው በመሳልና ከፍተኛ በጀት በመመደብ የቀብር አምልኮን በማስፋፋት ላይ ያሉ አንዳንድ አካላት ድጋፋቸውን አጠናክረዋል። ተውሂድ ተፈጥሯዊ እምነት በመሆኑ ይህ ፍላጎታቸው እቅድ ከመሆን አያልፍም!

إِنَّ الَّذِينَ كَفَرُوا يُنفِقُونَ أَمْوَالَهُمْ لِيَصُدُّوا عَن سَبِيلِ اللَّهِ ۚ فَسَيُنفِقُونَهَا ثُمَّ تَكُونُ عَلَيْهِمْ حَسْرَةً ثُمَّ يُغْلَبُونَ ۗ وَالَّذِينَ كَفَرُوا إِلَىٰ جَهَنَّمَ يُحْشَرُونَ﴾ [الأنفال : 36]

«እነዚያ የካዱት ከአላህ መንገድ ሊከለክሉ ገንዘቦቻቸውን ያወጣሉ፤ በእርግጥም ያወጡዋታል፤ ከዚያም በነሱ ላይ ጸጸት ትሆንባቸዋለች፤ ከዚያም ይሸነፋሉ፤ እነዚያም የካዱት ወደ ገሃነም ይሰበሰባሉ» አል አንፋል 36

የሚያሳዝነው ግን... ከአላህ ውጪ ወደ ሙታን እጅ መዘርጋት፣ ስለት መሳል እና የቀብር አምልኮን ሁሉ ሸሪዓ አስመስሎ በማቅረብ የዚህ ተልእኮ አስፈፃሚዎች የሆኑት አንዳንድ ኢስላምን ከምንጩ ያልተረዱ የዋሆች መሆናቸው ነው።

የዱንያ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሽርክን ለማንገስ ለሚንቀሰቀሱት ለእነኚህ አካላት ጆሮ የሚያውሱ አላዋቂዎች በጥሩ ዘይ የማስተማር፣ የማንቃትና የሚዘውሯቸውን አካላት ሴራም ማጋለጥ እጅግ ተገቢ ነው።

የሽርክ እና የቢድዓ አራማጆች በከሀዲያን ቢመኩም በሀያሉ አላህ በመመካት ትክክለኛውን ተውሂድ በሰዎች ልቦና ውስጥ ለማስረፅ መጣር የጋራ ሀላፊነታችን ነው።

ላለመደናገር ንቃትን እናዳብር!!

እርዝ

ሀ. ትርጉሙ፦እርዝ ከክፋት ይጠብቅ ዘንድ ታሽጎ አንገት ላይ የሚንጠለጠል ፅሁፍ፣ ክሮች፣ አጥንቶች የመሳሰሉ ነገሮች ሲሆን ድሮ ዓረቦች በተሳሳተ አመለካከታቸው ልጆችን ከሰው አይን ለመከላከል የሚያንጠለጥሉላቸው ጥቅምን ለማግኘት ወይም ጉዳትን ለመከላከል በማሰብ የሚደረግ ነው።

ለ. ሸሪዓዊ ብይኑ፦ሀራም (የተከለከለ) ከመሆኑም በላይ ከሽርክ አይነቶች አንዱ ነው። ምክንያቱ ከአላህ ውጭ በሆነ ነገር መንጠልጠል ነው። ክፉን መካች አላህ ብቻ በመሆኑ ማንኛውም ሰው ጎጂን ነገር መከላከል ያለበት በአላህ በስሞቹና በባህሪያቱ ብቻ ነው።ኢብኑ መስዑድ እንዳሉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለው ‹‹ሩቃ፣ እርዝና መስተፋቅር መስራት ሽርክ ነው"

አብደላህ ኢብኑ ዑከይም እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል

"በአንድ ነገር ላይ የተንጠለጠለ ወደ ለርሱ ይተዋል"

ዑቅበት ኢብን ዓሚር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል "እርዝን ያንጠለጠለ አላህ አይሙላለት፣ ዛጎልንም ያንጠለጠለ አላህ አይተውለት"

ዑቅበት ኢብን ዓሚር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል "እርዝን ያንጠለጠለ ሽርክን ፈፅሟል" እነዚህና መሰል ጥቅሶች ዓረቦች በብዛት ሲያንጠለጥሉት የነበሩትን ሽርካዊ እርዞች የሚከለክሉ ሲሆኑ የተከለከሉትም ከአላህ ውጭ በሆነ ፍጡር ላይ መንጠልጠል በመሆኑ ነው።

ሐ. የሚንጠላጠለው ፅሑፍ የቁርአን ቃል ከሆነ፦ዑለማዎች በዚህ ዙሪያ አልተስማሙም ከፊሉ የሚፈቅድ ሲሆን ሌላው ደግሞ ይከለክላል። ቁርአንን ለፈውስ ማንጠልጠል አይቻልም የሚሉ አቋሚቸው ከአራት ምክንያቶች አንፃር ሲታይ ትክክል ነው።

1. ነብዩ ﷺ እርዝን የከለከሉት በጥቅሉ ሲሆን ይህን አይነቱን ነጥሎ የሚያወጣ ማስረጃ አለመኖሩ።

2. ይህን መፍቀድ ከቁርአን ያልሆነን ፅሁፍ ለማንጠልጠል መንገድ ስለሚከፍትና ወደ መጥፎ የሚመራን መንገድ መዝጋት ደግሞ ተፈላጊ ስለሆነ::

3. አንጠልጣዩ በመፀዳጃ፣ በኢስቲንጃና በመሳሰሉት ቦታ ይዞት ስለሚገኝ ቁርአንን ዝቅ የሚያደርግ በመሆኑ።

4. በቁርአን መፈወስ በምን መልኩ መሆን እንዳለበት ስለተገለፀ (እሱም ህመምተኛው ላይ መቅራት ነው) እና ይህን መተላለፍ ስለማይቻል።

እምነትሽን ጠብቂ!

የቂያማ ምልክቶችና አይነቶች

የቂያማ ምልክቶች

የቂያማ ምልክቶች ሲባል ቂያማ ከመምጣቱ በፊት መቃረቡን የሚጠቁሙ ክስተቶች ማለት ነው። አላህ እንዲህ ይላል

{ فَهَلْ يَنْظُرُونَ إِلَّا السَّاعَةَ أَنْ تَأْتِيَهُمْ بَغْتَةً فَقَدْ جَاءَ أَشْرَاطُهَا } (مُحَمَّد : 18)

<<ሰዓቲቱንም ድንገት የምትመጣባቸው መኾንዋን እንጅ ይጠባበቃሉን? ምልክቶችዋም በእርግጥ መጥተዋል።>> ሙሐመድ 18

የቂያማ ምልክት አይነቶች

የቂያማ ምልክቶች በሶስት ይከፈላሉ

አንደኛው፡- ራቅ ያሉ ምልክቶችና ተፈፅመው ያበቁ ናቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ ከሚካተቱ ምልክቶች አንዱ የነብዩ ﷺመላክ ነው። አነስ ኢብን ማሊክ በአስተላለፉት ሀዲስ ነብዩ ﷺ የመሀልና የአመልካች ጣታቸውን በማያያዝ እኔና ቂያማ እንዲህ ተቀራርበን መጣን።" ብለዋል

ከዚህ ክፍል ውስጥ የጨረቃ መሰንጠቅ ይጠቀሳል። አላህ እንዲህ ይላል

{ اقْتَرَبَتِ السَّاعَةُ وَانْشَقَّ الْقَمَرُ } (القمر : 1)

<<ሰዓቲቱ (የትንሣኤ ቀን) ተቃረበች፤ ጨረቃም ተገመሰ።>> አል ቀመር 1

ሂጃዝ ውስጥ የተቀሰቀሰ እሳት ነበልባል ቡስራ ድረስ መታየቱ። ቡኻሪና ሙስሊም ከአቡ ሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስ ነብዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

« لا تقوم الساعة حتى تخرج نار من أرض الحجاز تضيء أعناق الإبل ببصرى »

"ቂያማ ከመቆሙ በፊት ሂጃዝ ላይ እሳት ተነስቶ ቡስራ ያሉ ግመሎች አንገት ላይ የነበልባሉ ነፀብራቅ ይታያል።" (ቡኻሪ 7118 ሙስሊም 2902)

ነብዩ ﷺባሉት መሰረት ይህ እሳት በጁማደል አኺር ወር በስድስት መቶ ሃምሳ አራተኛ የሒጅራ አመት በመዲና በስተምስራቅ አካባቢ ተነስቶ ከፍተኛ ንዳድ የተፈጠረ ሲሆን የሻም ህዝቦች የእሳቱን ብርሃን እንደተመለከተ እንዲሁም የቡስራ ህዝብ በእሳቱ ብርሃን የግመሎችን አንገት እንዳዩ ታሪክ ዘግቧል።

ሁለተኛው፡- መካከለኛ የቂያማ ምልክቶች ሲሆን የተከሰተ ወደፊት የሚከተቱ ምልክቶች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ፡-

የሴት ባሪያ ጌታዋን መውለድና የታረዙ ድሆች በፈጣን ጊዜ ውስጥ ለግንባታ መፎካከር። ሙስሊም በዘገቡት የጅብሪል ሀዲስ እንደተዘገው

« قال فأخبرني عن الساعة ؟ قال : ما المسئول عنها بأعلم من السائل . قال : فأخبرني عن أماراتها ، قال : أن تلد الأمة ربتها ، وأن ترى الحفاة العراة العالة رعاء الشاء يتطاولون في البنيان »صحيح مسلم برقم (8)

"ጅብሪል ለነብዩ ﷺቂያማ አለት መቸ እንደሚሆን ንገርኝ ሲላቸው ተጠያቂ ከጠያቂ ይበልጥ ስለዚህ አያውቅም አሉት በማስከተል እንግዲያውስ ስለ ምልክቶቿ ንገሩኝ ሲላቸው እንዲህ ሲሉ ነገሩት ሴት ባሪያ ጌታዋን መውለድ፣ ጫማ ያልነበረው የታረዘ ድሃ እረኛ የነበሩ ለግንባታ መሽቀዳደም።" (ሙስሊም 8)

ነቢይ ነኝ የሚሉ ሰላሳ ውሸታሞች መምጣት።

አቡሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስ ነብዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

« لا تقوم الساعة حتى يبعث دجالون كذابون قريبا من ثلاثين كلهم يزعم أنه رسول الله » رواه البخاري برقم (3609)

"ቂያማ ከመከሰቱ በፊት ወደሰላሳ የሚሆኑ ውሸታሞች ነቢይ ነኝ በማለት ብቅ ይላሉ።" (ቡኻሪ 3609)

ሶስተኛው፡- ታላላቅ ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች መከሰታቸውን ተከትሎ ቂያማ ይቆማል

እነዚህ ምልክቶች አስር ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ አንዱም አልተከሰተም። ኢማም ሙስሊም ከሁዘይፋ ኢብን አሰየድ እንዳስተላለፉት

« اطلع النبي ﷺ علينا ونحن نتذاكر ، فقال : ما تذاكرون ؟ قالوا : نذكر الساعة . قال : إنها لن تقوم حتى تروا قبلها عشر آيات : فذكر الدخان والدجال ، والدابة ، وطلوع الشمس من مغربها ، ونزول عيسى ابن مريم ﷺ ، ويأجوج ومأجوج ، وثلاثة خسوف : خسف بالمشرق وخسف بالمغرب وخسف بجزيرة العرب ، وآخر ذلك نار تخرج من اليمن تطرد الناس إلى محشرهم »صحيح مسلم

"በሆነ አለት አብረን እየተዋወስን ሳለን ነቢዩ ﷺወደኛ ብቅ አለሉና "ምንድ ነው ምትመካከሩት?" አሉን እኛም "ቂያማን እየተዋወስን ነው" ብለን መለስን እሳቸውም እንዲህ አሉ "አስር ተአምሮች ሳይከሰቱ ቂያማ አይቆምም ከዚያ አስሩን ሲዘረዝሩ ጭስ፣ ደጃል፣ እንስሳ፣ የፀሐይ ከምዕራብ መውጣት፣ የኢሳን መውረድ፣ የእጁጅና መእጁጅ ፣ ሶስት የመሬት መስመጦች በምስራቅ በኩል የሚከሰት መስመጥ በምዕራብ በኩል የሚከሰት መስመጥና የአረብ ደሴት በኩል የሚከሰት መስመጥን ጠቅሰው የመጨረሻው ከየመን ተቁስቁሶ ሰዎችን ወደ መሰብሰቢያቸው የምትሰድ እሳት እንደምትቀሰቀስ ተናገሩ።" (ሙስሊም 2901)

በሌሎች ሀዲሶች የመህዲ መምጣት የከዕባ መፍረስና የቁርአን ከምድር መነሳት ተነግሯል። አብዛኞች ዑለማዎች እንደሚሉት ከሆነ አስሩ የቂያማ ምልክቶች ከላይ የተጠቀሱ ሶስቱ ምልክቶችና የሁዘይፋ ኢብን አሰየድ ሀዲስ ላይ ከተጠቀሱት ከመሬት መስመጥ ውጭ ያሉ ምልክቶች ናቸው። የመሬት መስመጥ ሀዲሱ ላይ እንደተባለ ከቂያማ ምልክቶች አንዱ ቢሆንም ከአስሩ ምልክቶች ቀደም ብሎ የሚከሰት ምልክት ነው።



እምነትሽን ጠብቂ!

ታላላቅ የቂያም ምልክቶች

የቂያማ እነዚህ አስር ምልክቶችን እንደሚከተለው በዝርዝር ከኦማስረጃዎቻቸው ይቀርባሉ።

አንደኛ ምልክት፡- የመህዲ መምጣት

መህዲ ከነቢዩ ﷺ ቤተሰቦች የሐሰን ኢብን አሊ ዘር የሚወለድ ስሙና የአባቱ ስም የነቢያችንና የአባታቸውን ስም ተመሳሳይ የሆነ ምድር በአድልዎና በበደል ከሞላች በኃላ በፍትህና እኩልነት ሊለውጥ የሚመጣ ሰው ነው።

አቡዳውድ ቲርሚዚይ ከአብደላ ኢብን መስዑድ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺእንዲህ ይላሉ

« لا تذهب الدنيا حتى يملك العرب رجل من أهل بيتي يواطئ اسمه اسمي واسم أبيه اسم أبي ، يملأ الأرض عدلا وقسطا كما ملئت جورا وظلما »

"አንድ ሰሙ ከሰሜ ጋር የአባቱ ስም ከአባቴ ስም ጋር የሚስማማ ሰው ዓረብን ገዝቶ ምድር በአድልዎና በበደል ከተሞላች በኃላ በፍትህና በእኩልነት ሳይሞላት ይህች አለም አትወገድም" (አቡዳውድ 4282 ቲርሚዚይ 2230)

ሁለተኛው ምልክት፡- የመሲህ ደጃል መምጣት

መሲህ ደጃል በዘመን መጨረሻ አካባቢ ብቅ የሚል ሰው ሲሆን የተለያዩ ከተለምዶ ወጣ ያሉ ነገሮችን እንዲሰራ አላህ ያስቻለው ፈታኝ ነው። እኔ ጌታ ነኝ የሚል ጥሪ በማድረግ ያመነበትን ጀነት መሳይ እውነታው ግን ጀሃነም በሱ የካደን ጀሃነም የሚመስል ውስጡ ግን ጀነት ያስገባል።

ሙስሊም ከአብደላህ ኢብን ዓምር ኢብኑል ዓስ በአስተላለፈው ሀዲስ ነብዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

« يخرج الدجال في أمتي فيمكث أربعين لا أدري أربعين يوما أو أربعين شهرا أو أربعين عاما فيبعث الله عيسى ابن مريم كأنه عروة بن مسعود فيطلبه فيهلكه »

"ደጃል በህዝቦቼ መሀል ይነሳና አርባ ይቆያል (አርባ አመት ይበሉ አርባ ወራት ይበሉ አርባ ቀናት ይበሉ አላስታውሰም) የመርየም ልጅ ኢሳ ይወርድና አሳዶ ይገለዋል።" (ሙስሊም 2940 አህመድ 2/166)

ቡኻሪና ሙስሊም ከአብደላህ ኢብን ዑመር እንዳስተላለፉት በአንድ ወቅት ነቢዩ ﷺቆመው አላህን በሚገባ ካወደሱ በኃላ ስለደጃል እንዲህ ብለው ተናገሩ

"ሁሉም ነቢይ እሱን እንዳስጠነቀቀው እኔም አስጠንቅቃለሁ ኑህም ህዝቦቹን ከሱ አስጠንቅቋል። እኔ ግን የትኛውም ነቢይ ያልተናገረውን ልንገራችሁና እሱ አንድ አይን ሰውር ነው። ጌታችሁ ግን አንድ አይን ሰውር አይደለም።" (ቡኻሪ 2892 ሙስሊም 2931)

ሶስተኛው ምልክት፡- የኢሳ ከሰማይ በመውረድ በፍትህ መፍረድና ጀጃልን ማጥፋት

አላህ እንዲህ ይላል

{ وَإِنَّهُ لَعِلْمٌ لِلسَّاعَةِ } (الزخرف : 61)

<<እርሱም (ዒሳ) ለሰዓቲቱ (ማወቂያ) በእርግጥ ምልክት ነው።>> ዙኽሩፍ 61

ይህን አንቀጽ አብዛኞች የቁርአን አብራሪ ዑለማዎች በኢሳ መምጣት ተርጉመዋል። ኢማም አህመድም እንደዘገቡት ኢብኑ አባስ በዚህ አንቀጽ ዙሪያ እንዲህ ብለዋል "ይህ አንቀጽ ከቂያማ በፊት ስለኢሳ መውረድ የሚጠቁም ነው።" (አህመድ 1/318)

ኢሳ እንደሚወርድ የሚገልፁ ሀዲሶች ከነቢዩም ﷺተዘግቧል። አቡ ሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢይ ﷺእንዲህ ብለዋል

« والذي نفسي بيده ليوشكن أن ينزل فيكم ابن مريم حكما عدلا فيكسر الصليب ويقتل الخنزير ، ويضع الجزية ويفيض المال حتى لا يقبله أحد ، حتى تكون السجدة الواحدة خيرا من الدنيا وما فيها »

"ነፍሴ በእጇ ባለው ጌታ እምላለሁ ኢሳ በእናንተ መካከል ፍትሃዊ ፈራጅ ለመሆን መስቀልን ለመስበር፣ አሳማን ለመግደልና ግብር ለማስቀረት ይመጣል፣ ገንዘብ በጣም በዝቶ ተቀባይ ይጠፋል አንድ ሱጁድ ማድረግ ዱንያን ሁሉ ከማግኘት የተሻለ ብልጫ ይሰጠዋል።"

(ቡኻሪ 3264 ሙስሊም 155)

አራተኛው ምልክት፡- የየእጇድና መእጇጅ መምጣት

ከኑህ ልጆች ውስጥ የያፊስ ዘሮች እንደሆኑ የሚነገርላቸው ማንም ሊዋጋቸው የማይችሉ አጥፊ ቡድኖች ናቸዉ። አላህ እንዲህ ይላል

{ حَتَّى إِذَا فُتِحَتْ يَأْجُوجُ وَمَأْجُوجُ وَهُمْ مِنْ كُلِّ حَدَبٍ يَنْسِلُونَ } { وَاقْتَرَبَ الْوَعْدُ الْحَقُّ فَإِذَا هِيَ شَاخِصَةٌ أَبْصَارُ الَّذِينَ كَفَرُوا } (الأنبياء : 96 ، 97)

<<የእጇድና መእጇጅም እነርሱ ከየተረተሩ የሚንደረደሩ ሲኾኑ (ግድባቸው) በተከፈተች ጊዜ እውነተኛውም ቀጠሮ በቀረበ ጊዜ፣ ያን ጊዜ እነሆ የእነዚያ የካዱት ሰዎች ዓይኖች ይፈጥጣሉ።>> አል አንቢያ 96-97

ቡኻሪና ሙስሊም ከዘይነብ ቢንት ጀህሽ እንዳስተላለፉት በአንድ ወቅት የአላህ መልዕክተኛ ﷺወደ ቤት ገብተው እንዲህ አሉ

« لا إله إلا الله ويل للعرب من شر قد اقترب فتح من ردم يأجوج ومأجوج مثل هذه " وحلق بأصبعه الإبهام والتي تليها »

"ዓረብ ጉድ ፈላበት ክፋት ቀረበ ከየእጇጅ ማእጇጅ ግድብ የዚህን ያህል ክፍተት ተከፈተ በማለት በአውራ ጣታቸውና በአመልካች ጣት የክብ ቅርፅ አሳዩ።"

(ቡኻሪ 3346 ሙስሊም 2880)



እምነትሽን ጠብቂ!

አምስተኛው ምልክት፡- በሀበሻ ሰው ከዕባ መፍረስ

ቡኻሪና ሙስሊም ከአቡ ሑረይራ እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል

« يخرب الكعبة ذو السويقتين من الحبشة »

"እጆቹ ቀጫጭ የሆኑ የሀበሻ ሰው ካዕባን ያፈርሳል።" (ቡኻሪ 1591 ሙስሊም 2909)

ኢማም አህመድ ከአብደላህ ኡብን ዓምር እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል

« يخرب الكعبة ذو السويقتين من الحبشة ، ويسلبها حليها ويجردها من كسوتها ، ولكأني أنظر إليه أصيلع أفيدع يضرب عليها بمسحاته ومعوله »

"እግሮቹ ቀጫጭን አዋንቱ የዞረ መላጣ ሀበሻ በመቆፈሪያው እየመታ ካዕባን ያፈርሳል ከልብሷና ከጌጣጌጦቿም ያራቁታታል።" (ሙስነድ 2/220)

ስድስተኛ ምልክት፡- የጪስ መቀስቀስ

አላህ እንዲህ ይላል

{ فَارْتَقِبْ يَوْمَ تَأْتِي السَّمَاءُ بِدُخَانٍ مُبِينٍ }{ يَغْشَى النَّاسَ هَذَا عَذَابٌ أَلِيمٌ } (الدخان : 10 ، 11)

<<ሰማይም በግልጽ ጭስ የምትመጣበትን ቀን ተጠባበቅ። ሰዎችን የሚሸፍን (በኸነ ጭስ) ይህ አሳማሚ ቅጣት ነው።>> ዱኻን 10-11

ሁዘይፋ በአስተላለፉትም ሀዲስ ነቢዩ ﷺ "አስር ነገሮችን ሳታዩ ቂያማ አይቆምም በማለት ከአስሮቹ ጭስን ጠቅሰዋል።"

(ሙስሊም 2901)

ሰባተኛው ምልክት፡- የቁርአን ወደ ሰማይ መውጣት

ሁዘይፋ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ይላሉ

« يدرس الإسلام كما يدرس وشي الثوب حتى لا يدرى ما صيام ولا صلاة ولا نسك ، وليسرى على كتاب الله عز وجل في ليلة فلا يبقى في الأرض منه آية »

"ከጊዜ ርዝመት የልብስ ጌጥ እንደሚጠፋው ኢስላም ይጠፋና ሰላት፣ ፆም፣ ሐጅ ምን እንደሆኑ አይታወቅም፤ በአንድ ሌሊት ምድር ላይ አንድ አንቀጽ ሳይቀር ይነሳል።"

(ኢብን ማጃህ 4049 ሙስተድረክ 4/473)

ስምንተኛው ምልክት፡- ፀሐይ ከምዕራብ መውጣት

አላህ እንዲህ ይላል

{ يَوْمَ يَأْتِي بَعْضُ آيَاتِ رَبِّكَ لَا يَنْفَعُ نَفْسًا إِيمَانُهَا لَمْ تَكُنْ آمَنَتْ مِنْ قَبْلُ أَوْ كَسَبَتْ فِي إِيمَانِهَا خَيْرًا } (الأنعام : 158)

<<ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ በሚመጣ ቀን ከዚህ በፊት አማኝ ያልኾነችን ነፍስ እምነትዋ ወይም በእምነትዋ (ጊዜ) በጎ ያልሠራችን (ነፍስ ጸጸትዋ) አይጠቅማትም።>> አል አንዓም 158

ይህን አንቀጽ ሲተነትኑ "ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ" የሚለውን ነቢዩ ﷺ የፀሐይ ከምዕራብ መውጣት ነው ማለታቸውን ኢብን ጀሪር አጠበሪይ ተናግረዋል። (ተፍሲር ኢብን ጀሪር 8/97)

ቡኻሪና ሙስሊም ከአቡ ሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል

« لا تقوم الساعة حتى تطلع الشمس من مغربها فإذا طلعت فرآها الناس آمنوا أجمعون فذاك حين لا ينفع نفسًا إيمانها لم تكن آمنت من قبل أو كسبت في إيمانها خيرًا »

"ፀሐይ ከምዕራብ ሳትወጣ ቂያማ አይከሰትም፣ ፀሐይ ከምዕራብ ስትወጣ ሲያይ ህዝቡ ሁሉ ያምናል ነገር ግን ከዛ በፊት አምና መልካምን ያልሰራች ነፍስ ያኔ ማመኗ አይጠቅማትም።" (ቡኻሪ 4636 ሙስሊም 157)

ዘጠነኛ ምልክት፡- የእንስሳ መውጣት

ስልሳ ክንድ የምትረዝም ረዣዥም እግሮችና ፀጉር ያላት የተለያዩ እንስሳዎች መልክ የያዘች እንስሳ ከቂያማ በፊት እንደምትመጣ ነቢዩ ﷺ ተናግረዋል። አላህ እንዲህ ብሏል

{ وَإِذَا وَقَعَ الْقَوْلُ عَلَيْهِمْ أَخْرَجْنَا لَهُمْ دَابَّةً مِنَ الْأَرْضِ تُكَلِّمُهُمْ أَنَّ النَّاسَ كَانُوا بِآيَاتِنَا لَا يُوقِنُونَ } (النمل : 82)

<<በእነርሱም ላይ (የቅጣት) ቃሉ በተረጋገጠ ጊዜ ሰዎቹ በአንቀጾቻችን የማያረጋግጡ እንደነበሩ የምትነግራቸውን እንስሳ ለእነርሱ ከምድር እናወጣለን።>> ነምል 82

ኢማም ሙስሊም ከአቡ ሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል

(ثلاث إذا خرجن لا ينفع نفسًا إيمانها لم تكن آمنت من قبل أو كسبت في إيمانها خيرًا ، طلوع الشمس من مغربها والدجال ودابة الأرض)

"አንዲት ነፍስ አስቀድማ ካላኘችና መልካም ካልሰራች ሶስት ነገሮች ከመጡ በኃላ ብታምን እምነቷ አይጠቅማትም ፀሐይ ከመግቢያዋ መውጣት፣ የደጃል መምጣትና የእንስሳ መውጣት።" (ሙስሊም 158)

ኢማም አህመድ ከአቡ ኢማማ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ይላሉ

« تخرج الدابة فتسم الناس على خراطيمهم ثم يغمرون فيكم حتى يشتري الرجل البعير فيقول ممن اشتريته فيقول : من أحد المخطمين »

"አንዲት እንስሳ ብቅ ትልና ሰዎች አፍንጫ ላይ ምልክት ታደርጋለች።" (ሙስነድ 5/268)

አስረኛው ምልክት፡- የእሳት መቀስቀስ

ከፍተኛ ንዳድ ያላት እሳት ከዔድን ተነስታ ሰዎችን ወደ መሰብሰቢያ ቦታቸው ትሰዳለች። ከላይ በተጠቀሰው ሀዘይፋ በአስተላለፈው ሀዲስ ነቢዩ ﷺ የመጨረሻው ምልክት ከየመን ከፍተኛ እሳት ይቀሰቀስና ሰዎችን ወደ መሰብሰቢያቸው ትሰዳለች።" ብለዋል (ሙስሊም 2901)

እነዚህ ታላላቅ ምልክቶች በተከታታይ የሚከሰቱ ሲሆን ካለቁ በኃላ በአላህ ፈቃድ ቂያማ ይቆማል። አቡሑረይራ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺ

« خروج الآيات بعضها على إثر بعض ، يتتابعن كما تتابع الخرز في النظام »

"የቂያማ ምልክቶች ጨሌ ገመድ ላይ እንደሚከታተለው አንዱ ከሌላው ጋር ተከታትለው ይከሰታሉ።" ብለዋል (ሙዕጀሙል አውሰጥ 4283)



እምነትሽን ጠብቂ!

የኢስላማዊው አቂዳ አላማዎች

የኢስላማዊ እምነት አላማዎች ኢስላማዊውን አቂዳ አጥብቆ በመያዝ የሚገኙት ውድ የሆኑ ግቦች ብዙና የተለያዩ ሲሆኑ ከነሱም መሐከል

አንደኛ፡- ኒያንና (ፍላጐትን) አምልኮትን ለአላህ ማጥራት። አላህ ብቸኛ ምንም ተጋሪ የሌለው ፈጣሪ እንደመኑ ፍላጐትና አምልኮትም ለሱ የጠሩ መሆን ይገባቸዋል።

ሁለተኛ፡- ይህንን እምነት በማጣት ከሚከሰት የአእምሮና የአስተሳሰብ ሀብት መጠበቅ። ልቡ በኢስላማዊው አቂዳ ዉጪ የሆነ ሰው ወይም ምንም አይነት እምነት የሌላው ቁስ አምላኪ ይሆናል አልያም የተሳሳተ እምነት ውስጥና አፈተረት ውስጥ ይዘፈቃል።

ሶስተኛ፡- በዚህ እምነት የፀና ሰው የነፍስና የአመለካከት መረጋጋትን ያገኛል የነፍስ ጭንቀትም ይሁን የአመለካከት መዛባት አያጋጥሙትም ይህቺ እምነት አማኙ ከፈጣሪው ጋር ታገናኝዋለች ስለሆነም የፈጣሪውን አስተናባሪ ጌትነቱ፣ ደንጋጊ ፈራጅነቱን ይወዳል፣ በውሳኔውም ልቡ ይረጋጋል ለኢስላምም ልቡ ክፍት ይሆናል ተለዋጭም አይፈለግለትም።

አራተኛ፡- በአላህ አምልኮ ላይም ይሁን ከፍጡራን ጋር በመኗኗር ላይ ፍላጐትና ተግባርን ከመዘንበል ማዳን። ከመሰረቶቹ መሐከል አንዱ ሰላማዊ የነውን መንገዳቸውን ከመከተል ጋር በመልዕክተኞች ማመን ነውና።

አምስተኛ፡- በነገሮች ላይ በአጠቃላይ ቆራጠኛና ትጉህ መሆን፣ የአላህን ምንዳ በመከጀል የመልካም ስራን አጋጣሚ በሚያሳልፍበትና የአላህን ቅጣት በመፍራት የወንጀልን መውደቂያዎች ሁሉ በሚርቅበት ደረጃ ከእማን መሰረቶች አንዱ ከሞት በኃላ መቀስቀስ በሰሩት መመንዳት በመኖሩ ማመን ነውና።

﴿ وَلِكُلٍّ دَرَجَاتٌ مِّمَّا عَمِلُواْ وَمَا رَبُّكَ بِغَافِلٍ عَمَّا يَعْمَلُونَ ﴾ [سورة الأنعام : 132]

"ለሁሉም ከሠሩት ሥራ (የተበላለጡ) ደረጃዎች አልሏቸው። ጌታህም ከሚሠሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም።" አል አንዓም 132

ወደዚህ ግብም ነብዩ ﷺ በተከታዩ ንግግራቸው አነሳስተዋል

(المؤمن القوي خيرٌ ، وأحب إلى الله من المؤمن الضعيف ، وفي كل خير ، احرص على ما ينفعك ، واستعن بالله ، ولا تعجز ، وإن أصابك شيء فلا تقل : لو أنِّي فعلت كذا كان كذا وكذا ، ولكن قلْ : قدَّر الله وما شاء فعل ؛ فإن (لو) تفتح عمل الشيطان)

"ጠንካራው አማኝ ከደካማው የበለጠ አላህ ዘንደ በላጭና ተወዳጅ ነው። ሁለቱም መልካም ነገር አላቸው የሚጠቅምህ ነገር ላይ ትጉ ሆነህ በአላህ ጋዝ አትዳከም የማትወደው ነገር ቢደርስብህ እንዲህ ባረግ እኮ እንዲህ እንዲህ ይሆን ነበር አትበል ነገር ግን አላህ ወሰነ የፈለገውንም ፈፀመ በል ቢሆን ኖሮ የሸይጣንን በር ትከፍታለች።"

ስድስተኛ፡- ውዱንም ይሁን እርካሹን ንብረቱን ሃይማኖቱን መሰረቶቹንም ለማጠንከር ለማፅናት የሚሰዋ በዚህ መንገድ ለሚደርስበት ችግርም የሚታረስ ጠንካራ ማህበረሰብ መመስረት ለዚህም አላህ እንዲህ ይላል

﴿ إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا وَجَاهَدُوا بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أُوْلَئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ ﴾[سورة الحجرات : 15]

"እውነተኛዎቹ) ምእምናን እነዚያ በአላህና በመልእክተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው። እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው።" ሁጁራት 15

ሰባተኛ፡- ግለሰቦችንም ይሁን ማህበረሰቡን ለማስተካከል፣ ለምንዳና ለቀብር ለቅርቢቱ አለምም ይሁን ለወዳኛው አለም እድለኝነት ማብቃት። ይህንን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል

﴿ مَنْ عَمِلَ صَالِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴾ [سورة النحل : 97]

"ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ሁሮን በእርግጥ እናኖረዋለን። ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።" አል ነህል 97

እነዚህ ከፊል የእስልምናው እምነት አላማዎች ሲሆኑ ሁሉንም አላማዎች ለእኛም ለሙስሊሞችም በአጠቃላይ አላህ እንዲያረጋግጣቸው እንከጅላለን።

ሸፋዓ (ምልጃ)

እና ክፍሎቹ

ነብዩም ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ሆኑ ማንኛውም ደግ ሰው አላህ ዘንድ አማላጅ እንዲሆንልን የሚጠየቀው አላህን ብቻ ነው። ለምሳሌ ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም የቂያማ እለት ሸፋዓ (አማላጅ) እንዲሆኑን ስንፈልግ "ጌታዬ ሆይ! የቂያማ እለት ነብዩን ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም አማላጅ አድርግልኝ" ብሎ መለመን የተፈቀደ ነው። ነገር ግን ነብዩንም ሆነ ሌላን ሠው እባክህን ነገ አማላጅ ሁነኝ ብሎ መለመን የማይፈቀድ ሸርክ ነው። ምክንያቱም ይህን ማድረግ የሚችለው አላህ ብቻ ስለሆነና ከአላህ ሌላ ማንም ሊፈፅመው የማይችለውን ነገር ፍጡርን መለመን ሸርክ ስለሆነ ነው።

ሸፋዓ በሁለት ይከፈላል፡-
1. የተረጋገጠ ሸፋዓ እና
2. የተወገደ ሸፋዓ ናቸው።

1. የተረጋገጠ ሸፋዓ

የተረጋገጠ ሸፋዓ፡- ከአላህ ብቻ የሚለመን ሲሆን ይህም ተገቢ የሚሆነው ተውሂድን ፈፃሚ ለሆነና በአላህ ላይ ለማያጋራ ብቻ ነው።ይህ ምልጃ ተፈፃሚ የሚሆነው አላህ ለአማላጁ ሲፈቅድና አማላጁና ተማላጁንም ሲወድ ብቻ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

مَن ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِندَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ

"እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጂ የሚያማልድ ማነው?" (አል በቀራህ 255)

وَكَم مِّن مَّلَكٍ فِي السَّمَاوَاتِ لَا تُغْنِي شَفَاعَتُهُمْ شَيْئًا إِلَّا مِن بَعْدِ أَن يَأْذَنَ اللَّهُ لِمَن يَشَاءُ وَيَرْضَى

"በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ ቢሆን እንጂ ምልጃቸው ምንም አትጠቅምም" (አን ነጅም 26)

وَلَا تَنفَعُ الشَّفَاعَةُ عِندَهُ إِلَّا لِمَنْ أَذِنَ لَهُ

"ምልጃም እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም" (ሰበእ 23)

وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ارْتَضَى

"ለወደደውም ሰው እንጂ ለሌላ አያማልዱም" (አል አንቢያእ 28)

2. የተወገደ ሸፋዓ

የተወገደው ሸፋዓ፡- አላህ ያስወገደው ያልፈቀደውና ያልወደደው ሲሆን እሱም ከአላህ ውጭ ከሆነ ፍጡር የሚለመን ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

وَأَنذِرْ بِهِ الَّذِينَ يَخَافُونَ أَن يُحْشَرُوا إِلَى رَبِّهِمْ لَيْسَ لَهُم مِّن دُونِهِ وَلِيٌّ وَلَا شَفِيعٌ لَّعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ

እነዚያንም ከእርሱ ሌላ ረዳትና አማላጅ የሌላቸው ሲኾኑ ወደ ጌታቸው መሰሰብሰብን የሚፈሩትን ይጠነቀቁ ዘንድ በርሱ (በቁርኣን) አስፈራራ። (አል-አንዓም 51)

የቁርዓን እና ሀዲስን መረጃ በራሳቸው ፍላጎት ሳይለውጡ የሚከተሉ አማኞች (አህሉ ሱንና ወል ጀመዓ) የቂያማ ዕለት በግንባር ቀደምነት ነብዩ ከዚያ ሌሎች ነቢያት ደጋግ ባሮች እንደሚያማልዱና በነሱም ምልጃ ምክንያት ኃጢአተኛ ሙስሊሞች ጀሐነም እንዳይገቡ ወይም የገቡት እንዲወጡ እንደሚደረግ የሚያምኑ ሲሆን ሙስሊምን በወንጀል ምክንያት የሚያከፍሩ (ኸዋሪጆች) ግን ይህን አይቀበሉም። ነብዩ እንዲህ ይላሉ፡-

"አላህ፦ መልአኮች አማለዱ ነብዮችም አማለዱ የቀረው የአዛኞች አዛኝ ነው ይልና መልካም ሰርተው የማያውቁ ሰዎችን ከእሳት ዘግኖ ያወጣል" : :

ኸዲጀቱ ቢንት ኹወይሊድ

ኸዲጀቱ ቢንት ኹወይሊድ ቀዳማዊ የኢስላም ተቀባይ ፡-

በእርግጥ በኢስላም አንዲት ሴት በአላህ አምና የምትጓዝ ከሆነ ወንዶች የሰሩትን ጀብድ ተቋዳሽ ከመሆን የሚያግዳት አንድም ነገር የለም፡፡

ይኸው እንደምንመለከተው ቁርአን እና ሱና ይህን ድካውን የደረሰ ፍትሃዊ ጉዞዋን አንድ ሁለት እያሉ እያስቃኙን ነው። አላህ ከተጠቃሚዎቹ ያድርገን፡፡

በአረቡ ባህረ ሰላጤ ምድረ በዳ ላይ በነብዩ ﷺ ላይ አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው። የአላህ መልክተኛ ከመላካቸው በፊት ወደ "ጋር ሄራ" የተባለ ዋሻ እየሄዱ ስለ አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) ያስተነትኑ ነበር፡፡ ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ ጀብሪል (ዐለይሂ ሰላም) ከተፍ አለ። ነብዩንም ﷺ ጭምቅ በማድረግ አንብብ አላቸው። እርሳቸውም ማንበብ እንደማይችሉ ነገሩት፡፡ እርሱ ግን ሶስት ግዜ በዚህ መልኩ ካደረጋቸው በኋላ የምእራፍ "አል-ዐለቅን" የመጀመሪያዎቹ አምስት አንቀጾችን አነበበላቸው።

" " اقْرَأْ بِاسْمِ رَبِّكَ الَّذِي خَلَقَ * خَلَقَ الْإِنسَانَ مِنْ عَلَقٍ * اقْرَأْ وَرَبُّكَ الْأَكْرَمُ * الَّذِي عَلَّمَ بِالْقَلَمِ * عَلَّمَ الْإِنسَانَ مَا لَمْ يَعْلَمْ

*"አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም * ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም) * አንብብ ጌታህ በእጅጉ ቸር ነው * ያ በብእር ያስተማረ * ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ነው" (አል ዓለቅ 1-5)*

ነብዩ (ﷺ) በሁኔታው እጅግ በጣም ተደናገጡ። ወደ ውዲቷ ባለቤታቸውም እየገሰገሱ በመምጣት ደርቡልኝ ደርቡልኝ በማለት አረፍ አሉ ።ከአፍታ ቁይታ በውኃላ ገጠመኛቸውን አንድ በአንድ ተረኩላት ።ለህይወታቸውም እንደፈሩ ገለጹላት። ነገር ግን ብሩህን ተስፋ አቀንቃኝ የነበረችው ውዲቷ ባለቤታቸው እንዲህ በማለት አፅናኗቸው ።

"ፍጹም አይዘህ ምንም አይገጥምህም፡፡ በአላህ ይሁንብኝ አላህ አያዋርድህም፡፡ አንት ዝምድናን ቀጣይ፣እንግዳን አክባሪ፣የተቸገረን ደጓሚ፣የታረዘን አልባሽ፣የተራበን አጉራሽ ነህና፡፡"

በዚህም አላቀመችም፡፡ ነብዩን ﷺ ይዛ የአጐቷ ልጅ ወደሆነው ወረቃ ቢን ነውፈል ዘንድ ገሰገሰች፡፡ እርሱም ነሳራ የሆነና ኢንጅልን የሚያውቅ ነበር፡፡ ነገሩን የአላህ መልክተኛ ﷺ አጫወቱት እርሱም፡- "ይህ በሙሳ ላይ የወረደው ነው"፤በማለት ገለፀላቸው። በመቀጠልም እንዲህ አለ። "ህዝቦችህ ከአገርህ በሚያሶጡህ ሰአት ብኖር ኖሮ እረዳህ ነበር"። በዚህ ጊዜ የነብዩ ﷺ ድንጋጤ ጨመረ። እንዲህም አሉት። "እነርሱ እኔን ያስወጡኛል?" ወረቃም ይህን መልስ ሰጣቸው፡- "አዎ አንተ በመጣህበት የመጣ ሁሉ ጠላት ተደርጐ ይያዛል"። ከዚህ በኃላ ነብዩና ኸዲጃ ወረቃን ተሰናብተው ወጡ፡፡ በዚህን ጊዜ ይህች ውድ እንስት የእረፍት ጊዜ እንዳበቃ ተገነዘበች። ከዚህ በኃላ የፈተናዎች አይነት ከሚወርድበት ባል ጋር መተሳሰሯን አረጋገጠች ። እናም እርሷም ልጆችዋም ፈተናውን በሰፊው ተቋዳሽ እንደሚሆኑ አመነችበት፡፡ ለዚህም እራሷን አዘጋጀች። ግን ይህች እንቁ ሴት መጀመሪያ ማን ነበረች??? አዎ! እርሷ ማለት በምኞትና በእንክብካቤ በክብር ያሳለፈች ነበረች። ነገር ግን ይህ ምኞትና ቅንጦት ከባሏ ጐን ተሰልፋ ሽርክን የማርከስ፤ ጣኦትን የመገርሰስ፤ ተውሂድን የማንገስ ትግል ላይ ከመቆም አላቀባትም፡፡ ይልቁንም በጌታዋ አመነች። ነብዩንም ተከተለች። የመጀመሪያዋ ኢስላምን ተቀባይ የሆነች እንስት ለመሆንም በቃች፡፡ በራሷም፣በገንዘቧም ፣በንብረቷም ከውዱ ባለቤቷ ﷺ ጐን በመቆም ታሪክን አድምቃ አለፈች (ረድየላሁ አንህ)። ነብዩም ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ይሉ ነበር።

" "..وأين مثل خديجة صدقتني حين كذبني الناس

{ማን እንደኸዲጃ አይነት ።ሰዎች ባስተባበሉኝ ጊዜ ያመነችኝ ነበረች} ። ሙስሊም የዘገቡት ሃዲስ ላይ

ደግሞ ጅብሪል (ዐለይሂሰላም) ወደ ነብዩ ﷺ በመምጣት እንዲህ ብሏል ፡-

"አንተ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይህች ኸዲጃ ነች፡፡ ወደ አንተ መጥታለች፡፡ ከእርሷ ጋርም ሳህን ይዛለች፡፡ በውስጡም ወጥ ወይም ምግብ ወይም መጠጥ አለ፡፡ልክ ስትመጣ ከጌታዋ ከእኔም የሆነን ሰላምታ አቅርብላት፡፡ጀነት ውስጥ ከሸንበቆ የሆነን በውስጡ ጩኸትም ሆነ ድካም በሌለው ቤትም አበስራት፡፡"

ታዲያ እህቴ ሆይ! እኔና አንቺ የአማኞች እናት የሆነችውን ኸዲጃን ምን ያህል አርአያ አድርገናታል??? ምንም ቢመጣ ቢከሰት በኢማንና ዳእዋ ላይ ጸንተናል ??? ትክክለኛ እምነት (ዓቂዳን) እና የነብዩን ﷺ ፈለግ (መንሀጅ) ን ይዘው በመጓዝ ሌላውን ወደዚህ ብሩህ ጐዳና የሚጠሩ ወንድሞች ጐን ተሰልፈናል?? ባለንና በምንችለው ከጐናቸው ቆመናል?? መልሱን ለአንቺ ትቼዋለሁ።

✍ኡሙ ዑበደላህ ሙሐመድ





ዓኢሻ ቢንት ሲዲቅ



ዓኢሻ ቢንት ሲዲቅ የእውቀት ተምሳሌት ፡-

በኢስላም ታሪክ ውስጥ ሙስሊሟ ሴት ከወንዱ ጐን ቆማ እውቀትን ትቀስም ነበር ፡፡ ምንም ነገር ሳያግዳቸው በእውቀት መሰላል የበላይነትን ኮርቻ የተቆናጠጡ እንስቶች ጥቂት የሚባሉ አልነበሩም። ዳሩ የሚደንቅ አይደለም ፡፡ ነብያቸው (ﷺ)እንዲህ ሲል መሰረትን ጥሎላቸዋልና

"طلب العلم فريضة على كل مسلم"

«ዕውቀትን መገብየት (መፈለግ) በማንኛውም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው ፡፡ (ኢብኑ ማጀህ ኪታቡ ሱና224)

ታዲያ ከእነዚህ ውዶች መካከል እናታችንና የነብዩ (ﷺ)ተወዳጅ ባለቤታቸው የነበረችው አዒሻ ቢንት አቢዲቅ በቀዳሚነት ትጠቀሳለች። እጅግ በጣም ሰፊ እውቀትና ጥልቅ ግንዛቤ የነበራት ሴት ነበረች ፡፡ እድሜዋ በአስራ ስምንትና በአስራ ዘጠኝ አካባቢ እያለ ነበር ይህን የእውቀት ሀብት ያካበተችው ፡፡ አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ከሰባት ሰማያት ላይ ንፅህናዋት ያወጀላት እንቁ እንስት ናት። ዓምር ኢብኑል ዓስ ረዲየላሁ ዓንሁ ነብዩ አንድ ጦር ሜዳ ላይ በላኩት ጊዜ የተከሰተውን እንዲህ ሲል ተናግሯል።

ወደ እርሳቸው መጥቼ አንተ ዘንድ በጣም የሚወደደው ሰው ማነው? አልኳቸው። እርሳቸውም {ዓኢሻ} አሉኝ። ከወንዶችስ? አልኳቸው።{አባቷ} አሉኝ። ከዚያስ ማነው? አልኳቸው። {ዑመር ኢብኑል ኸጣብ} አሉኝና ሌሎችንም ወንዶች ቆጠሩ ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ስለ አዒሻ (ረድየላሁ አንህ) ሲናገሩ አል ኢማሙ ዙህሪ እንዲህ ብለዋል ፡-

«የአዒሻ ዕውቀት ተሰብስቦ ከሁሉም የነብዩ ባለቤቶችና ወደ ሁሉም ሴቶች ዕውቀት ጋር ቢወዳደር የአዒሻ ዕውቀት ይበልጥ ነበር ፡፡ (አል ኢስቲያዓብ 4/1883 አል ኢሷባ 8/140)

አዎ! ስንትና ስንት ታላላቅ ሰሃባዎች ናቸው የተለያዩ የእውቀት ዘርፎችን እንድታብራራላቸው ወደ አዒሻ ይመጡ የነበሩት ፡፡ ኡርወት ኢብኑ ዙበይር (ረድየላሁ አንሁ) እንዲህ ብሏል ፡-

«በፊቅህም ይሁን በህክምና እንዲሁም በግጥም ከአዒሻ የበለጠ አዋቂ አንድንም አላየሁም» (ታሪኽ አጠበሪ ሃዋዲሱ ሰና 58)

ሱብሃነላህ! ምን ያለት ታላቅ ሴት ነበረች! አላህ ስራዋን ይውደድላት ፡፡ አማኟ ሴት ከዚህ ብዙ ትማራለች ፡፡ ምክንያቱም ኢስላም ያጸደቀላትን መብት ተቋዳሽ የምትሆነው ስታውቅና ሥታውቅ ብቻ ነው ፡፡ እውቀት ከሌለ ግን የራሷንም ይሁን የሌሎችን መብትና ግዴታ ልታውቅ አትችልም ፡፡ እናም ውዷቷ እህቴ በተለይ ያላገባሽና ያልወለድሽ ከሆነ ይህንን እድል አላህ እስኪያድልሽ እራስሽን በትክክለኛ እውቀት ከትክክለኛ ሰዎች በመውሰድ ልትገነቢው ይገባል። ነገ እንዳያፀፅትሽ ዛሬውኑ ተጠቀሚበት አላህ የጣሩትን ሊረዳ ቃል ገብቷልና ፡-

وَالَّذِينَ جَاهَدُوا فِينَا لَنَهْدِيَنَّهُمْ سُبُلَنَا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ لَمَعَ الْمُحْسِنِينَ [٢٩:٦٩]

«እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን። አላህም በእርግጥ ከበጐ ሠሪዎች ጋር ነው።» (አል አንከቡት 69)

እንግዲህ የእንቁዎችን ማህደር እንዲህ በቀላሉ ዳሰን የምንጨርሰው አይደለም። ነገር ግን ከባህር ላይ መቋለፍም ቢሆን እንኳ ማስታወሱ አማኟ ሴት ከነጠረ ታሪኳ ብዙ እጅግ ብዙ ትማርበታለች ፡፡

ኡሙ ሱለይም

ኡሙ ሱለይም ከአንሷር ሴቶች የነበረች ስትሆን ኡሙ ሱለይም ቢንት ሚልሀን ተብላ ትጠራለች ፡፡ ከመስለሚ በፊት ማሊክ ቢን አንነድርን አግብታ አነስን ወለደች ፡፡ እርሱም መስለሚን ስላወቀና በዛውም ስለፀናች ተዋት ፡፡ ከዚያም ይህ ሁኔታ ገጠማት። በወጣትነቱ፣በሃይሉ ፣በንብረቱ ከመዲና ወጣቶች ውስጥ ተመራጭ የተባለ ወጣት ለትዳር መጣላት ፡፡ እርሱም **አቡ ጠልሀ** ከመስለሙ በፊት ነበር ፡፡ በወጣትነቱ፣በሃይልና ሃብቱ የየስራብ (የመዲና) ወጣት ሴቶች የአይን ማረፊያ ነበር ፡፡ እናም ኡሙ ሱለይም በዚህ ጥያቄው በደስታ ልትበር እንደምትደርስ አሰቦ ነበር ፡፡ ነገር ግን ባለችው ነገር ተደናገጠ ፡፡ እንዲህ አለችው “አንተ የጠልሀ አባት ሆይ! አንተ አምላክ ብለህ የምትገዛው ሀበሻዊ የሆነው የአከሌ ጐሳ የጠረበውና ከመሬት የበቀለውን ዛፍ እንደሆነ አታውቅምን??? እርሱም “እንዴታ” ሲል መለሰ ፡፡ እርሷም ቀጠለች “ታዲያ እከሌ ለጠረበውና ከመሬት ለበቀለው ስታጐበድድ (ስትሰግድ) አያሳፍርህምን?”። አቡ ጠልሀ ግን ያለበትን የሙጥኝ በማለት በውድ ስጦታና በተመቻቸ ኑሮ ሊያታልላትና ሊያሳምናት ሞከረ። ኡሙ ሱለይም ግን ባለችበት ፀናች። እንዲህም አለችው። “በአላህ ይሁንብኝ አቡ ጠልሀ መስልህ የሚመስስ አልነበረም ፡፡ ዳሩ ግን አንተ ከሃዲ ወንድ ስትሆን እኔ ደግሞ አማኝ ሴት ነኝ ፡፡ ስለሆነም አንተን ማግባት ፈፅሞ አይፈቀድልኝም። ከሰለምክ ግን ጥሎሽ (መህር) አርሱ ይሆናል ሌላም አልጠይቅህም”። ታዲያ በዚህ መልኩ አርሱም የተለያዩ ነገሮችን በማድረግ ለማሳመን ሞከረ ፡፡ አርሷም በአቋሟ ፀናች በመጨረሻም እንዲህ አለችው ፡- “አንተ የጠልህ አባት ሆይ የምታመልኩት አምላክ የአከሌ ብሂረሰብ የሚጠርበውን ዛፍ መሆኑን እውን አውቀሃልን? እናንተም አባት ብትለኩሰበት የሚያያዝና የሚቃጠል አኮ ነው ፡፡” በዚህ ጊዜ ግን ይህ ንግግሯ አቡ ጠልሃን ከፍኛ አስደነገጠው። አራሱንም ጠየቀ። “እውነትም እውን ጌታ ይቃጠላልን???” በዚህ ጊዜ ነብር አንደበቱ የእውነትን የምስክርነት ቃል የተናዘዘው ፡፡

“ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና መህመድም የእርሱ ባሪያና መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ ” በማለት ከክህደት ወደ ኢስላም የገባው ፡፡ በዚህ ግዜ ግዚን የመታችው፣አላማዋን እውን ያደረገችው ኡሙ ሱለይም በደስታ ደምቃና ፈክታ ልጇን አነስን (ረዲየላሁ ዓንሁ) እንዲድራት ጥያቄ አቀረበችለት። እርሱም ምስክሮችን በማምጣት የጋብቻው ስነስርአት እውን ሆነ ፡፡

(ነሳኢ **ሰሂህ በሆነ ሰነድ ዘግበውታል**። ኪታቡ ኒካህ 6/114)

ሱብሃነረቢ! በጣም ይገርማል። ኡሙ ሱለይም ሃብት ጤና መልክ ቁመና ሌላም ሌላም ሳይበግራት ያስቀመጠችው የእምነት መስፈርት ከጫፍ ደርሶላታል። ስታደርገው የነበረውም ወደ “ተውሂድ” የመጣራትና የ”ሽርክን” ከንቱነት የማብራራት ሁኔታ በእውነቱ ምን ያህል የተፈጠረችለትን አላማ በሁሉም የህይወት ዘርፍ ተግባራዊ አድርጋ ለማለፍ ያላትን ቁርጠኝነት ቁልጭ አድርጎ የሚያስቀምጥ ነው ፡፡ ታዲያ ይህችን መሰል እፁብ ድንቅ እንስት ነው ሙስሊሟ ሴትም እውን አማኝ ከሆነች አርአያ የምታደርገው።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

የትዳር የመጀመሪያ ወራቶች !!

የትዳር የመጀመሪያ ዓመት አዲስ የህይወት ምዕራፍ መክፈቻ እንደመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋል። በዚህ ወቅት የሚያጋጥሙ የቤት ውስጥ ፈተናዎችን ለመወጣት ባልና ሚስት ከባድ ኃላፊነቶች ይወድቅባቸዋል።

የመጀመሪያ ዓመቱን በሠላም ማጠናቀቅ የቻለ ትዳር ቀጣይ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። በርካታ ፍቺዎች በትዳር የመጀመሪያ ዓመት እንደሚፈጽሙ የሚጠቁሙ ጥናቶች አሉ። ከዚህ ለመዳን በትዳር የመጀመሪያ ዓመት ሊወሰዱ ስለሚገቡ ጥንቃቄዎች በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።



በትዳር ውስጥ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባውና እጅግ አስፈላጊ የሆነው የመተማመን መንፈስ መሠረቱ የሚጣለው በትዳር የመጀመሪያ ዓመት ነው። ባለትዳሮች በዚህ ጥንቃቄን በሚፈልግ ወሳኝ የትዳር ወቅት ይህን መተማመን እንዴት መገንባትና ማዳበር እንደሚኖርባቸው ማወቅ ኖርባቸዋል። በዚህ ግዜ መተማመን ከሚያደፈርሱ ነገሮች ሁሉ መራቅ አለባቸው። በዚህ ግዜ በመካከላቸው በቂ የመተማመን መንፈስ መገንባት ካልቻሉ የትዳራቸው ዘላቂነትና ህልውና ከፊት ለፊቱ አደጋ ይጋረጥበታል።

በትዳር የመጀመሪያ ወራት ባልና ሚስት የትዳር ተጣማሪዎቻቸውን ዝንባሌ፣ ፍላጎት አስተሳሰብና ጠቅላላ ስብዕና በቅርብ ለመረዳት መሞከር አለባቸው ወንዶችንና የሴቶችን ስብዕና ጅምላ በአራት ክፍሎች ከፋፍሎ ማስቀመጥ ይችላል።

ምክንያታዊ ስብዕና

ይህ ስብዕና አውነታዎችና መረጃዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋል፤ ሁኔታዎችን ሳይፈትሸና መርጃን ሳይመለከት ውሳኔ ለመስጠት ይቸገራል። «ምን ያህል» «ለምን» «እንዴት» የሉ ጥያቄዎች ዘወትር ከአንደበቱ አይጠፉም።

ፈጠራና ለውጥ አፍቃሪ ስብዕና

ይህ ስብዕና ሁልግዜ መታደስ ይወዳል። ለውጥ ይፈልጋል። ሐሳቦቹ ጠንካራና ጥልቅ ናቸው። ለምሳሌ ይህን ዓይነት ስብዕና ያላት ሚስት በአዳዲስ አለባበስ ስልቶች ሁልግዜ ለባልዋ አዲስ ሆና መቅረብ ትፈልጋለች።

ትዕዛዝ ተቀባይና ስርዓት አፍቃሪ ስብዕና

ይህ ስብዕና ለውጥና አዲስ ነገር ስሜቱን አይኮረኩረውም። ሁሉ ነገር ባለበት እንዲቀጥል ይፈልጋል። ስርዓት በጣም የሚወድ ሲሆን ስርዓት አልበኝነት ይጠላል። ለምሣሌ ይህን ዓይነት ስብዕና ያላት ሴት ከባልዋ ጋር በምትሆንበት ግዜ ለረዥም ወቅት አንድ አይነት ልብስ ብቻ ታዘወትራለች። ስርዓት መውደድ ጥሩ ቢሆንም ስርዓት መጠበቅን በዚህ መንገድ መተርጎምን መጠበቅ ግን ስህተት ነው።

ስሜታዊ ስብዕና

ይህ ስብዕና እጅግ ሲበዛ ስሜታዊ ነው። በቀላል ነገር ልቡ ይኮረኮራል፤ እንባው ዓይኖቹ ጫፍ ላይ ነው። እርጋታ ይወዳል፤ ሠዎችን መርዳት ያስደስተዋል።

ከላይ የተጠቀሱት የስብዕና ዓይነቶች ተፈጥሮዓዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ባልና ሚስት የትዳር ተጣማሪዎቻቸው ምን ዓይነት ስብዕና እንዳለቸው መረዳት እና ከዚያ ስብዕና ጋር ተስማሚ የሆነ አካሄድ መምረጥ አለባቸው አንድ አይነት ተመሳሳይ ስብዕና ካላቸው ነገሮች በተሻለ ቀላል ይሆናሉ። ስብዕናቸው የተለያየ ከሆነ ግን የመደጋገፍ የመሚሚላት ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

በትዳር የመጀመሪያ ወራቶች ሊታወቁ ከሚገባቸው አስፈላጊ ነጥቦች አንዱ በቤት ውስጥ ለራስ ያለን መብት እና በራስ ላይ ያለን ግዴታ ማወቅ ነው። ኢስላም ለባልና ሚስት ለእያንዳዳቸው ያለን መብት እና በራስ ላይ ያለን ግዴታ ማወቅ ነው። ኢስላም ለባልና ሚስት ለእያንዳዳቸው የየራሳቸውን መብቶች ሰጥቷቸዋል፤ በእያንዳንዳቸው ላይ ያለውን ግዴታ አስቀምጧል። በተለይ በመጀመሪያ የትዳር ወራቶች ኢስላም ለትዳር አጋር ያስቀመጠውን መብት መስጠትና የራስን ግዴታ መወጣት ለትዳር ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ብዙ የትዳር ፈተናዎች እና መናጋቶች ባል የራሱን መብት ሲያስታወስና የሚስቱን መብት ሲረሳ ፣ ሚስት የራሷን መብት ስታስታውስና የባልዋን መብት ስትረሳ የሚፈጠሩ ናቸው። ይህ ሁኔታ በተለይ በትዳር የመጀመሪያ ዓመት ልዩ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል። (በቀራህ 237)

ጤናማ ትዳር

የትዳር ህይወት ጤናማ እንደሆነ ሶስት መሠረታዊ ነጥቦች አሉ። የሠከነ እና ለተጣማሪዎቹ ሠላማዊ ህይወት የሚመግብ ትዳር እነዚህን ሶስት መሠረታዊ ነገሮችን ሚሟላት አለበት።

1 ሙገሳና አክብሮት

ጤናማ የትዳር ህይወት ብዙ ጥረት ይፈልጋል። ጤናማነቱ እያበበና እያደገ እንዲሄድ ደግሞ ጥረቱ መቋረጥ የለበትም። ይህም ሆኖ ፈተናዎች ችግሮች ማጋጠማቸው አይቀርም። በትዳር ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለማለፍ ደግሞ በባልና በሚስት መካከል መከባበር መኖር አለበት። ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው የሚለዋወጡበት አክብሮትና ሙገሳ ከፍተኛ ስነ ልቦና ጠንካራን ይፈጥርላቸዋል። በመሀላቸውም ጠንካራ መተማመን ያብባል። በዚህ ታግዘው ከችግሮቻቸው በአላህ ፈቃድ ሊወጡ ይችላሉ። ሙገሳና አክብሮት መለዋወጥ ለትዳር ህይወት ጤናማነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። በላትዳሮች ችላ ሊሉት አይገባም። የትዳር ጤናማነትም ይጠቁማል።

2 ለትዳር አጋር መልካም መመኘት

ለትዳር አጋሩ መልካም መመኘት የማይወድ ሠው አለ የሚለውን ለማመን ይከብዳል። ነገር ግን በአሳዛኙ ጤንነቱን ባጣ የትዳር ህይወት ውስጥ ይህን ይህን አይነት ችግር ሊከሰት ይችላል። በትዳር ተጣማሪዎች መካከል ጥላቻና ሌላውን የመጉዳት ስሜት ሊኖር አይገባም።ይህ ስሜት ካለ ትዳሩ በሽተኛ ነው። በጣም አደገኛም ስለሆነ አስቸኳይ ህክምና ያስፈልገዋል።

3 ምስጢር ከቤት አለማውጣት

የቤት ውስጥ ምስጢሮች ሾልከው በየስፍራው የሚገኙበት ትዳር ጤናማ አይደለም። ጤናማ ሊሆንም አይችልም፤ ጤንነቱን ለማስመለስም ይከብደዋል። ጤናማ የትዳር ህይወት ለትዳር ውስጥ ምስጢሮች ከፍተኛ ትኩረትና ጥንቃቄ ይሠጣል። የቤት ችግሮች ምንም ያህል ቢገዝፉ አደባባይ አያወጣቸውም። ምስጢርን የመጠበቅ ይህ ሁኔታ ትዳሩ ጤናማ መሆኑን ከማሳየቱም ባሻገር በባልና በሚስት መካከል ያለውን ጠንካራ ትስስር ያሳያል። ኢስላም የቤት ውስጥ ምስጢሮች መጠበቅና ባልና ሚስት ጋር መቅረት እንዳለባቸው የጠበቀ መርህ አስቀምጧል። ይህ መርህ በትዳር ውስጥ በተግባር መተርጎም አለበት። የሠከነ ትዳር ለማግኘትም መሠረታዊ ነጥብ ነው።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

ጠቃሚ ነጥቦች ለትዳር !

ሁልግዜም ቢሆን በትዳር ውስጥ ችግሮች መፈጠራቸው አይቀርም። አልፎ አልፎ በባልና በሚስት መካከል መጨቃጨቆች ሊፈጠሩ ይችላል። እነዚህ ሁኔታዎች በሁሉም ትዳር ውስጥ የሚከሠቱ እና የሚጠበቁ ነገሮች ናቸው። በመነሻ ላይ ብዙም ጉዳት ላይኖራቸው ይችላል። እየተደራረቡ ስሄዱ ግን የትዳሩን ህልውና የሚፈታተን ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላሉ። በትዳር ህይወት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

በዚህ ወቅት ባልና ሚስት የትዳራቸውን ህልውና ለመታደግ እና መሠላቻቸትን ለማስቀረት የመፍትሄ እርምጃዎችን መውሠድ ይኖርባቸዋል። የሚከተሉት ምክረ - ሐሳቦች ትዳር ሁልግዜም ጣፋጭ ሆኖ እንዲቀጥል ይጠቅማሉ።

1 ፍፁም እና እንከን የለሽ ትዳር የለም። ባልና ሚስት ይህን ማወቅ አለባቸው። የሁሉም ሠው ትዳር ሠላማዊና ጭቅጭቅ አልባ የነርሱ ትዳር ብቻ በጭቅጭቅ የተዋጠ እንደሆን ማሠብ አይኖርባቸውም። አልፎ አልፎ የሚከሠቱ ጭቅጭቆችና አለመግባባቶች በየትኛውም ትዳር ውስጥ ሊኖር የሚችል የትዳር ህይወት አንድ ገጽታ ነው። ይህ መገንዘብ ይጠቅማል።

2 አለመግባባቶች ሲከሰቱ ወደ ከረረ ጭቅጭቅ ቁመት ከመጨመራቸው በፊት ገለል ማለት በጣም ጠቃሚ ነው። ነገሮች ረጋ ብሎ በሠከነ መንፈስ ለማሰብ እና ልዩነቶችን ለማብረድ ይረዳል።

3 ባልና ሚስት በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ለራስ ጠበቃ የመቆም ዝንባሌ ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ስህተቱን ማመን እና በስህተቱ የተፈጠረውን ችግር ኃላፊነት ችግር መቀበል እንዲሁም ጭቅጭቆችን ማለሥለስ ፣ በጭቅጭቅ ወቅት ለትዳር አጋር ፍቅር ለማሳየት መሞከር ፈተናዎችን ለመሻገር ይረዳል፤ ትዳርንም ጣፋጭ ያደርጋል።

4 ህይወትን በቁም ነገር ከምጠጥ ባለ ነገሮች ብቻ እንድትቀጥል ማድረግ ያስቸግራል። ስለሆነም ከሐራም በራቀ ሁኔታ በቤት ውስጥ የተፍታታ እና ቀለል ያለ የሚያዝናና ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል። ባልና ሚስት በየግዜው በጋራ ዘና የሚሉበት ፕሮግራም ሊኖራቸው ያስፈልጋል።

5 ባልና ሚስት ሁሌም ሊነጋገሩ ይገባል። በግልፅና በመደማመጥ የመነጋገር ባህል ማዳበር አለባቸው፤ ይህ ባህል በሠላምና በፍቅር ግዜ ብቻ ሳይሆን ፣ በአለመግባባትና በጭቅጭቅ ግዜም ሊታይ ይገባል። መነጋገር የማይችሉ ባለትዳሮች ደስታ አኖራቸውም፤ የትዳር ዕድሜው አጭር ይሆናል።

6 ባለትዳሮች አንዳንድ ነገሮች በጋራ የማድረግ ወይም የማዘውተር ልምድ ማዳበር እጅጉም ይጠቅማቸዋል። አብሮ ቁርዓን (ማዳመጥ) ፣ አብረው ጉዞ ማድረግ፣ አብረው ገባያ መውጣት፣ አብረው መመገብ... .

7 ስህተቶችን ሁሉ በትዳር አጋር ትካሻ ላይ ማሳረፍ ጭቅጭቆች እንዲዳብሩ ስለሚያደርግ ከዚህ መራቅ ያስፈልጋል።የትዳር አጋር ራሱን ማስረዳት እንዲችል ዕድል ሊሠጠው /ሊሰጣት ይገባል።

8 ባለትዳሮች ለትዳራቸው በቂ ትኩረት መስጠት አለባቸው፤ ትዳራቸውን እንደ ህይወት ሊመለከቱት ይገባል። ብዙ ግዜ የባል ወይም የሚስት ትኩረት ትዳር ላይ መሆኑ ቀርቶ ስራቸው ወይንም ትምህርታቸው ላይ ሲሆን ችግሮች መፈጠር ይጀምራሉ። ይህ እንዲሆን መፍቀድ የለበትም። ስራ ወይንም ትምህርት ሊሠጣቸው ይገባል። ነገር ግን ትዳርን እና የትዳር አጋርን ወደ ማስረሳት ደረጃ ከፍ ሊሉ አይገባም። የትዳር አጋር በቂ ትኩረትና ግዜ ሊያገኝ የግድ ይላል።

9 በትዳር ውስጥ በሁሉም ጉደይ ላይ ስሞታ ማቅረብ መሠላቸትን ይፈጥራል፤ ለትዳር ጠቃሚ አይደለም። ማሳለፍ ባህል መሆን አለበት።

10 የትዳር አጋራችን ራሱን እንዲሆን መፍቀድ መቻል አለብን፤ የትዳር አጋራችን በሁሉ ነገር የእኛን ፍላጎት እንዲከተል እና ማንነቱን እንዲቀይር ማስገደድ የለብንም።

11 አክብሮት መለዋወጥ ለባለትዳሮች መሠረታዊ ነገር ነው። ፀያፍ ቁስል የሚፈጥሩ ቃላቶችን በትዳር አጋር ላይ ከመሠንዘር መቆጠብ ያስፈልጋል። በተለይ ይህ ነጥብ በንዴት እና በጭቅጭቅ ወቅቶች ሊተኮርበት ይገባል።

وَقُل لِّعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ إِنَّ الشَّيْطَانَ يَنزَغُ بَيْنَهُمْ ۚ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلْإِنسَانِ عَدُوًّا مُّبِينًا [١٧:٥٣]

<<ለባሮቼም በላቸው፦ ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ። ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና። ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና። >> /ኢስራእ 53/

የባልን ክብርና ስሜት መጠበቅ

መልካም ሚስት ባልዋ የሚወደውንና የሚያስደስተውን ነገር ጠንቅቃ ታውቃለች የሚያስደስተውንም ነገር ለመፈጸም ዘወትር ቁርጠኛ ናት ባልዋን ማስደሰት ብቻ ሳይሆን እንዳይከፋባትም ጥንቃቄ ታደርጋለች። ከባልዋ ፍላጎትና ደስታ ፊት ጋሬጣ ሆና የምትቀም ግትር አይደለችም። በባልዋ መከፋት ውስጧ የሚደሰት የቤት ምስጥም አይደለችም። በባልዋ ላይ የበላይነቷን ለማሳየትም ትዕቢት አይዘትም። የባልዋን ስሜት ትጠብቃለች። ስነ ልቦናው እንዳይጎዳ እርሱ ለራሱ ከሚያስበው በበለጠ እርሷ ለርሱ ታስባለች። እጅግ የሚያረካት ነገር የትዳር አጋሯን የደስታ ፊት ማየት ነው። ደስታውን እርሷ የሠራችው ከሆነ ደግሞ እርካታዋ ወደር አይኖረውም።

ዑደላህ ቢን ጀዕፈር አቡሚሊብ ለባለትዳር ልጁ የሚከተለውን ምክር መስጠቱን የታሪክ ድርሳናት ጽፈዋል

"ልጄ ሆይ ከቅናት ራሽን ጠብቂ ፤ በትዳር ውስጥ መቅናት የፍቺ ቁልፍ ነው። ብዙ ቅሬታ አታሳሚ ቅሬታ ጥላቻን ይወልዳል።... "
መልካም ሚስት ባልዋ በቤት በማይኖርበት ግዜው ቢሆን ክብሩን ትጠብቃለች በነፍሷ እና በንብረቱ ላይ ክህደትን አትፈጽምም። ከራሷ ፍላጎትና ሀቅ ፣ የባሏን ፍላጎትና ሀቅ ለማስቀደም ትመርጣለች ምላሷ አጭር ነው ባልዋን የሚያስቀጣ መርዝ ቃላቶች አያምራትም።

ትዳርን የሚያናጉ 4 ምክንያቶች

በርካታ ጉዳዩች ትዳርን የሚያፈርሱ ምክንያቶች ይሆናሉ። በተለይ አራት ምክንያቶች በትዳር ውስጥ ከተከሠቱ በትዳሩና በፍቺ መካከል የሚኖረው ርቀት ቅርብ ይሆናል። የትዳርን ውድቀት ያፋጥናሉ። የሚከተሉት ናቸው።

ንቀት

አንድ ሙስሊም በፍጹም ሙስሊምን ሊንቅ አይገባም ንቀት አንድን ሠው ለጀሀነም ሊዳረግ የሚችል በቂ መጥፎ ተግባር ነው። ንቀት የትዳርን ህይወት የመበጥበጥና የማፍረስ ዓቅሙ ከፍተኛ ነው። ጥላቻን ይወልዳል። መርዝ ያመነጫል። ንቀት በቃላት ብቻ ሳይሆን በፊትና በእንቅስቃሴም የሚገለጽ ስሜት ነው። በየትኛውም መንገድ መወገዝ አለበት።

ትኾት (የመረረ ነቀፌታ)

በትዳር ውስጥ ብዙ ችግሮች ሊከሠት ይችላል። በዚህ ወቅት ስርዓት ባለው መንገድ ቅሬታን ማሠማት ችግር አይኖረውም። ሆኖም ግን ቅሬታን በመረረ ትኾት መግለጽና ስህተቱንና ስህተት ፈጻሚውን ደባልቆ በኃይል ቃል መንቀፍ ለትዳር አጋር መጥፎ መልዕክት ያስተላልፋል። ለምሳሌ ሚስት የቤት ቆሻሻዎችን ወደ ውጪ ሳታወጣ ቀረች። «ረስታ» ሲሆን ተንኮለኛ ስለሆንሽ ነው ያላወጣሽው የሚል ስህተቱን ሳይሆን ራሷን (ስህተቱ ላይ ሳይሆን ስህተት ፈጻሚ ላይ) ያነጣጠረ ቅሬታ መሠንዘር በትዳር ህይወት ውስጥ ችግር ይፈጥራል። በተደጋጋሚም ሲከሠት ትዳሩ የፍቺ በር ማየት ይጀምራል።

ራስን መከላከል

ችግሩ የእኔ አይደለም፤ የአንቺ ነው። ይህ አገላለጽ በውስጡ ራስን የመከላከልና ሌላውን በጅምላ የማውገዝ ድባብን ይዟል።አለመግባባት ያባብሳል። በመጨረሻም ወደ ፍቺ በር ያደርሳል። ስለዚህ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ራስን መከላከያ ድንበር ማስመር ብቻ ሳይሆን የትዳር አጋርን ስሜት ለመረዳት ይበልጥ ጠቃሚ ይሆናል። ሌላውን በማውገዝና ራስን በማጽዳት የትዳር ዘለቄታ ማረጋገጥ አይቻልም።

ችግሮችን በውይይት አለመቋጨት

ውይይት ማቆም ወይንም በዚህ ርዕስ በፍጹም አልነጋገርም ብሎ ውይይትን አቋርጦ መውጣት፣ ችግሮች እንዳይቋጩ ያደርጋል። ችግሮች ዘወትር ተንጠልጥለው ይቀጥላሉ። ይህ ሁልግዜ የተከፈተ፣ ያልተከደነ ፣ ያልተቋጨ አጀንዳ ይኖራል። ይህ ሁኔታ የትዳር ህይወትን ይጎዳል። ችግሮች እንዲከማቹም ያደርጋል። በመጨረሻም ለፍቺ ያጋልጣል።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

የባልሽኝ ልብ ለመያዝ

የትዳር ህይወትን በኢማን ያበበ ጣፋጭ ለማድረግ የትዳር ክህሎቶችን ማወቅ ያስፈልጋል። ወደ አዲስ የትዳር ህይወት እግሯን ያስገባች ወጣት ሴት የትዳር ክህሎቶችን በተለይም የትዳር አጋሯን ልብ መቆጣጠር የምትችልባቸውን ባህሪያት ጠንቅቃ ማወቅ አለባት። በርግጥ የትዳር ህይወት ክህሎቶችን ማወቅ አዲስ ትዳር ውስጥ የገቡ ወጣት ሴቶችን ብቻ ሳይሆን በትዳር ውስጥ ያሉትን ሁሉ ይመለከታል።

ጓደኛው ሁኚ

ባልሽ ሚስቱ ብቻ ሳይሆን ጓደኛውም እንድትሆኚ ይፈልጋል። ልቡን በእጅሽ ለማስገባት ከማንም በላይ የሚቀርበው ጓደኛ ሁኚለት ሁሉንም ጉዳዩቹን ተካፈይው። ችግሮቹን አድምጪው። ለርሱ ችግር መጨነቅሽንና በችግሩ ፊት አብረሺው እንደምትቀሚ አስረጂው ጓደኝነታችሁ የጠለቀ እንዲሆን በምድር ላይ የሚያስፈልግሽ ብቸኛው ሠው እርሱ እንደሆነ እንዲሠማው አድርጊው ጓደኛሞች የሚያደርጉት ሁሉ አብራችሁ አድርጉ።

እናቱን ሁኚለት፣

እንደ እናቱ ተንከባከቢ ሁኚለት፤ እንደ አባት አሳቢ ይሆንልሻል፤ ልቡን አሳልፎ ይሰጥሻል። ህግን መሆን ሲያምረው እቀፊው። እናት ለልጇ የምትሠጠውን እንክብካቤ ስጪው። አርፍዶ ሲገባ መጨነቅሽን አሳይው። ዓለሙን ሁሉ ሁኚለት በሚወዳቸው ትናንሽ ነገሮች ላይ ሳይቀር ትኩረት አድርጊ። እንክብካቤሽና የምታሳይው አሳቢነት ልቡን ይቆጣጠረዋል። ከእንቺ መለየት ከእናቱ እንደመለየት ይከብደዋል።

ከግትርነት ራቂ

ወንድ ልጅ ግትራና ጨቅጫቃ ሴትን አይወድም። በንዝንዝ ህይወቱን ወደ እስር ቤት የምትለውጥበትን ሴትን አይወድም ግትርነት እና ጭቅጭቅ የትዳር ሠላምን ያናጋል። በምትነጋገሩበት ወቅት ስህተቱን ብትነግሪው ችግር የለውም። በፍጹም ግን ከብሩንና ወንድነቱን አትፈታተኚው። የምትፈልጊውን የሚሚላት ብቃት እንደሌለው እንዲሰመው አታድርጊ። ከዚህ በኋላ ልቡ ውስጥ ቦታ አይኖርሽም። የወንድ ልጅ ክብር የሚቆሰለው በፍጥነት ነው። ከዚያ በኋላ ለማከም ያስቸግራል።

ንፁህ ልብ ይኑርሽ

ባል ንፁህ ልብ ያላት ሚስቱን እስከ እድሜው መጨረሻ ከመውደድ አይቆጠብም። ረሡል አላህ ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የመጀመሪያ የህይወት አጋራቸውን ኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድን ምን ያህል ይወዷትና ከህልፈቷ በኋላም ምን ያህል ያስታውሷት እንደነበረ አስታውሺ ለኸዲጃ ካላቸው በጣም ብዙ የውዴታ ምክንያቶች አንዱ ኸዲጃ ንፁህ ልብ ያላት ምርጥ ሴት መሆኗ ነው።

በተንኮል ልቧን ለሞላች ሚስት ልቡን አሳልፎ የሚሠጥ ባል የለም። ሚስቱን መጀመሪያ ላይ የሚወድ ቢሆን እንኳ ተንኮለኛ ልብ ካላት በሂደት እየጠላትና ልቡን ከእርሷ እያራቀ ይሄዳል። ቀስበቀስም አንዲትም ደቂቃን ቢሆን ከእርሷ ጋር ለማሳለፍ ይጠላል። የባልሽን ልብ ለመቆጣጠር ንፁህ ልብ ይኑርሽ።

ቀልድ እወቂ

ባልሽ ፈገግ እንዲል ቀልድ ንገሪው በራስሽ ላይ ፣ በርሱ ላይ ለጨዋታ የሚሆን ቀልድ ፍጠሪ ቀኑን ብሩህ አድርጊለት፤ ልቡን አሳልፎ ይሠጥሻል። ጭንቀቱን ቀላል ስላደረግሽለት ያመሰግንሻል፤ ከልቡ ይወድሻል። ባሎች ቀልድ የሚችሉ ሚስቶችን ይወዳሉ።

በዐይኖችሽ አናግሪው፤

ዐይን የልብ መስተዋት ነው። አንደበትሽ ሳይናገር በዐይኖችሽ ብቻ ምን ያህል እንደምትወጂው ንገሪው። ዐይኖችሽ ወደ ዐይኖቹ ፍቅርሽን ያደርሱልሻል። የዓይኖችሽ መልዕክቶች ከአንደበትሽ በበለጠ ወደ ባልሽ ልብ በፍጥነት የደርሳሉ። ልቡንም ይቆጣጠሩታል። ተፅዕኖአቸውም ከባድ ነው። ዓይኖችሽን መናገር ያስቻላቸው መናገር አላህ የተመሠገነ ይሁን።

ውበትን መጠበቅ በትዳር ውስጥ

አብላጫ ቁጥር ያላቸው ሴቶች ከትዳር በኋላ ራሳቸውን ይጥላሉ። አንዳንድ ሴቶች ራሳቸውን በመጠበቅ ረገድ ከኒካህ በፊት የነበራቸው እና ከኒካህ በኋላ የሚኖራቸው ሁኔታ የሠማይና የመሬት ያህል ይለያያል። ይህ ከባድ ስህተት ብዙ ትዳሮችን የጦርነት ቀጠና አድርጓቸዋል። ወጣት ሴቶች ከትዳር በኋላ ከትዳር በፊት ከነበራቸው ልምድ በተሻለ ውበታቸውን ለመጠበቅ እና ለባሎቻቸው ዕይታ በመጉላት ላይ ብርቱ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ትዳር ውበታቸውን ከመጠበቅና ከመንከባከብ ጋር የሚለያዩበት የመሰነባበቻ ድንበር አለመሆኑን መረዳት አለባቸው። እንድያውም ትዳር ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ውበት የሚጠበቅበት፣ ለትዳር አጋር ራስን ውብ አድርጎ ለማሳየት ከፍተኛ ትኩረት የሚሠጥበት የአዲስ ህይወት መክፈቻ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። በዚህ ጉዳይ ላይ አላህን መፍራትና የባሎቻቸውን ሀቅ መጠበቅ አለባቸው። መልካም ሚስት ባልዋ አላህን በማይፈቅደው ፈተና ላይ እንዳይወድቅ ዐቅሟ የቻለውን ሁሉ ታደርጋለች። ዘወትር ራሷን ውብ በማድረግ ዓለሙን ሁሉ ረስቶ ዐይኖቹ በርሷ ላይ ብቻ ያጠሩ እንዲሆኑ ትተጋለች። በባልዋ ዐይን አስቃሚና ራሷን ያልጠበቀች ሆና ከመታየት የበለጠ የሚያስጠላትና የሚያስፈራት ነገር አይኖርም።

ትክክል ነው ባለቤትሽ ውብ ሁነሽ አጠገቡ ስትቀርቢ እርካታን ያገኛል። ደስታ ይሠማዋል። አላህ አንቺን ስለሠጠው አመስጋኝ ይሆናል። ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ ግን ውበትሽን በመጠበቅሽ የመጀመሪያው ተጠቃሚ አንቺው ራስሽ ነሽ። ውበትሽን ስትጠብቂ ስለራስሽ ያለሽ ግምት ከፍ ያለ ይሆናል። ጥሩ ይሠማሻል። ዘወትር ውብ ለመሆን መሞከር ውብ ነገር ነው።

ብዙ ሚስቶች ከትዳር ጥቂት ወራት ቆይታ በኋላ ከብደታቸው ይጨምራል። ባል የሠውነት መገጣጠሚያቸው ለመለየት እስኪቸገር ድረስ ያለመጠን ይወፍራሉ። ራሳቸውን ለመጠበቅ የአመጋገብ ስርዓታቸውን ለማስተካከልም ሆነ በኢስላማዊ አዳብ በቤት ውስጥ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለማድረግ አይፈቅዱም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ባል ፍፁም ማየት የማይፈልገውን ገጽታ ይላበሳሉ። ውፍረት ውበትን ከመዋጡም በተጨማሪ ለጤና ችግር ያጋልጣል። ይህን ማወቅና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ፀጉር የሴት ልጅ ውበት ዋነኛ መገለጫ ነው። ከትዳር በኋላ ፀጉርሽን ብዙ ጊዜ የምትታጠቢበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም። ይህም ስለሆነ ለፀጉርሽ የምትሰጪው እንክብካቤ ከትዳር በፊት ከነበረው ሁኔታ በብዙ መጠን መጨመር አለበት። ውሃ የሚነካው ፀጉር ብዙ እንክብካቤ ያስፈልገዋል።

አለባበስ ውበትን ያጎላል። ከባልሽ ጋር በሚኖርሽ ቆይታዎች ሁሉ አቅም በፈቀደ አለባበስሽ ዘናጭና ዓይኖቹን ከአንቺ ላይ የማያስነቅል መሆን አለበት። በቤት ውስጥ ከእርሱ ጋር ካለሽ በፍፁም ያረጁና ቆሻሻ ልብሶችን ከመልበስ ተጠንቀቂ። አዲስና ንፁህ ልብሶች በባልሽ ፊት ካልለበስሻቸው ትርጉም የላቸውም። በቻልሽው መጠን በየግዜው አለባበስ ስልትሽን ቀያይሪ። አለባበስሽ ዘወትር አዲስ ሠው የሚመለከት ያህል እንዲሠማው የማድረግ ዐቅም ይኑረው።

ጠረን ነፍስን ያናግራል። ትዝታዎችን ይሸከማል። በባልሽ ፊት የሚኖርሽ ጠረን ልብን የሚሠረስር ጣዕም እንዲኖረው ጥረት አድርጊ። ሁልግዜ በጥሩ ሽታ ባልሽን ልትቀርቢው ይገባል። ይህን ለማሳካት በየዕለቱ መታጠብና ሽቶ መታጠን የሚያስፈልግ ከሆነ ከማድረግ ወደ ኋላ አትበይ። ሽቶሽ ግን በፍፁም ተከትሎሽ ከቤት እንዳይወጣ ጥንቃቄ አድርጊ። ውብ ጠረንሽ ማሽተት የሚፈቀድለት በአላህ ቃል የህይወት አጋርሽ የሆነው የባልሽ አፍንጫ ብቻ ነው።

በቤት ውስጥ የሚኖርሽን ጠረን ሁልግዜ ብዙም ሳትቸገሪ ጣፍጭ ሆኖ እንዲቀዋል ወጥ ቤት ስትገቢ የምትለብሺው ተለዋጭ ልብስ ማዘጋጀት ጠቃሚ ይሆናል።

ለህይወት አጋርሽ ውብና ንጹህ ለመሆን የምታደርጊውን ጥረት ሁሉ የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም እንደምታደርጊው መልካም ስራ አስቢው። በእርግጥም የአላህን ውዴታ የሚያስገኝልሽ መልካም ስራ ነው። በአላህ ፈቃድ ይህ መልካም ስራሽ ጀነትን የሚያወርስሽ ምክንያት ሊሆን ይችላል። የአላህ ቸርነት ሠፊ ነው።



ቤተሰባዊ ጉዳይ

የሙስሊም ቤተሰብ ኢኮኖሚው ገጽታ ምን መምሠል አለበት ?

የሙስሊም ቤተሰብ ኢኮኖሚው ገጽታ ምን መምሠል አለበት ?

የሠዎች ሪዝቅ የተለያየ ነው። የአንዱ ሪዚቅ (ሲሳይ) እንደ ውቅያኖስ ሠፊ ይሆናል። ይህ ደግሞ የአላህ ችሮታ ነው። የሌላው ሪዚቅ አንደ እጅ መዳፍ ጠባብ ይሆናል። ይህ የአላህ ጥበብ ነው። ይህ ቢሆንም ሪዝቁ የሠፋ አላህ ዘንድ የተወደደ ነው ማለት አይደለም። ሪዝቁ የጠበበም አላህ ዘንድ የተጠላ ነው ማለት አይደለም። በተቃራኒውም ገንዘብ ያገኘ ሁሉ አላህ ዘንድ የተጠላ ነው ማለት አይደለም። ገንዘብ ያጣም ሁሉ አላህ ዘንድ የተወደደ ነው ማለት አይደለም። አላህ ዘንድ መወደድና የደረጃ ብልጫ የሚገኘው በአላህ ፍራቻ እና በመልካም ስራ ብቻ ነው። ድህነት ከትዕግስት፣ ከታታሪነት ፣ ጋር ውበት ነው፤ ሀብት ከምስጋናና ከልግስና ጋር በረከት ነው።

ቤትን የማስተዳደር ኃላፊነት በባል ትከሻ ላይ የወደቀ ነው ኃላፊነቱና ተጠያቂነቱ የርሱ ነው። ለቤተሰቡ የሚያወጣው ወጪ አቅሙ በፈቀደ መጠን ልክ ሊሆን ይገባዋል።

የቤት ወጭ ከብክነት እና ከንፍግነት የራቀ ሊሆን ይገባዋል። የቤት ውስጥ ስርዓት በአጠቃላይ ሚዛናዊነት ሊኖረው ያስፈልጋል።

ሚስት ቤት የማስተዳደር ኃላፊነት በመጀመሪያ ደረጃ እርሷን የሚመለከት ባይሆንም አላስፈላጊ ወጪዎች በመቀነስና ከአቅም በላይ የሆኑ የወጪ ጥያቄዎችን ባለማቅረብ ለባልዋ ድጋፍ ልታደርግ ይገባል። ባል ለቤት የሚጠብቀው ወጭ ከፍ ባለ ቁጥር ችግር ውስጥ ይገባል፤ እዳም ውስጥ ሊዘፈቅ ይችላል። ዕዳን መሸከም ደግሞ ድንጋይ እንደመሸከም ይከብዳል። ይህ ጥሩ ባህሪውን ሊቀይረው ይችላል።ተከታትሎም የቤቱን ሠላም ያናጋዋል።

ስርዓት ባለው መልኩ የቤት ወጪን በማውጣት እና በስስታምነት መካከል ያለውን ልዩነትን ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል። ሙስሊም ከስስት መራቅ አለበት ኢማን እና ስስታምነት በአንድ ልብ ውስጥ አይሠበሰቡም የቤት ወጭ እንደሁኔታው እንደቤተሰብ አባላት ብዛትና እንደ አካባቢው ከቤተሰብ ቤተሰብ ይለያያል። የቤት በጀትና ወጪ የቤተሰብን ብዛትና ሁኔታ እንዲሁም ፍላጎት ግንዛቤ ማስገባት አለበት።

የቤት ወጪ ስርዓት፣ ዐቅምን በትክክል ከማወቅ ይነሳል። ወጪዎች ዐቅምን ያገናዘቡ በዐቅም የተመጠኑ መሆን አለባቸው የወጪ ቅደም ተከተሉን በስርዓት ማስቀመጥም ያስፈልጋል። የቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶች ከቅንጦት እና ከትርፍ ወጪዎች ቅድሚያ ሊሠጣቸው ይገባል ያልተፈለጉና እቅድ ያልተያዘላቸው ወጭዎችን መጠንቀቅ የቤት በጀትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም አስፈላጊ ነው።

የቤተሰብ ፍላጎት በሚገባ ከተሸፈነ በኋላ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ ሊቀመጥ ይገባዋል ገንዘብ የማጠራቀም ልምድ በቤት ውስጥ ማዳበር ጠቃሚ ነው። ከግዜ በኋላ ድንገተኛ ነገሮች ሊከሰቱ ይህን የተጠራቀመ ገንዘብ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል።

የምግብ ፍጆታ

የብዙ ቤተሰቦች አብላጫ በጀት ለምግብ ፍጆታ ግዥዎች ይውላል የቤተሰብ የምግብ ፍጆታ ከግዥ ጀምሮ እስከ አጠቃቀም ያለው ሂደት ስርዓት ባለው መልኩ መከናወን አለበት የምግብ ብክነትና የምግብ እጥረት እንዳይኖር የቤት በጀትን በአግባቡ መከፋፈል ያስፈልጋል።

- ለምግብ ፍጆታ የሚገዙ እቃዎችን መግቦችን ዋጋና ጥራት በትክክል ማወቅ
- አማራጭ የፍጆታ እቃዎችን ማወቅ
- የፍጆታ እቃዎችን ግዢ በማስታወቂያ ጫና ብቻ አለመግዛት
- የሚያስፈልጉ እቃዎችን በሚያስፈልገው መጠን በአንድ ግዜ መሸመት
- የቤተሰብ ዐቅም የሚመጥኑ እቃዎችን መሸመት

6. የቤት ውስጥ ስነ - ምግባሮች

እዝነትን በቤት ውስጥ ማስፈን

ወንዶች / ባሎች በቤት ውስጥ እዝነትን/ መተዛዘንን ባህል ማድረግ መቻል አለባቸው የሙዕሚኖች እናት ዓኢሻ በዘገበችው ሐዲስ ረሡል (ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የሚከተለውን መናገራቸውን ተጠቅሳል። "አላህ ለአንድ ቤተሰብ መልካምን ሲፈቅድ በመካከላቸው መተዛዘንን ያሰፍናል።" ሐዲሱን ኢማም አህመድ ዘግበውታል።

ለባልና ሚስት መተዛዘን በጣም ጠቃሚ የስሜት ትስስር ይፈጥርላቸዋል። ውጤቱም በህይወታቸው ላይ ግሩም ተጽዕኖ ያስገኛል። በአምባገንነት ፣ በኃይል ቃል ትዕዛዝ በመስጠት ፣ በመጨቃጨቅና መተንፈሻ በማሳጣት ሊገኝ የማይችለውን በመተዛዘንና በመተሳሰብ ሐሳብን በመለወጥ ማግኘት ይቻላል። ለዚህም ነው ነብዩ (ሠላምና ሰላት በርሳቸው ላይ ይሁን) " አላህ እዝነትን ይወዳል ፤ ለኃያልና ለሌሎች ነገሮች የማይሠጠውን ለእዝነት /መተዛዘን/ ይሠጣል" በማለት የተናገሩት።

መተጋገዝ

ብዙ ወንዶች ባሎች የቤት ውስጥ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ይጠላሉ። ቀላል እቃ ማቀበልን ያህል ነገር ላይ እጃቸውን ማስገባት እንኳ ያንገሸግሻቸዋል፤ በቤት ስራ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግና የቤተሰብ አባላትን ማገዝ ደረጃቸውን ዝቅ እንደሚያደርገው የሚያስቡም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ይህ ስህተት መሆኑን ማመን ያስፈልጋል። በቤት ውስጥ ስራዎች ከቤተሰብ አባላት ጋር መተጋገዝ የመተሳሰብ አንድ ምልክት ነው። ወንዶች በዚህ ጉድ ላይ ለዓለማት እዝነት ነብይ (ሰላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) ተምሳሌታቸው አድርገው መውሠድ ይኖርባቸዋል።

ረሡል (የአላህ ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) በዚህ ጉዳይ ላይ እንዴት ነበሩ ?

ዓኢሻ (መልካም ስራዎቿን አላህ ይቀበላት) እንዲህ መልስ ትሰጣች።

"ቤተሠባቸውን በስራ ያግዙ ነበር ፤ የሠላት ወቅት ሲደርስ ለሠላት ከቤት ይወጣሉ። "

ይህ ሐዲስ ቡኻሪ በትክክለኛ የሐዲስ ስብስብ ስራዎች ውስጥ ዘግቦታል።

በቤት ውስጥ ለቤተሰብ በሚስት ስራ ድጋፍ ማድረግ ወንዶች ባሎች አስፈላጊ መሆኑን ከረሡል (ሠላምና ሠላት ይሁን) ህይወት ትምህርት መውሰድ ይኖርባቸው አንድ ባል ለሚስቱ የቤት ውስጥ ስራ ስላገዘ "ወንድነቱን " የሚፈታተን ምንም ዓይነት ስህተት አልፈጸመም። በዚህ አካባቢ ምንም ነውር የለም። የ "ወንድነት " ጥንካሬ በዚህ የሚለካ አይደለም።

ሚስት ባልዋ የቤት ውስጥ ስራዎችን ሲያግዛት ደስታ ይሠማታል። በመካከላቸው ያለው መተሳሰብም ይዳብራል። የመፈቃቀር ስሜትንም ያቀጣጥላል። በዚህ ላይ ባል ለሚስቱ ቤት ውስጥ ስራ እገዛ በማድረጉ የረሡልን (ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የህይወት ፈለግ (ሡና) ይከተላል። በዚህም የአላህን ውዴታ ያገኛል።

አንዳንድ ባል ቤት እግሩ በረገጠበት ቅጽበት ምግብ እንዲቀርብለት ይጠይቃል። ምናልባት ሚስቱ በልጆች እንክብካቤና በስራ ብዛት አስር ጉዳዩችን በአንድ ግዜ የምትሰራበትን አስር እጆች እንዲኖራት እየተመኘች ከወዲህ ወዳ እየተዋከበች ይሆናል። ምድጃው ላይ የተጣደ ሻይ አለ። ከርሱ አጠገብ ሌላ ምግብ እየበሰለ ነው። ከዚያኛው ክፍል ጡት የፈለገ የህጻን ልጇ ልቅሶ ድምጽ ይሠማል። ሌሎች ልጆች ደግሞ ቁርሳንና ትምህርት እንድታስጠናቸው ከእግሯ ስሮች እየተከተሉ በጥያቄ ያጠድፏታል።

በዚህ ሁኔታ ላይ ነው እንግዲህ ምግብ አሁን ካልቀረበልኝ በማለት ለመቆጣት መንደርደር የሚጀምረው ለአፍታ ያህል ራሱን ተቆጣጥሮ ምግብ እስኪቀርብለት መጠበቅ አልቻለ፤ ወይም ደግሞ ልጆቹን የማስጠናት ድርሻውን ለጥቂት ግዜያት ያህል እንኳ አልተረከበ ፣ ወይ የሚያለቅሰውን የራሱን ልጅ ሂዶ አላጫወተ ፣ እንዲያው ባለበት ተቀምጦ በዚያው ቅጽበት የጠየኩት ምግብ እንደ "መና" ከሠማይም ወርዶ ቢሆን ካልቀረበልኝ እዚህ ቤት አንድ ዓይነት የመተሳሰብ ችግር አለ ብሎ ይደመድማል ።

ለእርሱ በቅጽበት ምግብ ካልቀረበ ለዛውም በዚያ ሁሉ ወከባ መሀል አንድ ዓይነት የመተሳሰብ ችግር አለ። የሚስቱን ውክቢያ ምንም ከቁም ነገር ሳይቆጥር ምግብ በቅጽበት እንዲቀርብለት መጠየቁ ሳያንስ ለሚስቱ ምንም ዓይነት የማገዝ መልክት ሳያሳይ እጅና እግሩን አጣጥፎ መቀመጡ ደግሞ የመተሳሰብ ችግር አይደለም ። የሚያስቅም ፤ የሚያስለቅስም ድምዳሜ ነው። ባሎች ከዚህ ዓይነት ባህሪ ራሳቸውን ሊያርቁና በቤትም ከቤት ውጭም የረሱልን (ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) የሕይወት ፈለግ ሊተገበሩ ይገባል።



ቤተሰባዊ ጉዳይ

በሁለተኛ ጋብቻ ዙርያ የተደቀኑ እንቅፋቶች

ሁለተኛ፣ ሶስተኛም ሆነ አራተኛ ሚስት ለማግባት የቀድሞ ሚስትን ማሳወቅ ወይም ማስፈቀድ የጋብቻው የግዴታ መስፈርት ነውን ????

ይህ ሀሳብ ወይም መጠይቅ የበርካታ ሙስሊሞች የልብ ትርታ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው። ይህም አንዳንድ እንስቶች ባሎቻቸው ሌላ ሚስት ሲደርቡባቸው የራሳቸውን የትዳር ህይወት ጨምሮ አዲሱንም ጎጆ የማወክ ተግባር በመፈፀም የብዙሃኑን ትኩረት በመሳብ ላይ ተገኝተዋልና።

ሆኖም አንድ ሙስሊም ግለሰብ ተጨማሪ ሚስት ከማግባቱ በስተፊት የመጀመሪያዋን ሚስቱን ማስፈቀድ ግድ አይሆንበትም። ይህንን እንደ ግዴታ የሚመለከት ካለ ማስረጃውን እንዲያቀርብ ይገደዳል። ምክንያቱም ኢስላማዊው ሸሪዓ ለጋብቻ ካስቀመጣቸው መስፈርቶች ውስጥ የመጀመሪያ ሚስቱን ያስፈቅድ የሚል ደንብ አልተጠቀሰበትምና። አንድ ሙስሊም በቀዳሚዋ ሚስቱ ላይ ሌላ ለመጨመር የሚያስችለው በቂና ጤናማ ምክንያት እስካለው ድረስ ሚስቱን ሆነ ቤተሰቦቹን ቀድሞ ማሳወቁ ሸርጥ ወይም መስፈርት ነው ያለ ሊቅ አይታወቅም። ነገር ግን ለቀድሞውም ሆነ አዲስ ለሚመሰርተው ትዳሩ ጤናማነትና ከቤተሰቦቹም ሆነ ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ትስስር እንዳይጎዳበት ድብብቆሹን ቢተወው መልካም ነው ይላሉ ምሁራን። ሆኖም ግሃድ ማድረጉ አዲሱንም ሆነ ነባሩን ትዳሩን እንደሚጎዳበት ባብዛኛው የታመነበት ከሆነበትና ለመላው ቤተሰቡና ለሚመራው ህይወት ደህንነት ሲል ቢሸሸግ ኢን ሻአ አላህ አይጎዳም።

ከኒካህ ሸርጦች ዋነኛው የሴቷ ወሊይ በግልፅ አውቆ መፍቀዱ ሲሆን በምስክሮች ፊት በይፋ መፈፀሙ ደግሞ ተከታዩ ነው። በዚህም መሰረት ትዳሩን ልደብቀው ቢል እንኳ በአጭር ግዜ ውስጥ ወይም ገና ከጥንስሱ ለውዱ ባለቤቱም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ሊደርስ ይችላል። ባንደበቱ ያላሳወቀውን በሃሜት ተሸካሚዎች በኩል ቤቱን ማሳመሱ የማይቀር ይሆንበታል። በዚህም ሰበብ ላላስፈላጊ ሀሜት፣ ግጭትና የኑሮ መናጋት ሊጋፈጥ እንደሚችልም ሊገምት ይገባዋል። በራሱ በኩል ብታውቅና ምላሿም ሆነ አፀፋዋ እስከምን እንደሆነ በይፋ ማወቁ ራሱ ለመፍትሄው መዘጋጀትን ያፈራ ይሆናል። ሆኖም ይህ አካሄድ የሚመረጠው ከባለቤቱ ግንዛቤና ሁኔታ አንፃር ለጉዳዩ የሚኖራትን ምላሽ በመገመት ይሆናል።

↪የመጀመርያው ሳንካ

የቀዳሚ ሚስቶች ተቃውሞ ሲሆን በዚህ አካሄዳቸው በርካታ ጥፋትን አስከትለዋል። ከዚህ ስጋት የተነሳም ደፍረው ወደ ጋብቻው የተጓዙ ባሎች እንኳን ነገሩን በድብብቆሽ ይጀምሩታል።

ደርቦ ማግባትን በተመለከተ ሚስቶች የመፍቀድም ሆነ የመከልከል ስልጣን ባይኖራቸውም በመልካም አብሮ መኗኗር የትዳር ዋነኛው ተፈላጊ መርህ በመሆኑ ያንን ሊጎዱ ከሚችሉ ውሸንብሮች ለመራቅም ሲባል ጭውውቱን በይፋ ማድረጉ ለባል የውስጥ ለውስጥ ጦርነቶችን ይቀንስለታል። ቀድሞ በይፋ እንዳያሳውቅ ከሚያደርጉት ምክኒያቶች ዋነኛው ግን ብዙሀኑ ሴቶች ለጉዳዩ ያላቸው አሉታዊ ምልከታ ነው።

እንደሚታወቀው አላህ በእዝነቱ ልቦናቸውን ያቀናላቸው እንስቶች ሲቀሩ አብዛኞቹ ሴቶች ባላቸው ሌላ ሴት መደረቡን መቀበል ይከብዳቸዋል። ይኸ ደግሞ የምቀኝነትና የአልጠግብ ባይነት ውጤት ብቻ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው። ምክንያቱም የራሳቸውን ለራሳቸው ብቻ እንዲሆን መመኘታቸው ፈጣሪያችን አላህ በነሱ ውስጥ የፈጠረው ጤናማ ስሜትና እውነታ ነውና። የሚያወቃቅሰው ተከናኝ ነገር ይህንን ፍላጎታቸውን ለማሳካት ሲሉ ከመብታቸውና ከሸሪዓዊ መፍትሄዎች በላይ መራመዳቸው ብቻ ነው።

↪ሁለተኛው ሳንካ

የባሎች በቀዳሚዋ ሚስቶቻቸው አያያዝ ላይ ስህተት ላይ መዘፈቅና ሁለተኛዋን ሲያፈላልጉም ሸሪዓዊ ባልሆነ መንገድ የመንቀሳቀሳቸው ጉዳይ ነው።

እርግጥ ነው በዘመናችን በያቅጣጫው የምናስተውለውን የባሎች በዳይነትና ቀድመው ያገቧቸውን ሚስቶች እርግፍ የማድረግ፣ በችግር ግዜ ከመድከም አልፋ የሞተችለትን በተመቸው ግዜ የመዘንጋት እውነታ እንዲሁም በአላስፈላጊ የኢኽቲላጥና የኸልዋ በሽታ በመጠቃት ክብረቢስ በሆነ መንገድ ለሌላ ጋብቻ መንደርደር በቀዳሚዎቹ ሚስቶች በኩል ጉዳዩ ተቀባይነት እንዳያገኝ እና ብሎም እንዲከነን ምክኒያት ይሆናል። ይህ ጥፋት በአላህ ዘንድም ባሎች በዱንያም በኣኺራም የሚያዋርዳቸው ርካሽ ተግባር መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል።

ሸሪዓዊ ድንበሮችን መጣስ ውጤቱ የከፋ ነውና !!

እንደሚታወቀው ለየትኛውም ስርዓታችን መመርያዎችንና የአፈፃፀም ደንቦቹን የምንቀስመውና በአርኣያነት የምንከተለው ከፈጣሪያችን ወደኛ ከተላኩልን መልእክተኛው ሰለላህ አለይሂ ወሰለም ነው። እሳቸውም ከአምልኮ ስርኣትና ህግጋት ጀምሮ የማህበራዊ ኑሮ ስርኣቶችን እስከ ግላዊ የህይወት መርሆቻችን ሁሉ ምንም ሳያስቀሩ በአንደበታቸውም በተግባራቸውም መክረውናል። የሚያፀድቁትን በማፅደቅ የሚወገዝውንም በማውገዝ አስተምረውናል። ከነዚህም መካከል የትዳር ህይወት ዋነኛው የዱኒያ ላይ መጠቃቀሚያችን ነው።

በዚህ የህይወት መስክ ነቢዩ ሰለላህ አለይሂ ወሰለም ከአንድ በላይ አግብተው ነበር። በዚህም ሂደት ውስጥ ከውዶቹ ባለቤቶታቸው መካከል አንዳቸውንም ማስፈቀዳቸው አልተዘገበም። ልክ እንደዚያው የሳቸው ባልደረቦችም ረዲየላሁ ዐንሁም ከአንድ በላይ አግብተው ነበርና ሚስቶች ነበሯቸው። ይሁንና ከመካከላቸው አንዳቸውም ፍቃድ የጠየቋቸው አልነበሩም። ይህ እንግዲህ ተጨማሪ ሚስት ለማግባት የመጀመሪያዋን ሚስት ማስፈቀድ ግድ አይደለም ለሚለው በቂ የሆነ ሸሪዓዊ መነሻ ነው። ምክንያቱም ይህ ቀድሞውንም የሚስቶች መብት አልነበረምና ላለማስፈቀዱም የመብት ጥሰት አይሆንም።

ይህንኑ ርዕስ በተመለከተ የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ 19/53

"ተጨማሪ ሚስት ለማግባት የመጀመሪያዋ ሚስቱን ይሁንታ ማግኘት ግድ ነው ወይ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት በሰጠው ምላሽ ﷺ «ባል ሁለተኛ ሚስት ለማግባት ካስፈለገው የመጀመሪያ ሚስቱን ውዴታ ማግኘት ግዴታ አይሆንበትም። ነገር ግን እንደ ጥሩ ስነምግባርና በመልካም ሁኔታ ከመኗኗር አንፃር የእንስቶችን ተፈጥሯዊ ስሜት ላለመጉዳትና በዚህ ጉዳይ የሚሰማትን ህመም ለማቅለል ሲል ቢያሳውቃትና ልቦናዋን በመንከባከብ ቢያረጋጋው መልካም ነው። ለዚህም ሲባል ፊቱን ፈታ አድርጎ፣ በመልካም ግንኙነትና በጥሩ አነጋገር እንዲሁም ይህንን ፍላጎቱን የሚያሳካ ከሆነ በአቅሙ ልክ ከገንዘቡም ስጦታ ቢያበረክትላት መልካም ይሆናል።» በማለት መክሯል። (ፈታዋ አል ' ለጅናህ አድ ' ዳኢማህ 19/53)

የመልካም አስተዳዳሪነት ባህሪን መላበስ ክብር ነው !

ለቤቱ የሚቆረቆር ባል ሁለተኛ ሚስት ከማግባቱ በፊት በቅድሚያ ለመጀመሪያ ሚስቱ ቢነግራትና ለማስማማት ቢጥር ተገቢ ይሆናል። ይህም ጥሩ የሆነ ጥቅምን ያስገኝለታል። የሚገባበት አዲሱ ትዳርም ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ከአዲሷ ባለቤቱም ጋር በሰላም ትኖርለት ዘንድ ያግዘዋል። እንዲህ ሲባል ግን ግዴታ ነው ለማለት አይደለም።

ከክፍለ ዘመኑ ታላላቅ ፈቂሆች መካከል አል አልላማህ ሸይኽ ኢብኑ ዑሰይሚን ረሂመሁላህ "አንድ ሰው ሌላ ሚስት ለማግባት ሲነሳ የመጀመርያ ሚስቱን ማስፈቀዱ እንደመስፈርት ይደረግበታልን? ሳያሳውቃት ቢያገባስ ብያኔው ምንድነው?" ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ፤

«ፍቃድ ቢጠይቃት ማግባቱን እምቢየው ትለዋለች የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን ቀዳሚዋን ሚስት ፈቃድ መጠየቅ የጋብቻ ሸርጥ አይደለምና ጠይቋት እንኳን እምቢ አልፈቅድም ብትለው የማግባት መብት አለው። ከዚሁ ጋር ግን እኔ እንደሚታየኝ እሷኑ ማማከር እንዳለበትና ነገሩን አምናበት እስክትቀበለውም ቢያግባባት፣ ስለምን ይህንን ጋብቻ እንደፈለገም ቢያብራራላት መልካም ነው። በዚህ ሂደት አዲሷ ሚስቱ ብትመጣባት እንኳ የቀድሞዋ ራሷን ባረጋጋችበትና የምታውቀው ጉዳይ እንዲሁም የወደደችው ስለሚሆን ሁለቱም ሚስቶች ባለ መኮራረፍና ባለ መጠላላት ምስጉን የሆነ ጥሩ ኑሮን ይኖሩ ይሆናልና የዚህ አይነቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል የቀድሞዋን ማስፈቀዱና ቀድሞ መንገሩ ተገቢ ነገር ነው። ይሁንና ይህ ጉዳይ ግዴታ ነው ወይ ከተባለ ግዴታ አይደለም።» ሲሉ አብራርተዋል።

በተጨማሪም "ይህንን ጋብቻ ቢደብቃትስ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው «ምንም ችግር የለበትም» በማለት መልሰዋል።

(ፈታዋ ኑሩን አለድ ' ደርብ ሊኢብኒ ዑሰይሚን)



ቤተሰባዊ ጉዳይ

↪ሶስተኛው ሳንካ

የፀረ ኢስላም ሀይሎች የሚዲያ ዘመቻና የማህበረሰቡ አግባብነት ያጣ ጣልቃ ገብነት

በመሰረቱ ኢስላምን በበጎ እይታ የማይመለከቱ ሀይሎች ስለ ኢስላማዊ ህግጋትና የአኗኗር ስርዓት በአግባቡ ይረዳሉም ይመለከታሉም ተብሎ አይጠበቅም። ልዩነታችን ከመሰረታዊው የእምነታችን ርዕስ ከአሃዳዊው የአምልኮ ስርአት ጀምሮ የማይገናኝ በመሆኑ በሌሎች የአኗኗር ዘይቤያችን ላይ የሚሰነዘሩት አስተያየት ሆነ የሚያራምዱት አቋም በአብዛኛው አፍራሽ ነው። ስለዚህም ለዚህ ርዕስ የሚሰጡትን የመፍትሄ አቅጣጫ የማንጋራው ብሎም የምንቃወመው ነው።

እንደ ምሳሌነት በሀገራችን ያለውን የሚዲያ ሽፋንና ከተለያዩ ተቋማት የሚሰነዘሩትን ውግዘቶች እንዲሁም ለሴቶች በሚል የተቀመጡትን ደንቦች ካስተዋልን በቀጥታ ሃይማኖታዊ ስርዓታችንን ለማጣጣል የሚደረጉ ፍልሚያዎች መሆናቸውን እንረዳለን። ከአንድ በላይ ያገባ እንዲታሰር፣ ሚስት ተስማምታ እንዳትኖርና ከስ እንድትመሰርት እንዲሁም ንብረት እንድትካፈልና ወደ ወዘተ ግፊት ይደረጋል።

በማህበረሰቡም በኩል በአንዳንድ ኢስላምን ባማባቡ ባልተረዱ ሙስሊሞችም ሆነ በሌሎች አዛኝ ቅቤ አንጓቾች የሚደረገው አጉል የሆነ ጣልቃ ገብነት ለዚህ የትዳር ስርአት ክፉ እንቅፋት ሆኗል። በተለይ ሙስሊሙ ከልብ ሊረዳው የሚገባው በባልና ሚስት መካከል በመግባት አመፅን ማነሳሳት፣ የሚስትን ልቦና ማስሸፈት የተረገመና ከመልእክተኛው ጎዳና ያፈነገጠ መስመር መሆኑን ሊያስተውል ይገባል።

የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም *«ሚስትን በባሏ ላይ ያሳመፀ ከኛ አይደለም።»* ማለታቸው በአቡዳዉድ (2175) ተዘግቦ አል አልባኒይ ሰሂህ ብለውታል ። በሌላ የአቡ ዳዉድ (5170) ዘገባም የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም *«የአንድን ግለሰብ ሚስት ወይም ሰራተኛ (አገልጋይ) ያሰሸፈተ ከኛ አይደለም።»* ብለዋል። ይህንንም አል አልባኒይ ሰሂህ ብለውታል።

በሌላ በኩል ባል ይህንን የመሰለ ግዙፍ ጉዳይ ከሚስቱ መደበቁ ታማኝነቱና እውነተኝነቱ ላይ ጥያቄ አይፈጥርበትም ወይ ሊባል ይችል ይሆናል። ለዚህ ምላሽ የሚሆነው ባል የመጀመርያ ሚስቱ የዚህ አይነቱን ዜና ቀድማ ብትሰማ ጋብቻውን እንደማትቀበልና የትዳሩንም ህልውና ስጋት ውስጥ እንደሚጥል ስለሚያውቅ ሊሆን ይችላል። የዚህ አይነቱን ሽሪዓዊ ብይንና ስርዓት የሚቃወሙ የጥፋት ሚዲያ ሰለባዎች በአቅራቢያዋ መብዛታቸው ትዳሯን እንድታናጋ ሊጋብዛት ይችላልና። ባል ገና ለሷ ከማሳወቁ ከሃዲና ቃሉን የማይጠብቅላት በዳይ እንደሆነ አድርጎ በመተርጎት ይህ ማህበረሰብ ግፊት ይፈጥርባታል። ከዚያም የከፋ የሀሰት ወቀሳዎችን በመለጠፍ ከጅምሩ ህይወቱን ያናጉበታል።

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ ረሂመሁላህ በመጅሙዕ አልፈታዋ (23/363) *«የአንድ ሰው በባልና ሚስት መሃል ጉብቶ ለማለያየት መጣር ከባድ የሆነ ኃጢኣትና የድግምተኞች ተግባር አይነትም ነው። ይህም ትልቁ የሸይጣናት ስራ ነውና።»* ብለዋል።

ሸይኽ ሷሊህ አልፈውዛንም ሀፊዘሁላህ *«ሚስትን በባሏ ላይ ያበላሸ (ስርአት አልበኛ ያደረጋት፣ በባሏ ላይ እንድታምፅ ያመቻቻት) የተረገመ ነው።»* የሚል ሐዲስ ስላለ የሚስት ቤተሰቦችም ቢሆኑ በባልና ሚስት መካከል ያለውን ችግር ፈትቶ ለማስታረቅ መጣር ግዴታ ይሆንባቸዋል። ይህም ለሷም ለነሱም ጠቃሚው ነውና። ብለዋል። (አልሙንተቃ ሚን ፈታዋ አሸሸይኽ ፈውዛን (3/248-249)

አርግጥ ጣልቃ ገቦችን ወደዳር ለማውጣት እንዲረዳው ወንድ ልጅ ሁለተኛ ሚስት ሲያገባ የቀድሞ ሚስቱን ለማሳመን እና ስነልቦናዋን ላለመጉዳት የሚጠቅሙ በርካታ የስነልቦና ባለሙያዎች ምክሮች አሉና በዚያም በመታገዝ ሊያረግባት ይገባል።

ሙእሚን የሆነች ሴትም ባሏ ሁለተኛ ሚስት ያገባበት ምክኒያት ምንም ይሁን ምን ጫና መፍጠርና ከኔና ከሷ ምረጥ በማለት እንዲፈታት ልትጠይቅና ማስጠንቀቅያም ልትሰጥ አይገባትም። ይህን መጠየቋ ፍፁም የሆነ ስህተት ነው። እንደውም ሁለተኛዋን ሚስት እንዲፈታት መጠየቋ ትልቅ ወንጀል ነው። ይህንንም የአላህ መልእክተኛ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዲህ በማለት አስጠንቅቀዋል።

☞ *«አንዲት ሙስሊም ሴት እህቷ (ሌላኛዋ ሚስት) እንድትፈታ መጠየቅ አይገባትም። ለሷም ከአላህ የተመሰነላት አለላትና።»* ብለዋል። ይህም በቡኻሪ (4857)ና በሙስሊም (1413) የተዘገበ ሲሆን፤

«የትኛዋም እንስት ምንም ችግር በሌለበት (ለፍቺ በማያበቃ ሁኔታ) ባሏን ፍቺ ከጠየቀች የጀነት ሽታ ሃራም ይሆንባታል።» ማለታቸው ደግሞ በቲርሚዚይ (1187) በአቢዳዉድ (2226) እና በኢብኑ ማጃህ (2055) ተዘግቦ አል አልባኒም በሰሂህ አቢዳዉድ ላይ ሰሂህ ብለውታል።

እንደሚታወቀው የባሏ በሷ ላይ ሌላ ሚስት መደረብ ብቻውን ለፍቺ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም። ሴቶቹ ይህንን ማስጠንቀቅያ ባለማወቃቸው ወይም ባለማስተዋላቸው ስህተት ውስጥ ይዘፈቃሉ። ብዙውን ግዜ ባል ለመጀመርያ ሚስቱ ለተጨማሪ ጋብቻ መሰናዳቱን ቀድሞ ባሳወቀ ቁጥር ለቤቱ መናጋት ብሎም ለትዳር መፍረስና ለልጆች መበተን ሰበብ እንደሚሆንም ተስተውሏል። በዚህም ሰበብ ቤተሰቡን ከመናጋት ለመጠበቅ ሲል ቀድሞ ከማሳወቅ ሲታቀብም ይታያል።

የዚህ ድብብቆሽ ዋነኛው ምክንያት ይህንን አምላካዊ ህገ - ብያኔ የሚቃረነው ማህበረሰብ በትዳሩ ውስጥ እጁን በአሉታዊ መልኩ ማስገባቱ መሆኑን እንዳወሳነው ሁሉ መጥፎ ተፅዕኖውን ለመጠቆም ያህል አንዳንዷ ሚስት ባሏ በግልፅ ጋብቻ ከሚደርብባት ይልቅ ያለ ጋብቻ በድብቅ ከባዕድ ሴት ጋር ሃራም የሆነ ጉድኝት ፈጥሮ ቢኖር የምትመርጥ ትኖራለች።

ስለዚህም ባሎቻቸው ሲያገቡባቸው ቤታቸውን በአንድ እግር ከማቆምም አልፈው እስከመፋታት ሲደርሱ፤ ባሎቻቸው ባልገው ሲገኙ ግን በቀላል ሽምግልና ወይም ተቃውሞ ያልፋታል። አንዳንዴም እያወቁ እንዳላወቁ ሆነው ያሳልፋታል። ይህ ደግሞ የተነባበረ ድንቁርና ሲሆን ለባሎችም ሁለተኛ ትዳራቸውን መደበቅ ትልቁ ምክንያት እየሆነ ይገኛል። በዚህ የተነሳ ተጨባጩን ሁኔታውን በማመዛዘን ለቀድሞው ትዳሩ፣ ለልጆቹና ለቤቱ ሰላምና ጠቀሜታ በማሰብ ደብቋት ቢያገባ ያስነውራልን ??? ባል የቤቱ አውራ መሪ ስለሆነ ለትዳሩ ጠቃሚና ጎጂ ሂደቶችን መርምሮ መራመድ ግድ ይለዋል።

ሆነም ቀረ ሚስት ከመብቷና ከሃላፊነቷ ቀድማ እኔ ካልፈቀድኩ እበጠብጣለሁ ወይ መፈታት እፈልጋለሁ ወይ ደግሞ ያገባትን ይፍታ በሚል ዘራፍ ብትል በዱንያም በኣኪራም መጥፎ ይሆናል። እርግጥ ነው የሚወዱትን፣ የሚፈልጉትንና ለማካፈል የሚሳሱለትን ለሌሎች ባለመብቶችም ማካፈል ትልቅ ሰደቃና ከአላህ የሚገኘውን ወረታ የማስቀደም ውጤት መሆኑንም ልብ ማለት ይገባል።

በጣም የሚያስገርመው ብዙ ሴቶች ለሁለተኛ ሚስትነት ወይም ለሶስተኛነት ወይም ለአራተኛነት የጋብቻ ጥያቄ ሲቀርብላቸው ለትዳር ካላቸው ጉጉት የተነሳ በመልካም ፈቃደኝነት ይስማማሉ። እውነታውን ስናስተውለው ሚስት እንዳለው እያወቁ ትዳሩን ይቀበላሉ፤ ይደረባሉም። ከነሱ በኋላ ሲያገባባቸው ግን ከኔ በኋላ ማንም እንዳይሰለፍ በሚል ፈሊጥ እሳት ይገርሳሉ።

ውድ እህቴ! በዚህ አጋጣሚ ልምከርሽና፤ በመልካም አያያዝ የሚያስተዳድርሽና የሚንከባከብሽ ባል እስከሆነ ድረስ ሁለተኛ ሆነሽ ስትደረቢ እንዳስተዋልሽ ሁሉ ሲደረብብሽም አስተውዪ እላለሁ።

እንደሚታወቀው በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ውሽማ፣ የሚስጥር ፍቅረኛ፣ የጭንገረድ የመሳሰሉት ባህሎች ፀያፍ የዝሙት ህይወት በመሆናቸው ቦታ የለቸውም። ከምንም በላይ ወደር በሌለው መልኩ ስለ ፍጡራኑ ፍላጎትና ጥቅም የሚያውቀው ፈጣሪ አምላካችን አላህ በደነገገልን ህገ ደንብ መሰረት አንድም ሁለትም ሶስትም አራትም በስርዓቱ ማግባት የሙስሊም ወንዶች መብት ነውና ሚስቱን ደብቆም ሆነ በግልፅ አሳውቆ እንደ ተጨባጩ ለመስለሃ ማግባቱ ያስመሰግነዋል እንጂ አያስወቅሰውም። የያንዳንዱ ባልና ሚስት እንዲሁም አካባቢና ማህበረሰብ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት የላጤዎችንም ቁጥር ለመቀነስ መጣጣር ብልህነት ይሆናል!!

ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ከአንድ በላይ የማግባቱ መፈቀድ ዋነኛው ፋኢዳ ላላገቡት እንስቶች የትዳር እድልን ለመፍጠር፣ አምሮትንና ከሴቶች ይልቅ ለረዥም አመታት የሚቆየውን የወንዶች ፍላጎት በህላል ለመግታት፣ ዝርያን ለማብዛት፣ ቤተሰብን ለማስፋት፣ ዝሙትን ለመቀነስ፣ ዘርን ለመጠበቅ እና ለመሳሰሉት ሲሆን ሃላፊነት በጎደለው መልኩ ለተጨማሪ ጋብቻ በመንደርደር አዲስ ጎጆ በመሰረቱ ማግስት ነባሩን መናድ እንዲሁም ወዳዲሷ በማዘንበል ቀዳሚዋን መበደል ወይም የቀድሞ ሚስቱን ጫና ባለመታገስ አዲሷን መበደል እና የመሳሰሉት ሁለተኛ የማግባትን መብት መጠቀም ሳይሆን ህጉን ለሚፃረሩት ፈንጂ ማቀበል በመሆኑ አቶ ባልም ይጠንቀቁ እላለሁ!!!አላህ መብታችንን በስርዓቱ የምንጠቀምበትና ግዴታችንንም በአግባቡ የምንወጣ ያድርገን።

☞ በመጨረሻም፤ ሁለት ሴቶችን በአንድ ግዜ ስለማግባት ከተጠየቀ፤

ከአንድ በላይ እስከ አራት ማግባት መስፈርቶቹ እስከተሟሉ ድረስ ችግር የለውም። ይህም በቁርአን አላህ የፈቀደው ነው።

فَانْكِحُوا مَا طَابَ لَكُمْ مِنَ النِّسَاءِ مَثْنَىٰ وَثُلَاثَ وَرُبَاعَ

ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሦስት ሦስትም አራት አራትም አግቡ።» ኒሳእ 3

ከሁለት ሴቶች ጋር በአንድ ቀን ኒካህ በማሰር ጋብቻ መፈፀምን በተመለከተም በአንድ ቀን መሆኑን የሚከለክል ነገር የለም። ከላይ የተመለከትነው ፍቃድ የጊዜ ገደብ የለውም። ሆኖም የሁለቱን ሰርግና ጫጉላ በአንድ ቀን ማድረግ እንደማይገባ የፊቅህ ልሂቃን አሳስበዋል። ይህም የአንዷን ሀቅ በመሙላት የሌላዋ ስለሚጎደል ነው።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

የጥቢ ዝምድና (ረደዓህ) እና መስፈርቶቹ

ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ ሰላምና እዝነት በመልዕክተኛው፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

ሙስሊም የሆነ ሰው ኢስላማዊ ህጎችን ማወቅና መረዳት እንዲሁም መውደድ አለበት፤ አምላካችን አላህ ጥበበኛ ነውና ለእኛ የበለጠ የሚበጀውን ያውቃል። እንደ ኢስላም፤ ከአንድ እናት ጡት የጠቡ የተለያዩ ሰዎችን የሚያስተሳስር ዝምድና አለ። ይህ ዝምድምናም የስጋ ዝምድና እንደሚከለክለው ከጋብቻ ይከለክላል። የጥቢ ዝምድና እና ትስስርን ተከትለው የሚከሰቱ ተያያዥ ፈቃዶች እና ክልከላዎች ስላሉ ህግጋቱ መታወቃቸው ግድ ይሆናል። ህግጋቱ ባልታወቁበት ሁኔታ ሊፈጠሩ የሚችሉትን ቤተሰባዊና ማህበራዊ ቀውሶች ማስተዋል አይከብድም። የጥቢ ዝምድና ድንጋጌ በቁርአን በሱና የተረጋገጠ ከመሆኑም ባሻገር በሙስሊም ሊቃውንትም አጠቃላይ ስምምነት ኢጅማዕ የተደገፈ ነው። አላህ ለጋብቻ እርም የሆኑብንን ሴቶች ሲዘረዝር እንዲህ ብሏል፤

(وَأُمَّهَاتُكُمُ اللَّاتِي أَرْضَعْنَكُمْ وَأَخَوَاتُكُمْ مِنَ الرَّضَاعَةِ) [النساء: 23].

«እነዚያ ጡት ያጠቧችሁ እናቶቻችሁ፣ የጥቢ እህቶቻችሁም..» ኒሳዕ 23

በሌላ አንቀጽ እንዲህ ብሏል፤

(وَإِنْ تَعَاسَرْتُمْ فَسَتُرْضِعُ لَهُ أُخْرَى) [الطلاق: 6].

«ለእናንተም (ልጆቻችሁን) ቢያጠቡላችሁ ምንዳዎቻቸውን ስጧቸው። በመካከላችሁም በመልካም ነገር ተመካከሩ። ብትቸገገሩም ለእርሱ ሌላ (ሴት) ታጠባለታለች።» አጦላቅ 6

በሌላም አንቀጽ እንዲህ ብሏል፤

(وَإِنْ أَرَدْتُمْ أَنْ تَسْتَرْضِعُوا أَوْلَادَكُمْ فَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ) [البقرة: 233].

«ልጆቻችሁንም ለሌሎች አጥቢዎች ማስጠባትን ብትፈልጉ ልትሰጡ የሻችሁትን በመልካም ኹኔታ በሰጣችሁ ጊዜ (በማስጠባታችሁ) በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም።» አልበቀራህ 233

የማጥባት ትስስር ህግ አላህ ያዘዘውና የደነገገው ለመሆኑ እነዚህ በቂና ግልጽ ቁርአናዊ ማስረጃዎች ናቸው። በተመሳሳይ መልኩም ግልጽ የሆኑ ሀዲሳዊ መረጃዎችን እናገኛለን።

عن عائشة –ﷺ– أن عمها من الرضاعة يسمى أفلح استأذن عليها فحجبته فأخبرت رسول الله – ﷺ – فقال لها: "لا تحتجبي منه فإنه يحرم من الرضاعة ما يحرم من النسب" رواه البخاري ومسلمٌ

የምእመናን እናት አዒሻ ባስተላለፈችው ሀዲስ አፍለህ የተባለ በማጥባት አንቷ የሆነ ሰው ለመጣባት አስፈቀደና ተከለለችው፤ ይህንን ለመልዕክተኛው ስትነግራቸው "ከእርሱ አትከለይ፤ ምክንይቱም በዝምድና እርም የሆነ በጥቢም እርም ይሆናል" አሏት። ሀዲሱ በቡኻሪ ቁጥር (4941) እና በሙስሊም (1445) ተዘግቧል

عن ابن عباس رضي الله عنهما قال: قال رسول الله - صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ - في بنت حمزة: (إنها لا تحل لي، إنها ابنة أخي من الرضاعة، ويحرم من الرضاعة ما يحرم من الرحم) رواه البخاري ومسلم

ዓሊይ አቢ አቢጣሊብ የህምዛን ልጅ እንዲያገቡ የአላህ መልዕክተኛን ሲጠይቃቸው፤ **«እርሷ አትፈቀድልኝም! እርሷ የጥቢ ወንድሜ ልጅ ናት፤ በዝምድና እርም የሆነው በጥቢም እርም ይሆናል»** በማለት መለሱለት። በቡኻሪ ቁጥር (5100) እና ሙስሊም (1447) ከኢብኑ አባስ ተዘግቧል።

በጥቅሉ **"በዝምድና ምክንያት እርም የሆነ በጥቢም እርም ይሆናል"** የሚለው የመልዕክተኛው ንግግር ከምእመናን እናት አዒሻ፣ ከአሊይ፣ ከኢብኑ አባስ እና ከሌሎችም ተዘግቧል። ስለዚህም የማጥባት ትስስር፤ ጋብቻን ከመከልከልና እርም ከማድረግ፣ እይታን ልቅ ከማድረግ እንዲሁም ከሴቷ ጋር ለብቻ ከመገለል አንፃር ተፅእኖ እንዳለው ኡለማዎች ሁሉ ተስማምተውበታል።

የሙስሊም ሊቃውንትም አጠቃላይ ስምምነት ኢጅማዕ ያለበት ስለመሆኑ በርካታ የፊቅህ አዋቂዎች ያጸደቁት ሲሆን፤ ኢብኑል ሙንዚር፣ ኢብኑ ሀዝም እና ሙወፈቅ ኢብኑ ቁዳማህ ይገኙበታል።
(አል ኢጅማዕ ገጽ 77 ፣ መራቲበል ኢጅማዕ ገጽ 67 አልሙግኒ 9/191 ይመልከቱ)

የጥቢ ዝምድና ብይንና ተጽዕኖ

የጥቢ ዝምድና ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የዘር ዝምድና ያለውን ብይን ይጋራል። ማለትም የጥቢ ዝምድና ጋብቻን ከመከልከል፣ መህረም ከመሆን፣ ለብቻ ከመገለል እና ሴትን ከማየት አንጻር ተጽዕኖ አለው። የጥቢ ዝምድና የቅርብ ዘመድ ከማድረጉ ባሻገር ለጋብቻ እርምነትንም ጽኑ ያደርጋል። በስጋ ዝምድና አንድ ወንድ ልጅ በእናቱ ምክንያት ለጋብቻ እርም የሚሆኑበት የእናቱ ቤተሰብ የሆኑ ሴቶች ሁሉ በማጥባት ዝምድናም እርም ይሆኑበታል። የጥቢ ዝምድና በአብዛኛው አጥቢዋ ሴት በማጥባቷ ምክንያት የምታገኘውን እናትነት መሰረት አድርጎ የሚከሰት ዝምድና እና ትስስር ነው። ዝምድናው በአብዛኛው በአጥቢዋ በኩል እንጂ በጠቢው ህጻን በኩል የሚሰራጭ አይደለም። የሚጠባው ህጻን አድጎ ልጆች ካፈራ አጥቢዋ ለልጆቹ አያት ከመሆንዋ በቀር ዘመዶቹን እና ዘመዶቿን ሁሉ አያስተሳስርም። ይህ በመጥባት ዝምድና ዙርያ ብዙዎች የሚስቱት መሰረታዊ መነሻ ነው።

የጥቢ ዝምድና ፍቃዶች እና ክልከላዎች

የጥቢ ዝምድና ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ሁለት አይነት ትጽዕኖዎችን ይፈጥራል።

ክልከላ፦ አላህ ለጋብቻ እርም የሆኑብንን ሴቶች ሲዘረዝር እንዲህ ብሏል፤

«እነዚያ ጡት ያጠቧችሁ እናቶቻችሁ፣ የጥቢ እህቶቻችሁም...» ኒሳዕ 23

በዚህና **"በዝምድና ምክንያት እርም የሆነ በጥቢም እርም ይሆናል"** በሚለው የመልዕክተኛው ንግግር መሰረት የስጋ ዝምድና ክልክል የሚያደርገውን ሁሉ የጥቢ ዝምድናም እርም ያደርጋል። ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው አጥቢ ሴት ልክ እንደ እናት ትቀጠራለች፤ ክልከላው መሰረት የሚያደርገዉም እሷን ነው። ስለዚህም እሷ ላጠባችው ልጅ እሷና በስጋ ዝምድና ምክንያትከእናቱ ጋር በተያያዘ እርም የሚሆኑበት ሁሉ በአጥቢዋ እናቱም በኩል ክልክል ይሆኑበታል። በማጥባት ተጽዕኖ ምክንያትአንድ ወንድ ላይ ከጋብቻ እርም የሚሆኑበትን ሴቶች በሚከተለው መልኩ መዘርዘር ይቻላል፤

1. አጥቢዋ
2. የአጥቢዋ እናት (የጥቢ አያቱ)
3. የአጥቢዋ ባል እናት (የጥቢ አያቱ)
4. የአጥቢዋ እህት (የጥቢ አክስቱ)
5. የአጥቢዋ የባልዋ እህት (የጥቢ አክስቱ)
6. የአጥቢዋ ልጆች (የጥቢ እህቶቹ)
የአጥቢዋ የልጅ ልጆች (በጥቢ የእህቶቹ ልጆች)

ፈቃድ፦ በአንድ ሰውና እንደ እናትና ልጅ ባሉ ቅርብ ዘመዶቹ መካከል የሚፈቀድ እንደ መመልከት ለብቻ መገለልና የመሳሰሉ ፈቃዶች ሁሉ የጥቢ ዝምድናንም ተከትለው ይፈቀዳሉ። ሆኖም የጥቢ ዝምድና የስጋ ዝምድናን ያክል የጠነከረ አይደለምና ውርስን፣ የቀለብ ግዴታንና የመሳሰሉ ድንጋጌዎችን ሁሉ አያጋራም። (አልሙግኒ 9/191)

የጥቢ ዝምድና መስፈርቶች

የጥቢ ዝምድና እንዲኖር ተከታዮቹ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።

1 የሚጠባው ህጻን ከሁለት አመት በታች መሆን አለበት፦

ህፃን ልጅ በሚጠባበት እድሜ (ጡት ሳይለቅ) በምግብነት የጠባው መሆን አለበት፤ ይህም በህጻኑ በመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት የእድሜ ክልል ውስጥ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት አመታት ህጻናትን ማጥባት የተሟላና መደበኛ የማጥባት ስርአት መሆኑ በቁርአን በሱረቱል ሉቅማን 14 እና በሱረቱል በቀራህ 233 ላይ ተጠቁሟል።
አላህ እንዲህ ብሏል፤

وَالْوَالِدَاتُ يُرْضِعْنَ أَوْلَادَهُنَّ حَوْلَيْنِ كَامِلَيْنِ لِمَنْ أَرَادَ أَنْ يُتِمَّ) الرَّضَاعَةَ {البقرة : 233}

«እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የኾኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ። (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው» አል በቀራህ 233

በዚህ ጉዳይ ላይ ከምዕመናን እናት ኡሙ ሰለማ የተላለፈውን ተከታዩን ግልጽ ሀዲስ እናገኛለን፤

عَنْ أُمِّ سَلَمَةَ رضي الله عنها قَالَتْ : قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ : (لَا يُحَرِّمُ مِنَ الرَّضَاعَةِ إِلَّا مَا فَتَقَ الْأَمْعَاءَ فِي الثَّدْيِ، وَكَانَ قَبْلَ الْفِطَامِ) والحديث صححه الألباني في صحيح الترمذي

«እርም የሚያደርገው መጥባት አንጀት የደረሰ እና በጥቢ ዘመን ጡት ከመልቀቅ በፊት የተፈጸመ ነው» ሀዲሱን ቲርሚዚይ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል አልባኒም በሶሂህ አቲርሚዚይ የትክክለኛ ሀዲሶች ጥንቅር ውስጥ አካተውታል። ሀዲሱን የዘገቡት አል ኢማም አቲርሚዚይ ረሂመሁላህ እንዲህ ብለዋል፤ «ይህ ትክክለኛ ሀዲስ ሲሆን ደረጃው (ሀሰኑን ሰሂህ) ነው።
"እርም የሚያደርገው መጥባት ከሁለት አመት በፊት ከሆነ ብቻ ነው" የሚለው የሰሀቦችና ከእነሱም በኃላ የመጡት ታላላቅ ኡለማዎች ሁሉ አቋም ነው። ህፃኑ ሁለት አመት ከሞላው በኋላ የተከሰተ ማጥባት ምንንም እርም አያደርግም» ቱህፈቱል አህወዚይ ቅጽ 4 ገጽ 264

በዚህም መሰረት የጥቢ ዝምድና ሁለት አመት ያለፈው ልጅ በማጥባት አይከሰትም። እርም የሚያደርገው ማጥባት ህጻኑ ሁለት አመት ከመሙላቱ በፊት ያለው ብቻ ነው። ከሁለት አመቱ በፊት ጡት የለቀቀ ቢሆን እንኳ ቢጠባ ዝምድናው ይገኛል። ዋናው ከሁለት አመቱ አለማለፉ እንጂ ጡት መልቀቁ አይደለም። ይህ የብዙሀኑ የሻፊኢያ ይህንበሊያና የማሊክ እንዲሁም የከፊል ሀነፊያ የፊቅህ ሊቃውንት አቋም ነው (አልሙግኒ 9/201 ይመልከቱ)

ይህ የማጥባት ህግ እስከ 30 ወራት ይዘልቃል፤ ህጻኑ ጡት ለቀቀም አለቀቀ የሚታየው 30 ወራት አለመሙላቱ ነው ያሉት የሀነፊ መዝሀብ ኡለማዎች ሲሆኑ ተከታዩን የቁርአን አንቀጽ መረጃ አድርገዋል። (አል መብሱጥ ሊሰርሰኺ 5/136)

{وَحَمْلُهُ وَفِصَالُهُ ثَلَاثُونَ شَهْرًا} (سورة الأحقاف: 15)

«እርግዝናውና ከጡት መለያውም ሰላሳ ወር ነው።» አል አህቃፍ 15

የሀነፊ ኡለማዎች መረጃ ያደረጉት ይህ አንቀጽ አነስተኛውን የእርግዝና ግዜ 6 ወር አካቶ የመጣ በመሆኑ ሁለት አመት (24 ወራት) ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሌሎች መረጃዎችም ሁለት አመት የሚለውን ከማጠናከራቸው ከሁለት አመት በፊት የሚለው አንጻር ሚዛን ደፊ ነው።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

2 **አምስት ግዜ መጥባት፦** ህፃኑ ጠግቦ ሙሉ በሆነ ጥቢ አምስት ጊዜ የጠባና በራሱ ጊዜ ጡት የተወ መሆን አለበት። አንድ ግዜም ቢጠባ በቂ ነው ያሉ ኡለማዎች እንዳሉ ሁሉ በሶስት እና በአስር የገደቡትም አልጠፉም። ሆኖም አምስት ግዜ መጥባቱ ግዴታ ነው የሚሉት የሻፍኢያ እና የሀንበሊያ መዝሀብ ኡለማዎች አቋም ሚዛን የሚደፋና በጠንካራ መረጃዎች የተደገፈ ነው። (አል ሙግኒ 9/192 ፤ አል ሙሀዝብ 2/156)
አምስት ጊዜ መጥባት መስፈርት ለመሆኑ መረጃው ተከታዩ የምእመናን እናት አዒሻ ያስተላለፈችው ሀዲስ ነው፤
عن عائشة رضي الله عنها قالت : "كان فيما أنزل من القران عشر رضعات معلومات يحرمن ثم نسخن بخمس معلومات فتوفي رسول الله صلى الله عليه وسلم وهن فيما يقرأ من القرآن." رواه مسلم
የምእመናን እናት አዒሻ እንዲህ ብለዋል፤
«በቁርአን ላይ ከወረዱት አንቀፆች መካከል "አስር የታወቁ ጥቢዎች እርም ያደርጋሉ" የሚል ነበረ፤ በኃላ ግን ተሻረና "አምስት ግልጽ የሆኑ ጥቢዎች..." በሚል ተተካ፤ መልእክተኛው ሲሞቱም (ቅርብ ግዜ በመሻሩ አንዳንድ ያልደረሳቸው ሰዎች ዘንድ) ከቁርአን ይነበብ ነበር» ሙስሊም በቁጥር 1452 ዘግበውታል።

አስር የሚለው በአምስት ከተተካ በኃላ **"አምስት ግልጽ የሆኑ ጥቢዎች"** የሚለው ንባቡ ተሽሮ ህግነቱ ግን የፀና ሆኖ ቀረ ማለት ነው። ይህ አይነቱ ድንጋጌን ሳይሆን ንባብን ብቻ የመሻር የ "ነስኽ" አይነት የኢስላም ሊቃውንት ዘንድ የታወቀ ነው። ስለዚህም በትክክለኛው የኡለማዎች አቋም መሰረት ከአምስት ጊዜ በታች መጥባት እርም አያደርግም።

አንድ ግዜ መጥባት የሚባለው፦ ህፃኑ ጡት ከያዘ በኃላ በግልጽ ጠብቶ በሚስተዋል መልኩ ካቋረጠ አንድ ጊዜ ጠባ ተብሎ ይቆጠራል። አንዳንድ ኡለማዎች ዘንድ ለመተንፈስ ወይም ጡት ለመቀየርም ቢሆን አቁሞ ከቀጠለ እንደ ሁለት ጥቢ ይቆጥሩታል። ሆኖም የመጥባት ገደብ በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑ በተለምዶ ወደታወቀው የመጥባት ትርጉም ይመለሳል። በተቃራኒው ይህ አይነቱ ማቋረጥ እራሱን ችሎ መጥባት የሚባል አይሆንም የሚለው ትክክለኛው አቋም መሆኑን ታላላቅ ፋቀሀዕ አስምረውበታል። (አል ሙግኒ 9/194 ፤ ሙግኒል ሙህታጅ 3/417)

ታላቁ የፊቅህ አዋቂ ሸይኽ ሙሀመድ ቢን ሷሊህ አል ዑሰይሚን እንዳሉት፤ አንድ ጥቢ ማለት አንድ ማእድ እንደማለት ነው። በተለያየ ግዜ (መጅሊስ) የጠባ መሆኑ መስፈርት ነው ብዬ አምናለሁ፤ በአንድ ግዜ ጥቢ እያቋረጠ ቢቀዋል አንድ ጥቢ ነው የሚባለው። ጥንቃቄ ከማድረግ አንጻርም የተሻለው አቋም ይህ ነው በማለት አብራርተዋል። (ኑሩን አለደርብ ቅጽ 19 ገጽ 2)

በዚህም መሰረት ህፃኑ ጠብቷል ለማለት በማያሻማ መልኩ አምስት ጊዜ የጠባና በራሱ ጊዜ የተወ መሆኑ መስፈርት ነው። ቅጽበታዊ ማቋረጦችም ቁጥር ውስጥ አይገቡም። ከአምስት ግዜ በታች የሆነ ጥቢ ግን መስፈርት ያልተሟላበት ነውና ተፅዕኖ የለውም።

- *የጥቢ መዛመድ እንዲከሰት እድሜው ከሁለት አመት ያልበለጠ ህጻን አምስት ግዜ መጥባት አለበት። እዝህ ሁለት መሰረታዊ መስፈርቶች ባልተሟሉበት ሁኔታ የተፈፀመ መጥባት ከሆነ ምንም አይነት የመዛመድና እርም የማድረግ ተፅዕኖ አያሳድርም።*

ህፃኑ ከሁለት አመት በፊት ጡት እንዲለቅ ማድረግ ይፈቀዳልን?

ህጻኑ ሁለት አመት ሳይሞላው ጡት እንዲተው ለማድረግ የተቀመጡ መስፈርቶች ከተሟሉ ይፈቀዳል።
ጡት እንዲተው መደረጉ ህጻኑን የሚጎዳው ካልሆነ
ጡት እንዲተው የሚደረገው በሁለቱ ወላጆቹ ስምምነት ከሆነ

«እናቶችም ልጆቻቸውን ሙሉ የሆኑን ሁለት ዓመታት ያጥቡ። (ይህም) ማጥባትን መሙላት ለሻ ሰው ነው... (ወላጆቹ) ከሁለቱም በኾነ መዋደድና መመካከር (ልጁን ከጡት) መጣልን ቢፈልጉ በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም።» [አልበቀራ:233]
ሸይኽ አብዱረህማን አስ'ሰዕዲይ ረሂመሁላህ አንቀጹን ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፤ «አባትና እናት ህጻኑ ሁለት አመት ሳይሞላው ጡት መጥባትን ሊያስተውት ከፈለጉ፤ "ለልጁ ጠቃሚው የትኛው ነው" የሚለው ላይ ሁለቱ ተማክረው ከተስማሙና ፈቃደኛ ከሆኑ ማስተው ይፈቀድላቸዋል። አንቀጹ በውስጥ ታዋቂነት እንደሚያመለክተው ከሁለቱ የአንዱ ብቻ ፍላጎት ከሆነ ወይም ደግሞ ለልጁ የማይበጅ ከሆነ ጡት ማስለቀቅ አይፈቀድም» ሳእዲ ተፍሲር ገጽ 104

ተያያዥ ነጥቦች

1. ህጻኑ የጠባው የሰው ወተት መሆን አለበት፦

ሁለት ህጻናት ከአንድ ፍየል ቢጠቡ ወንድማማቾች አይሆኑም፤ በዝምድናም አይተሳሰሩም። ኢብኑልሙንዚር አል-ኢጅማዕ በተሰኘው መጽሀፋቸው ገጽ 77 ላይ የሊቃውንቶችን አጠቃላይ ስምምነት "ኢጅማዕ" አስተላልፈዋል። በተመሳሳይ መልኩ ከአንድ የዱቄት ወተት ቢጠቡ ዝምድና አያስከትልም (የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 18) ምክኒያቱም **የማጥባት ወንድምነት አጥቢዋ ሴት በማጥባቷ ምክንያት እናት መሆኗን ተከትሎ የሚከሰት ዝምድና ነው። እናትነት ባልተከሰተበት ሁኔታ ወንድማማችነት አይከሰትም።**

2. ህጻኑ የጠባው ወተት መሆን አለበት፦

የአጥቢዋ ጡት ወተት ባይኖረውና ህጻኑ ውሀ ቢጠባ ዝምድናን አያስገኝም (የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 15) በተመሳሳይ መልኩ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ደም መለገስ በደም ለጋሽና በደም ተቀባይ መካከል የጥቢ ዝምድና አያስኝም (የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 145)

3. ከሚኝ ሴት ቢጠባ፦

በአንዳንድ የጦርነት ጊዜያት እንደሚከሰተው እናት ህፀወቷ ካለፈ በኃላ ህጻኑ ቢጠባ ዝምድና ይከሰታል ወይስ አይከሰትም? አብዛኞቹ የፊቅህ ጠበብቶች በህፀወት መኖር መስፈርት ስላልሆነ እና ወተቱ የሙት ብፀን ስለሌለው ዝምድና ይከሰታል የሉ። ሆኖም የሻፊዒያ ሊቃውንት ህፀወቷ ካለፈ በኃላ ከህላልና ሀራም ማዕቀፍ ውጭ ስለሆነች ልክ ከእንስሳ መጥባት እንደማያዛምደው ሁሉ አያዛምድም ይሉ። (አልሙግኒ 9/198)

4. ወተቱ ግንኙነትን መሰረት ያላደረገ ከሆነ፦

ለምሳሌ ግንኙነት ያላደረገች ድንግል የሆነች ሴት ብታጠባ ሁክሙ ምን ይሆናል? የሀንበሊ መዝሀብ ኡለማዎች፤ ይህ ብዙ ግዜ የማይከሰት ከመሆኑ ጋር ህጻናትን ለመመገብ የተለመደ መንገድ ስላልሆነ ልክ እንደ ወንድ ለጅ ወተት የሚታይ እንጂ ዝምድናን ለማስገኘት ከቁብ የሚቆጠር አይደለም ብለዋል (አልሙግኒ 9/206) ሆኖም ብዙሀኑ ኡለማዎች "ጁምሁሮች" ዘንድ ይህ ወተት ዝምድናን የሚያስገኝና እርም የሚያደርግ ነው። ልጁ የጥቢ ልጇ ነው አባት አይኖረውም። ይህ የተለመደ ባይሆንም ነገር ግን በቁርአን ላይ የምናገኘው ፈቃድ አጥቢዋ ሴት መሆንዋን እንጂ አግብታ በግንኙነት ምክንያት ጡቷ ወተት የሞላ የሚል መስፈርት የለውም ይላሉ። ኢብኑልሙንዚር አል-ኢጅማዕ ገጽ 77 ላይ የሊቃውንቶችን አጠቃላይ ስምምነት "ኢጅማዕ" አስተላልፈዋል።

5. አጥቢዋ ሙስሊም ካልሆነች፦

አይሁድ ወይም ክርስቲያን የሆነች ሴት ብታጠባው ዝምድና እንደሚገኝ ግልጽ ነው። ሙስሊም ባትሆንም መስፈርቶች በተሟሉበት ሁኔታ ጋብቻም የተከለከለ ባለመሆኑ ማጥባትና ልጅን መንከባከብም ጋብቻን ተከትሎ የሚፈቀድ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ሙስሊም ሴት ሙስሊም ላልሆነ ልጅ ማጥባት ይፈቀድላታል።

(የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 61)
ሆኖም ከአህለል ኪታብ ሴቶች ጋር የሚፈጸም ጋብቻ ከሚያስከትላቸው ቤተሰባዊና ማህበራዊ ችግሮች በመነሳት የማይመክር እንደመሆኑ ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር የጡት ዝምድና መፍጠርም አይመክርም።

ጡት መጥባት በራሱ የሚያስከትለው የባህሪ ተጽዕኖ እንዳለ በመግለጽ ኡመር ኢብኑልኸጣብ አይሁድና ክርስቲያኖች ዘንድ ልጆች እንዲጠቡ ማድረግን አስጠንቅቀዋል።

6. ታልቦ ቢጠጣ፦

የጥቢ ትስስር የሚከሰተው፤ ወተቱ ለህጻኑ በምግብነት በማገልገሉ፣ አጥንቱንና ስጋውን በማዳበሩ፣ ረሀብን በማስታገሱ ነው። ወተቱ ታልቦ በእቃ ወይም በጡጦ እንዲወስደው ቢደረግ ይህ ሁሉ ጥቅም ይገኛል። ስለዚህም ከማጥባት ውጭ ባለ ማንኛውም መንገድ ወተቱ ወደ ሆዱ እንዲደርስ ቢደረግ እንደ ጥቢ ይቆጠራል። አምስት ግዜ ከተደገመ የጥቢ ዝምድናን ያስገኛል። ይህ የብዙሀኑ የፊቅህ ሊቃውንት (ጁምሁር) አቋም ነው። (አልሙግሊብን ቁጽግህ 8/ 139 ፤ አልካፊ ሊብን ቁጽግህ 5/65 ፤ የሳውዲ ቋሚ የፈትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 12)

7. ከሌላ ነገር ጋር ተቀላቅሎ ቢጠጣ፦

በዚህ ጉዳይ ላይ ያለው ሚዛን ደፊ አቋም ወተቱ ከሌላ ነገር ጋር ቢቀላቀልም በፐርሰንት ሲታይ ብዙ ሆኖ ከተገኘ መዛመድን ያስከትላል የሚለው ነው። ከሀነፊ መዝሀብ ኡለማዎች የአቡ ዩሱፍ እና የሙሀመድ ቢን ሀሰን አቋም ሲሆን፤ የማሊኪያ የሻፊዒያና የሀንብሊያ መዝሀቦች ሁሉ አቋም ነው። (በዳኢዕ ሰናዒዕ 4/9 ፤ ሙግኒል ሙህታጅ 3/410 ፤ አልሙግኒ 9/197 ፤ አል ኢንሷፍ 9/337 ፤ ከሻፋል ቂናዕ 5/447)

ሸይኽ ኡሰይሚን ህጻኑ ከመድሀኒት ጋር ተቀላቅሎ ቢሰጠው ወተቱ ወደ ሆዱ የሚደርስና ተጽእኖ የሚፈጥር ከሆነ እንደ ጥቢ ይታያል ብለዋል (ኑሩን አለደርብ ቅጽ 3 ገጽ 1867)

8. እርግጠኝነትና ጥንቃቄ፦

የጥቢ ዝምድናን ለማጽደቅ እርግጠኝነት ያስፈልጋል። የማጥባት ዝምድና ከጋብቻ የሚከለክል ዝምድና የሚፈጠረበት ትስስር ነውና ሳያረጋግጡ በቸልታ ዝምድናን ማወጅ ተገቢ አይሆንም። ከእናታችን ዓኢሻ በተላለፈ ሀዲስ የአላህ መልዕክተኛ እቤት ሲገቡ አንድ ሰው እቤት ነበርና "ይህ ሰው ማነው?" በማለት ጠየቁኝ፤ የጥቢ ወንድሜ ነው አልኳቸው። እርሳቸውም "አዒሻ ሆይ! ወንድሞቻችሁ እነማን መሆናቸውን አስተውሉ። የጥቢ መዛመድ የሚከሰተው በረሀብ ሲሆን ነው" አሉ። (ሀዲሱን ቡኻሪ በቁጥር 2453 ሙስሊም በቁጥር 1455 ዘግበውታል

ታላቁ የቡኻሪ ተንታኝ ኢብኑ ሀጀር እንዲህ ብለዋል፤ «የዚህ ትርጉም፤ ምን እንደተከሰተ አስተዉሉ፤ ከጠባበት ግዜ እና ከጠባው የወተት መጠን አንጻር መስፈርቶቹን ያሟላ ጥቢ ነውን? የጥቢ ዝምድና የሚኖረውና ተጽዕኖ የሚያሳድረው መስፈርትቹ ሲሟሉ ነው። ሙሀለብ እንዳሉት፤ የዚህ ወንድማማችነትን ምክንያትመለስ ብላችሁ ቃኙ፤ ጥቢ እርም የሚያደርገው መጥባት ረሀብን በሚያጠፋበት የህጻንነት እድሜ ነው... ጥቢ ከረሀብ የሚያላቅቅ ካልሆነ ቦታ አይሰጠውም እንደማለት ነው!» ፈትሁልባሪ ቅጽ 9 / ገጽ 148

በተመሳሳይ መልኩ ለጉዳዩ ቁብ አለመስጠትና ልጆችን በጋራ ማጥባት ትልቅ ስህተት ነው። በአንዳንድ የህክምና ተቋማትም የእናት ጡት ታልቦ ሲገባ የመቀላቀል አደጋ እንዳይደርስበት ማስጠንቀቅና መከታተል ያስፈልጋል። ሙስሊም ሴት አንድን ህጻን ማጥባት ስትፈልግ እርሱንም የሚያዛምድ ተግባር ስለሆነ ከባለቤቷ ጋር መማከሯ ግዴታ ነው። በጥቅሉ የሌላ ሰውን ልጅ ከማጥባት በፊት አስፈላጊነቱን እና ተጽዕኖዎቹን ማስተዋል ግድ ይለናል።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

አብረው ከጠቡት ሰው ጋር የስህተት የተፈጸመ ጋብቻ

የጥቢ ዝምድና መኖሩ በምን ይወሰናል የሚለውን መልስ ማግኘት እጀንዳውን ለመዳሰስ መሰረት ነው።
ሁለት ታማኝ ወንዶች ወይም አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች የመሰከሩበት **የምስክር ማስረጃ** ካለ የጥቢ ዝምድና ይጸድቃል። ይህ ከውዝግብ የራቀና ሁሉንም ኡለማዎች የሚያስማማ የጋራ አቋም ነው። የሀንበሊ መዝሀብ አቋም ከተከታዩ ሀዲሳዊ መረጃ በመነሳት፤ አንዲት በዲኗ የታመነች ሴት እኔ እገሌን፣ እገሌን አጥብቻለው ብላ **ማረጋገጫ** ከሰጠች የጥቢ ዝምድና መኖሩ ይረጋገጣል ብለዋል (አልሙግኒ 9/222) ሌሎቹ ዘንድ ግን ሀዲሱ አሻሚ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግን የሚያመለክት ብቻ ነው።

ከኡቅበት ቢን ሀሪስ በተዘገበ ሀዲስ ኡቅባህ እንዲህ ይላል። «አንዲት ሴት አገባው። አንዲት ጥቁር ሴቲዮ መጣችና አንተንም እሷንም አጥብቻችኋለው አለችኝ። ነብዩ ዘንድ መጣውና የአገሌን ልጅ እገሊትን አግብቼ ነበር። አንዲት ጥቁር ሴትዮ መጥታ ውሸቷን ሁሌታችሁንም አጥብቻችኋለው አለችን ስላቸው ትተውኝ ዞር አሉ። አሁንም ከፊትለፊታቸው መጥቼ ዋሽታ እኮ ነው አልኳቸው። እሳቸውም "ባለቤትህን ተዋት፤ ሁለታችሁንም አጥብቻለው እያለች እንዴት ይሆናል" በማለት መለሰች» በሌላ ዘገባም የአላህ መልዕክተኛ "እየተወራ እንዴት ይሆናል?" አሉት» ቡኻሪ በቁጥር 2517 ዘግበውታል

ኢብኑ ሀጀር ሀዲሱን ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፤ «"እየተወራ እንዴት ይሆናል?" የሚለው ንግግራቸው የሚጠቁመን ባለቤቱን እንዲለያት ያዘዙት ንግግሯ ትክክል ቢሆን ሀራም እንዳይፈጸም መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ ጥንቃቄን መሰረት ካደረገው የብዙሀኑ ኡለማዎች አቋም ጋር አብሮ ይሄዳል። ምስክርነቷን በመቀበል ነው ያሉም አሉ» (ፈትሁል ባሪ 4/374)

በጥቅሉ ይህ ሀዲስ በሀዳንነት እንጅ በትልቅነት የተፈጸመ መጥባት ዝምድናን እንደማይፈጥር ከሚያሳዩ መረጃዎች መከከከል ይጠቀሳል። በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ ቸልተኝነት እንደማይገባ ያስገንዝባል።

የህፃፊ መዝሀብ ምሁራን አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች የመሰከሩበት ምስክርነት ካልሆነ አይቀበሉም (በዳኢው-ሰናኢዕ 4/14) ፤ ማሊኪያዎችም እንዲት ሴት እና አንድ ወንድ መመስከር አለባቸው ብለዋል (ቢዳየቱል ሙጅተሂድ 2/29) ፤ የሻፊዒ ኡለማዕ አራት ሴቶች መመስከር አለባቸው ብለዋል (ሙግኒል ሙህታጅ 3/224) ፤ ሁሉም ለያዙት አቋም መነሻዎች አሏቸው።

ኢብኑ በጧል ይህንን ሀዲስ ሲያብራሩ፤ «ከኢብኑ አባስ፣ ከጧውስ፣ ከዙሀሪ፣ ከአውዛዒይና ከአህመድ እንዲሁም ከኢስሀቅ እንደተዘገበው፤ ታማኝ የሆነች አንድ ሴት ከመሠከረች በቂ መሆኑን ነው ቢሉም እንደትምል የደረጋል ብለዋል። ይህንን ሀዲስም መረጃ ያደርጋሉ። ከአውዛዒይ እንደተዘገበው ደግሞ ከመጋባታቸው በፊት ከመሰከረች ተቀባይነት አለው ከተጋቡ በኋላ ግን ተቀባይነት የለውም ብለዋል» ከአንድ በላይ ምስክርነትን መስፈርት ያደረጉ አቋሞችን ከዘረዘሩ በኋላ « ከመጀመሪያው አቋም ውጭ ያለውን ያንጸባረቁት ኡለማዎች በዚህ ሀዲስ "እየተወራ እንዴት ይሆናል?" ያሉትን ጥንቃቄን ከማስቀደም ብቻ እንጂ መለያየታቸው ዋጂብ ሆኖ አለመሆኑን ይጠቅሳሉ። አሊይና ኢብኑ አባስን ተመሳሳይ ዋያቄ ቀርቦላቸው፤ ለጥንቃቄ ቢተዋት መልካም ነው። ነገር ግን እርሱ ላይ እርም ማድረግ ለማንም አይቻለውም። ኡመር ኢብኑል ኸጣብም የአንድን ሴት ብቻ ምስክርንት እንዳላጸደቁ ተነግሯል» ሸርህ ሶሂሁል ቡኻሪ ቅጽ 7 ገጽ 202

የአላህ መልዕክተኛ ጥንቃቄን ማስቀደማቸውን የሚያስረዳ ሌላ ዘገባ አለ። አብዱላህ ኢብኑ መሊካ ከቡቅባ ሰምቻለሁ ይበልጥ የማስታውሰው ግን ጓደኛዬ ከሱ ሰምተው የነገሩኝን ነው ካሉ በኋላ፤ "ኡሙ ያህያ ቢንት አቢ ኢሐብን አገባሁ እና አንዲት ጥቁር ሴት መጥታ አጥብቻችኋለው አለችን። ለመልእክተኛው ስነግራቸው ዝም አሉኝ ደገምኩላቸው ዝም አሉኝ አሁንም ደገምኩላቸውና "ውሸቷን እኮ ነው" ስላቸው፤ "ያለችውን ብላለች፤ አንተ ውሸቷን ስለመሆኑ ምን አሳወቀህ?" ልጅቷን ተዋት አሉኝ» ጦበራኒ ዘግበውታል አልባኒም ሰሂህ ብለውታል (አል ኢርዋዕ 7/225)

በአንድ ባልና ሚስት መካከል መስፈርቶች ተሟልተው በተገኙበት መልኩ የተከሰተ የጥቢ ተዛምዶ መኖሩ ከተረጋገጠ መለያየታቸው ግድ ይሆናል!!

ለአዋቂ ልጅ ማጥባት

ከላይ እንደተብራራው የብዙሀኑ የፊቅህ ሊቃውንት (ጁምሁር) አቋም የጥቢ ዝምድና ሁለት አመት ያለፈው ልጅ በማጥባት አይከሰትም የሚለው ነው። ሁለት አመት ያለፈው ህጻን ቢጠባ የጥቢ ዝምድናን ካላስገኝ አዋቂ ሰው ቢጠባ ፍጹም እርም ሊያደርግ አይችልም።በዚህ ጉዳይ ላይ ከምዕመናን እናት ኡሙ ሰለማ የተላለፈውን ተከታዩን ግልጽ ሀዲስ እናገኛለን፤

«እርም የሚያደርገው መጥባት እንጀት የደረሰ እና በጥቢ ዘመን ጡት ከመልቀቅ በፊት የተፈጸመ ነው»
ሀዲሱን ቱርሚዚይ እና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል አልባኒም በሶሂህ አቲርሚዚይ የትክክለኛ ሀዲሶች ጥንቅር ውስጥ አካተውታል። ሀዲሱን የዘገቡት አል ኢማም አቲርሚዚይ ረሂመሁላህ እንዲህ ብለዋል፤ «ይህ ትክክለኛ ሀዲስ ሲሆን ደረጃው (ሀሰኑን ሰሂህ) ነው። **"እርም የሚያደርገው መጥባት ከሁለት አመት በፊት ከሆነ ብቻ ነው"** የሚለው የሰሀቦችና ከእነሱም በኋላ የመጡት ታላላቅ ኡለማዎች ሁሉ አቋም ነው። ህፃኑ ሁለት አመት ከሞላው በኋላ የተከሰተ ማጥባት ምንንም እርም አያደርግም» ቱህፈቱል አህወዚይ ቅጽ 4 ገጽ 264

በተመሳሳይ ሀዲስ የአላህ መልእክተኛ ለዓኢሻ *«የጥቢ መዘመድ የሚከሰተው በረሀብ (ረሀብን የሚጋታ) ሲሆን ነው»* ያሉትም ግልጽ መረጃ መሆኑ ተገልጿል። ሀዲሱን ቡኻሪ በቁጥር 2453 ሙስሊም በቁጥር 1455 ዘግበውታል

በዚህ ጉዳይ ላይ የብዙሀኑን አቋም የተጻረሩ ኡለማዎች መሰረት ያደረጉባቸው መረጃዎችም ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ አንቀጹ ላይ **«አነዚያ ጡት ያጠቧችሁ እናቶቻችሁ፣ የጥቢ እህቶቻችሁም...»** ኒሳዕ 23 ሲል "እድሜያችሁ ከሁለት አመት በታች እያለ" የሚል ገደብ አላስቀመጠም የሚል መከራከሪያ ነጥብ ያነሳሉ። በመሰረቱ ማጥባት የሚባለው ህጻን ልጅን የሚመግብ እና ጡት ከመልቀቅ በፊት ያለው መሆኑ በተለምዶ የታወቀ ከመሆኑ ባሻገር የኡሙ ሱለይም ሀዲስም በግልጽ ያስቀመጠው እውነታ ነውና ይህ መረጃ ሊሆናቸው አይችልም። በሆነኝነት የሚያነሱት መረጃ ግን፤ ቅድመ ኢስላም ይሰራበት በነበረውና ኋላ በሱረቱል አህዛብ አንቀጽ 5 በተከለከለው የማደጎ ልጅን እውነተኛ ልጅ የማድረግ ልማድ ሳሊምን ያሳደጉት አቡሁዘይፋና ባለቤቱ አብረውት በአንድ ክፍል ይኖሩ ስለነበር እና ልጁ ለአቅመአዳም ከደረሰ በኋላ በመቸገራቸው የአላህ መልዕክተኛ የሰጡትን መፍትሄ ነው። ሆኖም እነሱም ቢሆኑ ሀዲሱ እንደሚመለከተው ሰሀቢ እንደ ሳሊም አይነት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ኖረው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ (ለህጃ) የሚፈፀም ብለው ገደብ አድርገውበታል። አል ኢማም አጦበሪ ይህንን አቋም ከደገፉት መካከል፤ አብዱላህ ኢብኑዙበይር፣ አልቃሲም ኢብኑ ሙሀመድን ጠቅሰዋል። አጧዕ፣ለይስ ኢብኑ ሳዕድ፣ ኢብኑ ሀዝም እና ዳውድ አዚሂሪይ አቋሙን እንደሚጋሩ ይነገራል። (ፈትሁልባሪ 9/147)

ያቀረቡት መረጃ እንደሚከተለው ይነበባል፤

(የአቡሁዘይፋ ባለቤት ሰህላ ቢንት ሱሀይል መልእክተኛው ዘንድ መጥታ ሳሊምን ህጻን አድርገን እንቀጥረው ስለነበር ከኔና ከአቡሁዘይፋ ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ያድር ነበር። ያየኛልም፤ አሁን አላህ የቁርአን አንቀጽ አውርዷልና (አህዛብ 5) ምን ይመክሩኛል? በማለት ጠየቀች። የአላህ መልዕክተኛም፦ "አጥቢው" አሏትና አምስት ግዜ አጠባችው። ከዚያን ግዜ በኋላ ልከ እንደ ልጁ ሆነ...)
አቡዳውድ (2061) ነሳኢ (3324) እና ሌሎችም ዘንድ ተዘግቧል

ሀዲሱ በምን መልኩ ሳሊም እንደጠባ አይገልጽም። ሆኖም የሀዲስ ተንታኙ አል ኢማም አን'ነወዊይ እንዲህ ብለዋል፤ «"አጥቢው" የሚለውን አሰመልክቶ አልቃዲ ኢያድ እንዳሉት "ሰውነቷን ሳይነካ ታልቦ ጠጥቶት ነው የሚሆነው" ይህ ጥሩ ትንታኔ ነው። ነገር ግን ተልቅ ሆኖ እንዲጠባ በልዩ መልኩ እንደተፈቀደለት ሁሉ ይህም ለሀጀ ተፈቅዶለት ሊሆን ይችላል አላህ ያውቃል» ብለዋል። በተለይ ደግሞ ሳሊም የሚደነ ልጅ እንደመሆኑ ልክ እንደልጇ የምታየውና እሱም እንደ እናቱ የሚያያት ከመሆኑ አንጻር ነገሩ ቀለል ያለ ነው።

ሀዲሱ ሲጠናቀቅ የምዕመናን እናቶች ቢቃወሟትም ዓኢሻ ግን ይህንን የሳሊም ከስተት መረጃ በማድረግ ለተመሳሳይ ሀጃ መጠቀም እንደሚቻል አቋሟን ትገልጽ ነበር። ከዘይነብ ቢንት ኡሙ ሰለማ በተዘገበ ሀዲስ አዒሻን ስትጠይቃት ሳሊም ያገኘውን ፍቃድ በመጥቀስ መልሳለች (ሙስሊም ቁጥር 1453)

ብዙሀኑ ከልካይ ኡለማዎች ምላሽ፦

ይህ የሳሊም ሀዲስ እሱን ብቻ የተመለከተ ነው የሚለው የምእመናን እናቶች ምላሽ እንዳለ ሆኖ። ሀዲሱና ብይኑ በሌሎቹ ህጻን መሆንን መሰረርት በሚያደርጉ ሀዲሶች የተሻረ (ነስኽ የተደረገ) ነው የሚለውም ምላሻቸው ነው።

በርግጥ ይህንን የሳሊምን ከስተት ለተመሳሳይ ሀጃ መጠቀም የአዒሻ የግል ግንዛቤና አቋም ነበር። ሆኖም ግን በሌሎቹ የምእመናን እናቶች ዘንድ ተቀባይነት እንዳልገነበረው የሚያመላክቱ ብዙ መረጃዎች አሉ።
ከምእመናን እናት ከኡሙ ሰለማ በተዘገበ ሀዲስ «ሌሎች የመልእክተኛው ባለቤቶች ማንም ሰው (በልጅነቱ) ካልጠባ በቀር በዚህ አይነት ጥቢ እነሱ ዘንድ እንዲገባም ሆነ እንዲመለከታቸው አልፈቀዱም። ለዓኢሻም "ለሳሊም በልዩ ሁኔታ የፈቀዱት "ኸስ" ፈቃድ ነው ብልን እናምናለን ሲሉ አስረድተዋታል።» ሙስሊም በቁጥር 1454 ዘግበውታል

የትልቅ ሠው መጥባት ወጤት እንደሌለው የሚገልጹ የሰለፎች አስተምህሮችኖች ይገኛሉ።

1. ከዓጧዕ አልዋዲዒይ በተላለፈ መልዕክት፤ "አንድ ሰው ኢብኑ መስዑድ ዘንድ መጣና፤ የባለቤቴ ጡት ወተት ይዞ ተወጠረና እየጠባው ተፋሁት እንም አባሙሳ ዘንድ ሄጄ ስጠይቀው፤ ሀራም ሆናብሀለች አለኝ" ሲለው ኢብኑ መስዑድ ተነሳ እኛም ተከተልነውና አቡሙሳ ዘንድ ሄደ፤ ከዛም ለዚህ ሰው ምን አይነት ፈትዋ ነው የሰጠኸው? በማለት ጠየቀውና ምላሹን ሲነግረው፤ የጠያቂውን እጅ በመያዝ "አሁን ይህ ሰው ጡት የሚጠባ ነውን? ጥቢ ማለት በሰውነት ውስጥ ስጋና ደምን የሚሰራ ነው። አቡሙሳም ይህ አዋቂ ሰው በመካከላችን እያለ እኔን አትጠይቁ በማለት ተናገረ። (አብዱረዛቅ ሙሶነፍ ቅጽ 7 ገጽ 463 ላይ ጠቅሰውታል) በሌላ አገላለጽ አቡዳዉድ በቁጥር 2059 ዘግበውታል «አጥንትን ያንለበተና ስጋን ያበቀለ እንጂ ጥቢ አያባልም በማለት ሲመልስ፤ አቡ ሙሳ "ይህ አዋቂ ሰው በመካከላችሁ እያለ እኔን አትጠይቁኝ አለ» ሶሂህ አቡዳውድ ላይ አልባኒ ሶሂህ ብለውታል

2. ማሊክ ከናፊዕ ባስተላለፉት ሀዲስ ኢብኑ ኡመር እንዲህ ብለዋል፤ «በሀጻንነቱ ካልጠባ ሰው ጋር የጥቢ ዝምድና የለም። ትልቅ ሰው የጥቢ ዘመድ አይሆንም» አል ሙወጠእ 2/603

3. ማሊክ ሙወጠእ ላይ ሶሂህ በሆነ ዘገባ አብዲላህ ኢብኑ ዲናር ከአብዱላህ ኢብኑ ኡመር አባቱ ኡመር እንዲህ ማለቱን ዘግበዋል፤ «ጥቢ ማለት የህጻንነት መጥባት ነው!» አልሙወጠእ 2/606

ቤተሰባዊ ጉዳይ

ብዙ ኡለማዎች ዘንድ ፈትዋ የሚሰጥበት አቋም ትልቅ ሰው ቢጠባ ዝምድናን አያስገኝም ከጋብቻም አይከለክልም። የሳሊም ሃዲስም እርሱን ብቻ የተመለከተ ነው የሚለው ነው። ከዘመናችን ኡለማዎች ኢብኑ ባዝ፣ ልጅነቱዳኢማህ ይህንኑ ምላሽ ይሰጣሉ። መጅሙዕ ፈታዋ ሊብን ባዝ 22/264 ላይ ፈታዋለጅናህ 21/41 ይመልከቱ። አንዳንዶች ደግሞ ሀዲሶቹን ሁሉንም ተግባራዊ ያደረገ ሀሳብ ያቀርባሉ።

አል ኢማም አሰንዓኒይ እንዲህ ብለዋል፤ «የሰህላህ ሀዲስን እና ለሎቹን ሀዲሶች ከማስታረቅ አንጻር ጥሩ የሚባለው የኢብኑ ተይሚያህ ንግግር ነው። ኢብኑ ተይሚያህ "ህጻን ሆኖ መጥባት ተቀባይነት ያለው መስፈርት ነው። ሆኖም ልክ ሳሊም ከአቡሁዘይፋ ባለቤት ጋር እንደነበረው ሁኔታ ቤት ውስጥ መገኘቱ የግድ ሆኖ ሳለ፤ ለሴቶች ለመከለል አስቸጋሪ ሲሆን ረዷዓ ቢጠቀም የዝምድና ተጽዕኖ ይፈጥራል" ብለዋል። በሳሊም ብቻ ከመገደብ ወይም ተሸጋል ብሎ መልስ ከመስጠት ቋንቋዊ መርሆዎችንም ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር ይህ ንግግራቸው ጥሩ ማስታረቂያ ነው። እነዚህኑ ምክኒያቶች በመጥቀስ የማስታረቂያውን ሀሳብ ተማሪያቸው ኢብኑል ቀዩም ዛዱልመዓድ ላይደግፈውታል» ሱቡሱሰላም ቅጽ 2 ገጽ 313

እንዲህ አይነት ሁኔታዎችን በማገናዘብ የሳውዲ ቋሚ የፊትዋ ኮሚቴ ቅጽ 21 ገጽ 40 እና 46 ላይ የሶስት እና የስምንት ወይም የዘጠኝ አመት ልጆች በመጥባታቸው ዝምድናን አጽድቀዋል።

ሸይኽ ኢብኑ ኡሰይሚን የሳሊም ሀዲስ እሱን ብቻ የተመለከተ አይደለም የሚለውን አቋም ቢመርጡም

« እኔ ዘንድ የትልቅ ልጅ ጥቢ ተጽዕኖ አይፈጥርም። በሁሉም ሁኔታ ልክ እንደ ሳሊምና አቡሁዘይፋ አይነት ሁኔታ ብቻ ሲሆን ነው ተጽዕኖ የሚፈጥረው። አላህ የማደጎ ልጅ መያዝን ስለከለከለ የሳሊም አይነት ሁኔታ ላይ ያለ ሰው አይኖርምና አሁን ሀዲሱን መተግበር የማጥባት ዝምድናን አይፈጥርም።ቤትንም ክልክል አያደርግም። ከሁለት አመቱ በፊት እንደውም ጡት ሳይለቅ ከጠባ ብቻ ነው የሚለው አቋም ሚዛን ይደፋል... ከዚህ አንጻር ስናየው ይህ አቋም ከአብዛኛው ኡለሞች አቋም ጋር ይታረቃል በማለት ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል። (ሸርሁል ሙምቲዕ ቅጽ 13 ገጽ 435 እና 436)

ይህ የጥቢን ህግጋት በተመለከተ አስፈላጊ ያልኳቸውን ነጥቦች የዳሰስኩበት ጽሁፍ ሲሆን አላህ እውቀትን እና መልካም ስራን ይለግሰን ዘንድ እለምነዋለሁ።

አቡጁነይድ ሳላህ አህመድ

ጥር 16/2009

وصلى الله وسلم وبارك على سيدنا محمد وعلى آله وصحبه أجمعين

የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው?

- የልጆችህ ጓደኞች እነማን ናቸው ?
- ከልጆችህ ጓደኞች ጋር ተዋወቀህ ወይንም ቢያንስ እንኳ ተገናኝተህ ታውቃለህ?
- ልጆችህ ከውጭ ወደ ቤት ሲመጡ ምን ይዘው ይገባሉ?
- በልጆችህ ቦርሳ ውስጥ አሊያም በክፍላቸው ውስጥ ምን አለ?

ብዙ አባቶች የነዚህን ጥያቄዎች መልሶች አያውቁም። በቂ መልስ ማቅረብ አይችሉም። በጥያቄው አስፈላጊነት ላይም ጥያቄ ሊያነሡ ይችላሉ። ይህ ስህተት ነው። ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ጓደኞች ማንነት ስለ ልጆቻቸው ዝንባሌ ፣ ስለ ልጆቻቸው ውሎ ፣ ሙሉና በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል። ልጆቻቸው በባህሪና በአካሄድ በዝርዝር ማወቅ አለባቸው። ኃላፊነትም አለባቸው። ነሳኢ በሐዲስ ስብስብ ውስጥ ባካተተው ነብያዊ ሀዲስ ረሱል (ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን) « አላህ ኃላፊነት ያለበትን እያንዳንዱን ሠው ኃላፊነቱን በአግባቡ ተወጥቶም ይሁን ኃላፊነቱን ስቶ እንደሆነ ስለተሰጠው ኃላፊነት ይጠየቃል፣(አባት) (ወንድ) ስለ ቤተሰቦቹ (ስለተሰጠው ኃላፊነት) ይጠየቃል» በማለት ተናግረዋል።

ልጆችን የመቆጣጠር ኃላፊነት በመወጣት ዙሪያ አምስት ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል።

1. በቁጥጥር ስም የሽብር ድባብ ልጆች ላይ መፍጠር አያስፈልግም። ልጆችን መቆጣጠር ልጆችን ማሸበር ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።
2. አንዳንድ የቁጥጥር መንገዶች ድብቅ እና ልጆች በቁጥታ የማያውቋቸው ሊሆኑ ይገባል። ፊት ለፊት ዓይኑን ያፈጠጠ የቁጥጥር ዘዴ መሆን የለባቸውም።
3. ልጆች በራሳቸው ላይ እምነት እንዲያጡ ከማድረግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በቤተሠብ ውስጥ ያላቸው ታማኝነትም መከበር አለበት። በወላጆችና በልጆች መካከል ያለው ግንኙነት በመተማመንና በግልጽነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የልጆች ቁጥጥር መስመር መጠበቅ አለበት።
4. በልጆች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር እንዲሁም በጠቅላላው የልጆች አስተዳደግ ላይ የልጆችን የአድሜ ደረጃ የአስተሳሰብ መጠን ግንዛቤ ውስጥ መክተት ያስፈልጋል። የቁጥጥሩ መጠንና ዓይነት እንዚህን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።
5. የወላጆች ቁጥጥር የልጆችን ትንፋሽ እስከመቁጠር ድረስ ከፍ ያለ እና መድረሻ የሚያሳጣ ዓይነት መሆን የለበትም። እንዲህ አይነት ቁጥጥር አሉታዊ ነው። የሚያስገኘውም ውጤት አፍራሽ ነው። ልጆች አስረኛ የሆኑ አይነት ስሜት ይፈጥርባቸዋል። በራስ መተማመናቸውንም ይንደዋል። ከዚህም በላይ ለቤተሰባቸው ፍቅር እንዲያጡ ያደርጋል።

በጠቅላላው ማንኛውም የልጆች ቁጥጥር ኢስላም ካስተማረው የልጆች ስርዓትና መርህ መውጣት የለበትም። ረሠል/ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን? ከልጆች ጋር ያላቸው የግንኙነት አካሄድ አጥብቆ እንዲከተል ያስፈልጋል። ውጤቱም ተደናቂ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ታዳጊነትና እና ወላጆች

የታዳጊነት ግዜ እጅግ በጣም ወሳኝ የእድሜ ምዕራፍ ነው። ልጆች ሞግዚትነት እና ዕቅፍ ወጥተው የራስን ወሳኔ ወደ መስጠት የሚራመዱበት የሽግግር ምዕራፍ ነው። በታዳጊነት የእድሜ ክልል በሚከሠቱት በርካታ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ለውጦች ምክንያት ልጆች የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ወላጆች በዚህ ክልል ላይ የተለያየ እንክብካቤና ትኩረት ለልጆቻው መስጠትና አለባቸው። አላህ የጣለባቸውን ታላቅ ኃላፊነት መወጣት አለባቸው። በዚህ ወሳኝ የእድሜ ምዕራፍ ላይ ለልጆቻቸው የሚሠጡት ትኩረት በአላህ ፍቃድ በልጆቻቸው የወደፊት ህይወት ላይ ከባድ ሚና ይኖረዋል።

በታዳጊዎች ላይ የሚከሠቱ የስነ - ልቦና ሁኔታዎች

1 የስሜት መለዋወጥና ቶሎ መቆጣት

ታዳጊዎች በአንድ አጭር ቆይታ ውስጥ በተለያዩ የስሜት ሁኔታ ውስጥ ይለዋወጣሉ። አዲስና ትኩረት የሚስቡ ነገሮች ይማርካቸዋል። እዚህ ግባ በማይባል ቀላል ምክንያት ደግሞ በቶሎ ይቆጣሉ። ራሳቸውን መቆጣጠር አይችሉም። ወላጆች እነዚህን ሁኔታዎች ማወቅና በምላሹ የሚያስፈልገውን አያያዝ በደንብ መረዳት አለባቸው።

2 ራስን መሆን / መቻል

ታዳጊዎች ራሱን እንደሚያውቅ ትልቅ ሠው እንዲታዩ ይፈልጋሉ። ከቁጥጥር እንዳልወጡ ህዳናት መታየታቸውን አይፈልጉም። በዚህ ምክንያት ከዕድሜያቸው በላይ በሆነ ትላልቅ ጉዳዮች ውስጥ ራሳቸውን ለመክተት ሲሞክሩ ይታያል። ወላጆች ይህን ስሜት መረዳትና ለስሜቱ የሚመጥን ተገቢ የአያያዝ መንገድ መፈለግ አለባቸው። ታዳጊዎች በትክክል ለመያዝና ተገቢውን ቤተሠባዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮች

1 ውዴታ

ታዳጊዎች ከላይ ሲታዩ ግልፍተኞችና በቶሎ ስሜታቸውን የሚቀይር ቢሆንም ውስጣቸው የህይወት ተሞክሮና ከፋት ያልበረዘው ንጹህ በጣም ስስ ናቸው። ፍቅርና ውዴታን ማግኘት ይፈልጋል። ወላጆች ይህን የውዴታ ጥማት በቤተሠባዊ ፍቅር ሚሚላት አለባቸው። አለበለዚያ ታዳጊው በመጥፎ መንገድ ይህን ክፍተት ለመሙላት ይሞክራል። ካለፈ በኋላ መጸጸት ዋጋ ስለማይኖረው ቤተሠብ ለታዳጊው ልጁ በዚህ ወቅት ስለሚሠጠው ፍቅርና ወዴታ ጠንቅቆ ማሠብ አለበት።

2 እዝነት

ታዳጊዎች የቤተሠባቸውን በተለይ ደግሞ የእናታቸውን እዝነት ይፈልጋሉ። ከቤተሠባቸው የሚያገኙት እዝነት ውስጣቸው የሚኖረውን ሐዘን የሚያቀልህ ደማቅ ጸህይ ይሆንላቸዋል። እርጋታን ይሠጣቸዋል። ስለ ወደፊቱ ብሩህ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል። ስለዚህም በተሰፋ መቁረጥና በታዳጊነት የሐዘን ስሜት ሊዘፈቁባቸው ከሚችሉ ብዙ ችግሮች ራሳቸውን ያርቃሉ።

3 ጥበብ

ወላጆች ብዙ የህይወት ተሞክሮዎችን ያሳለፉ እንደመሆናቸው ወደ ህይወት አዲስ እየገቡ ለሚገኙ ልጆቻቸው የሚሠጡት አያያዝና ጥበብና ብስለት የተሞላበት መሆን አለበት። ከታዳጊዎች ጋር የቁጥታ ግጭት ውስጥ መግባት እና ጉዳዩቻቸውን በእልህ መያዝ አያስፈልግም። ጥፋት ሲፈጽሙም ስሜት በሚጎዱ ቃላቶች ምክር መስጠት የለባቸውም። ለምሳሌ፦ እንት ጎረመስክ ማለት ነው። የመሣሠሉትን ቃላቶች መጠቀም ጥሩ አይደለም።

4 ውይይት

ታዳጊዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ለመፍታት በአላህ ፈቃድ ጠቃሚውና ውጤት የሚያስገኘው የተሻለው አማራጭ ውይይት ነው። ታዳጊዎች ቀጥተኛ ትዕዛዝ ይልቅ በውይይት መልክ በአሳማኝ ሁኔታ የሚሰጣቸውን ምክር ይቀበላሉ። ወላጆች በዚህ ውይይት ወቅት መልዕክት ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ከታዳጊ ልጆቻቸው የሚመጡ መልዕክቶችንም መቀበል አለባቸው።

5 ትዕግስት / ሆደ ሠፊነት /

የልጆች አስተዳደግ ረዥም ትንፋሽ ይፈልጋል። ወላጆች በቶሎ መጠበቅ የለባቸውም። ታዳጊ ልጆች ከሌላው ግዜ በበለጠ በሆደ ሠፊነትና ቻይነት የሚንከባከባቸው የወላጆች ትኩረት ይፈልጋል። ሆደ ሰፊነት /ቻይነት/ ኢስላም ከብር የሚሠጠው መልካም ስነ - ምግባር ነው። ረሡል / ሠላምና ሠላት በርሳቸው ላይ ይሁን / ለአንድ ሰሀባ አላህ ከአንተ የሚወዳቸው ሁለት መገለጫ ባህሪያት አሉህ፤ ሆደ ሠፊነት እና እርጋታ ናቸው በማለት ተናግረዋል። ይህ መልካም የቻይነት ስነ-ምግባር በተለይ በታዳጊ ልጆች አያያዝ ላይ ጥቅም መስጠት አለበት።

ቤተሰባዊ ጉዳይ

ለልጆችህ በራስ የመተማመን ስነ - ልቦና ለመገንባት

✍ ልጅህን በሠዎች ፊት አሞግሠው ።

✍ ልጅህ ጥሩ ነገር ሲሰራልህ ፣ ያዘዝከውን ሲፈጽም አመስግናለሁ በለው ።

✍ አንድ ነገር አንዲፈጸም ስትፈልግ ቀጥተኛ ትዕዛዝ አታድርግበት ከተመቸህ ይህን እቃ ታቀብለኝ እቃዎችህን በስርዓት ብታስቀምጣቸው ጥሩ ነው ይህን የመሠሉ አገላለጽ ተጠቀም።

✍ ልጅህ ልጅነቱን እንዲያጣጥም እድል ስጠው ልጅነቱን እንዲኖር ፍቀድለት።

✍ በራሱ ምርጫውን እንዲወስንና አቋም የመያዝ ክህሎቱን እንዲያዳብር ድጋፍ አድርግለት ።

✍ ትላልቅ ጥሪዎች ሲኖሩህ ቁም ነገር ያላቸው ከፍተኛ ቦታዎች ስትሄድ በቻልከው አቅም አብሮህ እንዲሆን አድርገው ከሁሉም በላይ ልጅህን ይዘህ ልትሄድ የሚገባው ትልቅና ቁም ነገር ያለው ቦታ መስጅድ ነው።

✍ ሐሳብህን አካፍለው ፤ የርሱንም ሐሳብ ጠይቀው ሀሳቡ ከዲን የወጣ እስካልሆነ ድረስ ተቀበለው።

✍ በቤት ውስጥ ዐቅም በፈቀደ መጠን የራሱ ክፍል ፣የራሱ ቦታ እንዲኖረው አድርግ ።

✍ ጥሩ ጓደኞች እንዲያፈራ ድጋፍ አድረግለት በጓደኞቹ ፊት አትውቀሰው ክብር ስጠው።

✍ አላህ ብዙ ችሎታዎችን እንደለገሰው ንገረው ተፈላጊ እና ቦታ የሚሠጠው እንደሆነ እንዲሠማው አደርገው ።

✍ ሶላትን አስተምረው አብሮህ እንዲሠግድ አድርግ።

✍ በዋነኝነት አላህን እንዲወድ አድርገው ኢማን በልቡ ውስጥ ለማስገባት ጥረት አድርግ ።

✍ በአላህ ላይ መመካትን አስተምረው በራስ የመተማመን ስሜቱ በአላህ ላይ ከሚኖረው መደገፍ የመነጨ መሆን እንደሚገባው አስረዳው።

✍ ሐሳቡን እንዴት መግለጽ እንደሚችል አስተምረው ሐሳቡን ያለፍርሃት መግለጽ እንዲችል አደፋፍረው ስርዓትን አስተምረው

✍ በሠዎች ፊት አትናገር አትበለው ሀሳቡን በማቋረጥ አታሸማቀው።

✍ ራሱን ማክበርና ሰዎችን ማክበር እንዴት እንደሚችል አስተምረው ።

✍ ጥያቄዎቹን መልስለት፣ ልጅነው ብለህ ቸል አትበለው ።

✍ የገባህበትን ቃል አክብር ቃልህን ማክበር የማትችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ቀደም ብለህ አስረዳው ይቅርታም ጠይቀው።

✍ ቢያንስ ብቻውን ቢሆን ለራሱ ምግብ ማቅረብ የሚችልበትን ያህል ማብሰል አስተምረው ።

✍ ዘወትር ዱዓ ማድረግ እንደሚኖርበት አስተምረው። ሲጨንቀው ወደ አላህ መሸሸ እንዳለበት አስረዳው፡

✍ ከሌሎች ልጆችና ከወንድሞቹ/ ከእህቶች ጋር በጋራ መስራትን አስለምደው በቡድን ውስጥ እንዴት ኃላፊነቱን እንደሚወጣ አሳየው።

✍ የተለያዩ ምክንያቶች በመደርደር ከሠዎች አታርቀው። ሰዎችን መቅረብ የሚወድ አድርገው ።

✍ ጥያቄ እንዲጠይቅ አበረታታው የሚሠነዝራቸውን ጥያቄዎችን «ምን አይነት ጥያቄ ነው» የሚል መልስ በመስጠት አታሸማቀው ከተሳሳተ ስህተቱን አስረዳው ።

✍ እርሱን በተመለከተ በምትወስዳቸው ውሳኔዎች ላይ አማክረው፤ ሐሳቦችንና ፍላጎቶቹን አዳምጥ። እርሱ ምን ያውቃል ልጅ ነው ብለህ ፍላጎትህን ብቻ ልትጭንበት አትሞክር።

✍ ስለራስህ አጫውተው። በአባቱና በእናቱ ደስተኛ ልጅ እንዲሆን አደርግ።

✍ እሺ ማለት ብቻ ሳይሆን የማይስማማውና የማይወደው ነገር ሲኖር እንዴት እምቢ አይሆንም እንደሚል አስተምረው ።

✍ ሲወድቅ ራሱን ችሎ እንዴት መነሳት እንዳለበት አስተምረው።

✍ የራሱን ክፍል፣ የራሱን ልብሶች፣ እንዲሁም የራሱን የትምህርት መገልገያዎች ራሱ እንዲያስተካክልና በስርዓት እንዲይዝ አስተምረው ።

✍ ስለ ዓላማው ፣ ስለ ህልሙ፣ ስለምኞቱ አዋራው። ሐሳብህን አካፍለው።

✍ ኃላፊነቶችን እንዲወስድ አድርግ።

✍ ስራዎችን ሲያጠናቀቅ አወድሰው። የማበረታቻ ሽልማቶች ስጠው።

✍ ጥፋት ስትፈጽምበት ይቅርታ ጠይቀው።

✍ ልዩና አስደሳች ስጦታዎችን ባልጠበቀው ሠዓትና ቦታ ስጠው።

✍ ከቁርዓን ጋር ያለው ግንኙነት የጠበቀ እንዲሆን አድርግ ።

✍ ስለሶሀቦች የህይወት ታሪክ መፅሀፎችን አንብብለት ፤ ምን ያህል መንፈሰ ጠንካራ መልካም ሰዎች እንደነበሩ አስተምረው።

✍ መፅሀፍቶችን እንዲያነብ አበረታታው። በንባብ በሚያገኘውን ዕውቀት በራስ የመተማመን ስነ ልቦናውን እንዲዳብርለት አድርግ ።

✍ ዘወትር ዱዓ አድርግለት። አላህን መልካሙን መንገድ እንዲያመላክተው ከክፉት ሁሉ እንዲጠብቀው በወላጅ ልብ ተማፀንለት። ሁሉም መሆን የሚችለው በአላህ ሀይልና ፍቃድ ብቻ ነው።

ቁርዓን የጭንቀት መፍትሄ

ከየትኛውም መንገድ በተሻለ ከቁርዓንና ጋር በሚገባ መተዋወቅ መፍትሄ ነው። የሞከረው በደንብ ያውቀዋል። ጭንቀትን ለማስወገድና በስፍራው ቃላቶች ሊገልጹት ኃይል የሚሰጣቸውን ነፍስን የሚወዘውዝ እርካታ ለማግኘት ከቁርዓን የተሻለ መንገድ ከቶም የለም። ጭንቀት ስለማይታወቀው ነገር ከመጠን ባለፈ ማሠብ እንደመሆኑ የሸይጣን ውትወታ ውጤት ነው። ለሸይጣን መፍትሄው ደግሞ አላህን ዘወትር ማስታወስ ነው።


الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكْرِ اللَّهِ ۗ أَلَا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوبُ [١٣:٢٨]

(እነሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው። ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ። >> (ረዕድ 28)

በአላህ ላይ ጠንካራ እምነት ያለው ሠው ነገን በመፍራት ለጭንቀት አይንበረከክም። ሁሉም ነገር በአላህ እጅ እንደሆነ ያምናል። የሚሠጠው ፣ የሚያነሳው ፣ የሚያከብረው ፤ የሚያወርደው አላህ ብቻ ነው።

ከጭንቀት ለመራቅ ሸይጣን ማሸነፍና ወደ አላህ ቅርብ መሆን ያስፈልጋል ስለ አላህ ውሳኔና ቀደር የጎላበት እምነትና እውቀት ማከማቸት የግድ ይላል። ሀሉም ነገር በአላህ ውሳኔ የሚሆን ነው የማያስጨንቅ ነገር የለም !





ነፍስን ማጥራት

ከስክሪን በስተጀርባ ካሰፈሰፉ ሰይጣናት ሁሉ "በአላህ እጠበቃለሁ!"

እህቴ ሆይ!

በቅድሚያ፤ ያለሽው በፈተናዎች ዘመን ስለሆነ የተጋረጠብሽን ለመወጣት ካንቺ ጥንቁቅነት፣ ቆራጥነትና በአላህ መመካት የመሳሰሉ ባህርያትን መላበስ እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን ልብ በይ።

ባለንበት ዘመን አንቺን ወደ መጥፎ ነገሮች የሚጎተጉቱ ወስዋሶች በርካታ ናቸው።

☞ በተለይም ነፍሲያ፣ የሰው ሰይጣናትና የጂን ሰይጣናት ተጠቃሾች ናቸው።

ነፍሲያ ማለት የየራሳችን ግላዊ ስሜት ሲሆን፤

የሰው ሰይጣናት ስንል ደግሞ እንደ እኛው ሰዎች የሆኑ፤ ግና በሩቅም በቅርብም ሆነው ወደ ክፉ ነገር የሚያነሳሱን፣ ወደ ስህተት የሚገፋፉንና ለወንጀል የሚያመቻቹን የጥፋት ጓዶች ናቸው።

ባህሪያቸው የሰይጣንን ባህሪ የተላበሰ በመሆኑ የሰው ሰይጣናት ይባላሉ።

የጂን ሰይጣናት ደግሞ በተፈጥሮአቸው ከማይታዩት ከጂኖች/አጋንንቶች የሚመደቡ ሲሆን፤ በቁንጮአቸው ኢብሊስና ዝርዮቹ የሚመሩ ናቸው። እነኝህ ሰዎችን በስውር የሚጎተጉቱና ለወንጀል የሚዳርጉ ክፉ ፍጡሮች ናቸው።

☞ የሰው ሰይጣናዊነት አንዱ ባንዱ ላይ በሚያደርገው ክፉ እምነትና ተግባር የሚገለፅ በመሆኑ በብዙ ነገሮች ውስጥ ይገባል።

ለምሳሌ ያክል በዘመኑ የመገናኛ አውታር በኢንተርኔት በሰው ሰይጣኖች ገፋፊነት ብዙ ፈሳዶች ሲተገበሩ ይታያል ይሰማልም።

ሙስሊሟን ሴት ለማጥቃት እና ወደ ብልግና ለመሳብ ከስክሪን ጀርባ እንዳሰፈሰፉ መሽቶ የሚነጋባቸው ወስላቶች እዚህ ጋር ተጠቃሽ ናቸው

በተለያዩ ዘዴዎች ካንቺ ጋር ይፃፃፉና፣ ያወጋሉ። አንቺም ሂጃብሽን፣ ድብቅነትሽና ጥንቃቄሽ ትርጉም እንዲያጣ በሚያደርግ መልኩ በሱስ ትጠመጂና ወሬ ለጀመረ ሁሉ በርሽን ክፍት ታደርጊያለሽ።

የዚያኔ ቀድመው የተዘጋጁት መሰሪዎች የባጡን የቆጡን እየፈለፈሉልሽና እያስለፈለፉሽ ወደ ተንኮል መረባቸው ይከቱሻል። የትዳርም ይሁን ሌላ ወሬ ይዘው በምርቃና ያከንፉሻል፤ ላሰቡት ፀያፍ ምግባር ግብአት እስክትሆኚም በነገር ያዋኙሻል፤

☞ ይህ ጉዳይ አንተን ወንድሜንም ይመለከተሃል ።

በእንደዚህ አይነቶቹ የሰው ሰይጣናት ተሸንግለህ እውነተኛ ማንነቷን በውል ከማታውቃት ሴት ጋር የቻት የወሬ ትጀምራለህ፤ ቀስ በቀስም ውሃ ውስጥ እንደገባ ጨው ትሟሟለህ። ሀፍረን የመፍቅ ብቃትህ፣ ሃያልህና ትእግስትህ ሁሉ ይመናመናል!!

እናስታውስ...

ነቢዩላህ ዩሱፍ (ዓለይሂሰላም) ባሪያ ሆነው ተሸጦ ነበር። እንደፈለገ በሚያዝዘውና በሚያደርገው ንጉስ ስር በቤተመንግስት ነዋሪም ነበር።

በወቅቱ ነቢዩ ዩሱፍ በንጉሱም ሆነ ንግስቲቱ የታዘዘውን ከመፈም ውጭ አማራጭ አልነበረውም።

አንድ ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ብቻውን እያለ የንጉሱ ሚስት በጣም ተውባና ተቆንጃጅታ ዘው ብላ ገባች። በሮቹን ሁሉ ቆላለፈች። ለእርሱ ስትል ዝግጅቷን እንዳጠናቀቀችም አበሰረችው። የምትፈልገውን እንዲያደርጋትም ሹክ አለችው።

ይህንን ታሪክ አላህ በቅዱስ ቃሉ እንዲህ ገለፀልን፦

وَرَاوَدَتْهُ الَّتِي هُوَ فِي بَيْتِهَا عَن نَّفْسِهِ وَغَلَّقَتِ الْأَبْوَابَ وَقَالَتْ هَيْتَ لَكَ ۚ قَالَ مَعَاذَ اللَّهِ ۖ إِنَّهُ رَبِّي أَحْسَنَ مَثْوَايَ ۖ إِنَّهُ لَا يُفْلِحُ الظَّالِمُونَ }

[يوسف : 23]

« ያቺም እርሱ በቤትዋ የነበረባት ሴት፣ ከነፍሱ አባበለችው፤ ደጃፎችንም ዘጋች፤ ላንተ ተዘጋጅቼልሀለሁና ቶሎ ና አለችው፤ "በአላህ እጠበቃለሁ" እርሱ (አሳዳሪዬ የገዛኝ) ጌታዬ ኑሮዬንም ያሳመረልኝ ነውና (አልከዳውም)፤ እነሆ! በደለኞች አይድኑምና፤ አላት።» ዩሱፍ : 23

ነቢዩላሂ ዩሱፍ (ዓለይሂ ሰላም) ስሜቱን ከጫፍ የሚያደርሱ ነገሮች ቢያጋጥሙትም ራሱን አቅቦ፣ አሳዳሪ ንጉሱን ባለመክዳት፣ ፈጣሪ ጌታው አላህንም በመፍራት ይህን አጭር ምላሽ ሰጣት።

ምንም በንግስቲቷ ጥላ ስር ቢኖር፣ በሩን ቆላልፋበት ብታስገድደው፣ አማራጭ ማምለጫ ባይኖረውም ተስፋ አልቆረጠምና፤ የጭንቅ ግዜ ደራሹ ወደሆነው አላህ ጥሪውን አቀረበ።

قال معاذ الله"

«በአላህ እጠበቃለሁ አላት» ዩሱፍ : 23

በልቡ ውስጥ ያለና እርግጠኛ እምነቱ ነበርና ጌታውም አላህ ጠበቀው ፤ ከፈተናም አዳነው።

የዚህ አይነቱ ወደ ፀያፍ ተግባር የሚደረግ ጥሪ ዛሬም በኢንተርኔት የቻት መስኮቶች በተደጋጋሚ እየተለፈፈ ነው።

ነገር ግን ከወንዱም ከሴቷም የነብዩ ዩሱፍን አይነት አቋምና ምላሽ ማን ይስጥ

«በአላህ እጠበቃለሁ!» የሚል!

ሁሌም ከአጉል ስሜት፣ ከሰውና ከጂን ሰይጣናት ለመጠበቅ የአላህ ፍራቻና ዱዓእ ሊለየን አይገባም።

ውድ እህቴ በተለያዩ የመገናኛ መስመሮች ከሚደረጉብሽ ትንኮሳዎችና የተሳሳቱ ግብዣዎች ራስሽን ተከላከይ ማንነትሽን ጠብቂ! ክብርሽንም አታስደፍሪ! በአቋምሽ ላይም የፀናሽ ቆራጥ ሁኚ!

«በአላህ እጠበቃለሁ!» ማለት የሁልጊዜ ልማድሽ ይሁን!

አላህ ሆይ! እህቶቻችንን ከጥፋት ሁሉ ጠብቅልን! የሙስሊሙ ማህበረሰብ አለኝታና የቤተሰብ መሰረት ናቸውና ከሰውና ከጂን ሰይጣናት ሁሉ ሰውራቸው! ለትእዛዝህ ተገዢም አድርጋቸው!!



ቆም ብለን እናስብ!!

አንድ ቀን ሱለይማን ኢብኑ አብድልመሊክ ደማስቆ የሚገኝ መስጅድ ገባና አንድ ሽማግሌ ሲንፏቀቅ አገኘው። አሁን ብትሞት ደስ ይልሀል? አለው። ሰውየውም «በፍጹም!» በማለት መለሰ። «ይህ እድሜ ላይ ደርሰህ መሞት አትፈልግም?» አለው። ሰውየውም፤ «ወጣትነት እና ሽሩ አልፈዋል፤ ሽምግልና እና ኸይሩ ቀርትዋል። ከተቀመጥኩ አላህን አወሳለው፤ ከተነሳሁ አላህን አመሰግናለው። እነዚህ ሁለት መልካም ተግባሮች እንዲኖሩ እፈልጋለሁ» በማለት መለሰ።

አላህ ሆይ! በመልካም ስራ የተሞላ ረጅም እድሜ ለግሰን!

አሚን!!

ነፍስን ማጥራት

ሁላችንም ስውር ወንጀሎችን እንጠንቀቅ ! !

በግልፅ በሚታዩ አምልኮዎች ለአላህ እጅ እንደሰጠን ሁሉ በድብቅ ወደ አላህ የሚያቃርቡን መልካም ስራዎች ይኑሩን። በገሀድ ወንጀሎችን እንደማንዳፈር ሁሉ በድብቅም አላህን እንፍራ። የፍጡራን እይታ ከመጥፎ ስራ ካቀበን አላህ እንደሚያየን በማሰብ ወንጀሎችን እንጠንቀቅ። ባለንበት ወቅት ወንጀልን ለመፈፀም ነገሮች ቢመቻቹ፤ ፈተናችን እየበረታ ነውና እንዘናጋ ! !

ድብቅ ወንጀሎችን መላመድ የቀልብ ሞትን ያስከትላል። የምናመልከው፤ ግልፁንም ድብቁንም ስራችንን የሚያውቀውን አላህን ነው። በገሀድ ወንጀሎችን ከመዳፈር ጥንቃቄ እንደምናደርፍ ሁሉ በድብቅም ትእዛዛትን አንጣስ የተከለከሉ ነገሮችንም አንዳፈር። ሰሚ ተመልካችነቱን፣ ውስጥ አዋቂ መሆኑን የሚገልፁ ስያሜዎችን የማመናችን ፍሬ ይህ ሊሆን ይገባል።

☞ የዲን ተማሪዎች ሆይ . . . ስውር ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ! !

☞ ኡስታዞችና ታዋቂነትን ያገኛችሁ ዳኢዎች ሆይ . . . ስውር ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ! !

☞ ቁርአን የሀፊዛችሁ ወንድምና እህቶች . . . ስውር ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ! !

☞ ቤተሰቦችሽ እምነት የጣሉብሽ እህታችን . . . ስውር ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ! !

☞ አላህ ሁሉ ነገር አሚልቶልህ በበን ተግባር የታወቅከው ወንድም ሆይ . . . ስውር ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ! !

ዘወትር ይህንን ሀዲስ እናጢነው፤ ሰውባን እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺእንዲህ ብለዋል፤ «ከኔ ህዝቦች፤ በእለተ ትንሳኤ ንፃታቸው ቲሀማ የተባለውን ተራራ የሚመስሉ መልካም ስራዎች የሚኖሯቸውን ሰዎች አውቃለሁ፤ አላህ ስራቸውን የተበተነ ትቢያ ያደርገዋል።» ሰውባንም፤ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ባለማወቅ ከነሱ እንዳንሆን ማንነታቸውን ግልፅ ያድርጉልን" አሏቸው።

እሳቸውም፤ «እነዚህ ሰዎች ከናንተው የሆኑ ወንድሞቻችሁ ናቸው፤ እናንተ የለሊት ስግደት እንደምትሰግዱ እነሱም ይሰግዳሉ። ነገር ግን እነዚህ ጭፍሮች ከሰዎች ሲገለሉ አላህ እርም ያደረጋቸውን ነገሮች ይዳፈራሉ» ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል አልባኒም ሰሂህ ብለውታል

عَنْ ثَوْبَانَ رضي الله عنه ، عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَنَّهُ قَالَ : [لَأَعْلَمَنَّ أَقْوَامًا مِنْ أُمَّتِي يَأْتُونَ يَوْمَ الْقِيَامَةِ بِحَسَنَاتٍ أَمْثَالِ جِبَالِ تِهَامَةَ بِيضًا فَيَجْعَلُهَا اللهُ عَزَّ وَجَلَّ هَبَاءً مَنْثُورًا قَالَ ثَوْبَانُ يَا رَسُولَ اللهِ صِفْهُمْ لَنَا جَلِّهِمْ لَنَا أَنْ لَا نَكُونَ مِنْهُمْ وَنَحْنُ لَا نَعْلَمُ قَالَ أَمَا إِنَّهُمْ إِخْوَانُكُمْ وَمِنْ جِلْدَتِكُمْ وَيَأْخُذُونَ مِنَ اللَّيْلِ كَمَا تَأْخُذُونَ وَلَكِنَّهُمْ أَقْوَامٌ إِذَا خَلَوْا بِمَحَارِمِ اللهِ انْتَهَكُوهَا] رواه ابن ماجة (4245) وصححه الألباني .

አላህ ሆይ! ጥንካሬን ለግሰህ ከጥፋቶች ሁሉ ጠብቀን ! ! እንደጥፋታችን እና መዳፈራችን ሳይሆን እንደ እዝነትና ችሮታህ ገር የሆንን መተሳሰብ ተሳሰበን ! !



ተቅዋ

ውድ እህቶቼ ሆይ!

ታላቅና ከጉድለቶች ሁሉ ነፃ የሆነው አላህ በመጀመሪያዎቹና በመጨረሻዎቹም ሕዝቦች (ባሪያዎች) ላይ ያዘዘው ነገር ቢኖር አላህን ፉሩ በማለት ነበር። ይህንንም በማስመልከት ከፍ ያለው አለህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَقَدْ وَصَّيْنَا ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِكُمْ وَإِيَّاكُمْ أَنِ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۚ وَإِن تَكْفُرُوا۟ فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَنِيًّا حَمِيدًا ﴿١٣١﴾ ﴾ النساء: ١٣١

<<እነዚያንም ከበፊታችሁ መጽሐፍን የተሰጡትን እናንተንም አላህን ፍሩ በማለት በእርግጥ አዘዝን። ብትክዱም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። (አትጐዱትም)። አላህም ተብቃቂ ምስጉን ነው።>> (አል ኒሳእ 131)

በተጨማሪም መልዕክተኛው ለሕዝቦቻቸው ያስተላለፉት ትዕዛዝ (ምክር)፡- ከአቢ ኡማማ እንደተወራው ስማቸው ሱዳና ኢብኑ አጅላን አልባህሊይ ይባላል (አላህ ከሳቸው የሆነውን ይውደድላቸውና) የአላህ መልዕክተኛ ﷺበሐጀተል ወዳዕ ምክር ሲሰጡ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብሎ አለ።

اتقوا ربكم وصلّوا خمسكم، وصوموا شهركم، وأدّوا زكاة أموالكم، وأطيعوا أمراءكم، تدخلوا جنة ربكم

"ጌታችሁን ፍሩ፣ የአምስት ጊዜ ስግደታችሁንም ፈፅሙ፣ የረመዳንንም ወር ጹሙ፣ የገንዘባችሁንንም ዘካ ስጡ፣ አሚሮቻችሁንም ታዘዙ የጌታችሁን ጀነት ትገባላችሁ።"

ነብዩ ﷺ ለአንድ ሰራዊት አሚር አድርገው በላኩ ጊዜ በተለየ ሁኔታ ለእራሱ አላህን በመፍራት ምክር ያስተላልፉለት ነበር። በተጨማሪም እሱ ጋር ካሉት ሙስሊሞች በጥሩ ነገር ይመክሯቸው ነበር።

ቀደምት ሳሊሆች በምክሮቻቸውና በፅሁፎቻቸው ላይ እንዲሁም ከዚህችም አለም በሞት በተለዩ ጊዜ አላህን ፍሩ ከማለት አልተወገዱም።

ዑመር ኢብኑል ኸጣብ አንዲት ፅሑፍ ወደ ልጁ አብድላህ ጽፎ ነበር የፅሑፉም መልዕክት እንዲህ ነበር የሚለው፡-

"በመቀጠልም ..... ታላቁን አላህ በመፍራት እመክርሃለሁ። ነገሩ እንዲህ ነው አላህን የፈራ ይጠብቀዋል፣ እሱ ጋር ያስቀመጠም ይመሰደዋል፣ ላመሰገነውም ይጨምርለታል"

አልፅ አንድን ሰው እንዲህ በማለት መከረ "እሱን ከመገናኘት ምንም ቅሮት የሌለውን ያንን ታላቁን አላህ በመፍራት እመክርሀለሁ። ከእሱ ሌላ መጨረሻም የለህም እሱም (አላህ) የቅርቢቱንና የመጨረሻይቱ ሀገር ባለቤት ነው"

ከሳሊሆች ውስጥ አንዱ በአላህ መንገድ ላይ የተገናኘው ወንድም ነበረውና ወደእሱ አንዲትን ፅሑፍ ፃፈለት
" በመቀጠልም ይላል ...

"አላህን በመፍራት እመክርሃለሁ ያህ እሱ አልጋህ ላይ ሆነህ የሚጠብቅህን፣ ከላይ ሆኖ የሚቆጣጠርህን፣ በማንኛውም ሁኔታ በቀንም ይሁን በማታ (በሌሊት) አላህን ቀልብህ ውስጥ አድርግ፣ አላህን ከአንተ ባለው ቅርበትና በአንተ ላይ ባለው ችሎታ ልክ ፍራው፣ አንተ በእሱ እይታ (ጥበቃ) ስር እንደሆንክም እወቅ፣ ከእሱ ስልጣን ስር ወጥተህ ወደ ሌላ ስልጣን ስር አትግባ፣ ከእሱ ባለቤትነትም ወጥተህ ወደ ሌላ ባለቤትነት አትግባ፣ ከእሱ ጥንቁቅነትህ ከፍ ይበል ፍራቻህ ይብዛ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን።"

ፍራቻ (ተቅዋ)፡- ማለት አንድ ሰው በራሱና በሚፈራው ነገር መሀል ከእራሱ የሆነ መጠበቂያ ሲያደርግ ተቅዋ አድርጓል ይባላል።

አንድ ሰው አላህን ፈርቷል ስንል፡-

በእራሱና ከሚፈራው ነገር፣ ከቁጣውና ከጥላቻው የሚጠብቀውን ትዕዛዙን በመፈፀምና ክልከላውን በመራቅ መከላከያ ማድረግ ማለት ነው።

ይኸውልሽ ውድ እህቴ፡-

ቀደምት ሳሊሆች የተቅዋን ትርጉም በማብራት የተጠቀሟቸው ከፊል አባባሎች፡-

አብድላህ ኢብኑ አባስ (ከእሱ የሆነውን አላህ ይውደድለትና) እንዲህ ይላል ፡-

"አላህን ፈሪዎች የሚባሉት እነዚያ አላህንና ቅጣቱን የሚጠነቀቁ ናቸው።"

ጠልቅ ኢብኑ ሐቢብ ተቅዋን በማስመልከት እንዲህ ይላል ፡-

<<አላህን መፍራት ሲባል በአላህ ብርሃን የአላህን ትዕዛዝ ልትፈፅምና ከአላህ ምንዳ (ዋጋ) ልትፈልግ፤ እንዲሁም በአላህ ብርሃን የአላህን ክልክሉ ልትርቅና ቅጣቱን ልትፈራ ማለት ነው።>>

አብድላህ ኢብኑ መስዑድ

﴿ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ ﴾ آل عمران: ١٠٢

የሚለውን የቁርአን አንቀፅ ሲተረጉም እንዲህ ይላል፡-

"ትዕዛዙ ሊፈፅምና ክልክላው ሊራቅ፣ ሁሌም ሊታወስ ላይረሳ፣ ሊመሰገንና ዐጋው ላይካድ"

ውድ እህቴ ታላቁን አላህ በመፍራት ላይ ጓጊ እሱ ከጉድለቶች ሁሉ የጠራ ሲሆን ሊፈራ የተገባና እንዲሁም ልቅዕናውን ልብሽ ውስጥ ልታደርጊው ይገባል።



ተንቢሀት ካውንስሊንግ



በመጀመሪያው ቀን ትውውቅ እንዴት ልገመግመው?

ዕድሜዬ 22 ነው፤ የመጨረሻ ዓመት የዩንቨርስቲ ተማሪ ነኝ። ከአንድ ወጣት በቤተሰቦቹ በኩል የትዳር ጥያቄ ቀረበልኝ:: እናቱ ወደደችኝ እና ለእናቴ ጥያቄዎን አቀረበች፤ አባቱ እና አባቴ ተነጋገረው የሁለታችንም ቤተሰቦች በተገኙበት እንድንተያይ እና እንድንተዋወቅ ቀጠሮ ያዙልን ።

ከልጁ ጋር ምንም የቀደመ ትዉዉቅ የለንም፤ ተያይተን አናውቅም። ምናልባት ስንተያይ የምርጫውን አይነት ሴት እንዳልሆን ወይንም እርሱ እኔ የማልወደው ዐይነት ወንድ እንዳይሆን ፍርሃት አለኝ። ቤተሰቦቼ ቀጠሮው ለመተዋወቅ ያህል ብቻ እንደሆነ እና ሌሎች እርምጃዎች የሚኖሩት በሁለታችንም በኩል ሙሉ መፈቃቀድ ሲኖር ብቻ እንደሆነ አስረድተውኛል።

ጥያቄዬ የሚከተለው ነው ፤

በመጀመሪያ ትውውቅ የምርጫዬን ዓይነት እንደሆነ እንዴት ልገመግመው እችላለሁ?

ስብዕናውን ለመረዳት እና አስተሳሰቡን ለማወቅስ ምን መጠየቅ ወይም መናገር አለብኝ?

የተሳሳተ ምርጫ ላይ ወድቄ የስሜት ጉዳት እንዳይደርስብኝ መጠንቀቅ አፈልጋለውና እባካችሁ ምክር ለግሱኝ።

: : : : : : : : : : : : : : :

ምላሽ : – ከሁሉም በፊት ከአላህ ጋር ያለሽ ትስስር በጣም ጠንካራ ይሁን፤ ከአላህ ጋር ያለሽ ትስስር ጠንካራ ከሆነ እና ዘወትር ዱዓ ካልተለየሽ የጉዳዬችሽ ፍጻሜ ሁሉ ያማረ እንደሚሆን አያጠራጥርም። አላህ እርሱን ታዛዦችን ወደ መልካም መንገዶች ይመራል።

وَمَن يَتَّقِ اللَّهَ يَجْعَل لَّهُ مِنْ أَمْرِهِ يُسْرًا

«አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለርሱ መግራትን ያደርግለታል» ጦላቅ 4

ውዷ እህታችን !

በጥያቄሽ ላይ እንደቀረበው አይነት የህይወት መንገድን የሚያስቀይሩ መንታ መንገዶች ሲገጥሙን ምርጫን ወደ አላህ ማስጠጋት መልካም መሸሸጊያ ነው። ፍርሃትና ስጋትን ሁሉ ያጠፋል። አላህ ትክክለኛውን ምርጫ እንዲያሳይሽ ከብዙ እና ብርቱ ዱዓ ጋር ደጋግመሽ [እስቲኻራ] አድርጊ።

ትዳር ላሠቡ ሁለት ጥንዶች የመጀመሪያ ትውውቅ እና መተያየት በመሀላቸው መፈቃቀድ እና ተቀራራቢ የነፍስ ፍሰት መኖሩን ለመፈተሽ ወይም ለማወቅ የሚጠቅም ነው። በዚህ ሂደት ዐይን በሚያየው አካላዊ ገፅታ አሊያም በንግግርና በውይይት መጣጣምና መፈቃቀድ ሊፈጠር ይችላል።

በዚህ የመጀመሪያ ትውውቅ ወቅት አላህ ከአንቺ ጋር ሁሌም እንደሆነ አስቢ፤ ራስሽን ብቻ ሁኚ፤ ምን መናገር ወይም መጠየቅ እንዳለብሽ በማሰብ ስሜትሽን አትረብሺ። እነዚህ ነጥቦች ለትክክለኛው ምርጫ ያግዙሻል።

ነገር ግን ይህ ሰው ትክክለኛ ምርጫ መሆኑን ለማረጋገጥ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች መሠረታዊ የሆኑ በርካታ ወሳኝ ነጥቦችን መመርመር እና ማጣራት ያስፈልግሻል።

1) ለእምነቱ ያለው ትኩረት ምን ያህል ነው? ሰላት በህይወቱ ውስጥ ምን ቦታ አለው?ከሰዓት ከመዘውተር እና ከሁኔታ አንፃር በትክክል ሰላቱን ይጠብቃል?

ትክክለኛውን የትዳር አጋር ለማግኘት እነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ማግኘት አለባቸው። ሰላቱን የሚጠብቅ ሰው ከአላህ ጋር ዘወትር የተሳሰረ ነው ፤ ከአላህገር የተሣሠረ ሰው አብሮ ከሚኖረው ሰው ጋር መልካም ግንኙነት እንደሚኖረው ይታመናል።

2) ለወላጆቹ ምን ያህል መልካም ነው? ለወላጆቹስ በጎ ነውን? ይህን ጥያቄ ቀጥሎ ማቅረብ ያስፈልጋል።

ለወላጆቹ መልካም ከሆነ አላህን የሚፈራ እና የአላህን ውዴታ የሚፈልግ ሰው ለመሆኑ አንድ ማስረጃ ነው።

※ ከነዚህ ምላሾች በመነሣት ከዚህ ሰው ጋር የህይወት ጥምረት መፍጠር እምነት የሚጣልበት መሆኑን እና አለመሆኑን መገምገም ይቻላል።

3) ከወንድሞቹ ፣ ከእህቶቹ ፣ ከጓደኞቹ፣ ከስራ ባልደረቦቹ አንዲሁም በዙሪያው ከሚገኙ ሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ተወዳጅ ሰው ነው? ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ እና ያልተረበሸ ነው? ለሰዎች ያለው አቀራረብ ለዛ አለው?

※ የእነዚህ ጥያቄዎች ምላሾች ደግሞ የማህበራዊ ግንኙነቱን ስኬታማነት ያሳያሉ።

4) የህይወት ታሪኩ ምን ይመስላል? ቢያንስ ስለዚህ አጭር ነገር ማወቅ የጎላ ማንነቱን ለማወቅ ጠቃሚ ነው። ዕውቀት በመፈለግ ባሳለፈባቸው ትምህርት ቤቶች ፣ ሪዝቅ በመፈለግ ባሳለፈባቸው የስራ ቦታዎች እንዲሁም ኑሮውን ባሳለፈበት መንደር ትቶት ያለፈውን የህይወት ጠረን ጥሩ ይሁን መጥፎ ማሽተት ያስፈልጋል።

※ መልካም ሽታ የመልካም ስነምግባር ውጤት ሲሆን መጥፎ ሽታ የመጥፎ ስነምግባር ውጤት ነው።

5) ተቀዳሚ ምልከታሽ ዲን ይሁን ፤ ገንዘብን ወይንም ማህበራዊ ክብርን ከዲን አታስቀድሚ፤ የነብዩ /የአላህ ሠላም እና ሰላት በእርሳቸው ላይ ይሁን/ የምክር ቃል ይህን ይላል፦

قال النبي صلى الله عليه وسلم: إذا أتاكم من ترضون دينه وخلقه فانكحوه

«እምነቱን እና ስነምግባሩን የወደዳችሁት ሰው የትዳር ጥያቄ ሲያቀርብ ተቀበሉት»

አደራ የምንልሽ ቤተሰቦችሽ የትዳር ጥያቄ ያቀረበውን ሰው አስመልክቶ የሚሰጡትን አስተያየት ቦታ እንዳትነፍጊው ነው። አስተያየታቸው በህይወት ተሞክሮዎች የተፈተሸ በመሆኑ ጠቃሚነቱ አያጠራጥርም።

የምታማክሪዉን ሰው ልታውቂ ይገባል። በእድሜ ላንቺ እኩያ ወይም ካንቺ ያነሱ ያልበሰሉ ወጣቶችን ካማከርሽ፤ ቁሳዊ መመዘኛን ተጠቅመው ወይም ከቅናት ስሜት በመነሳት የማይበጅሽን ሀሳብ ሊለግሱሽ ስለሚችሉ ተጠንቀቂ።

ሁልጊዜም ለአላህ ትእዛዝትና ገደቦች ጥንቁቅ ሁኝ። አላህን መፍራት ያማረ ፍፃሜ የሚገኝበት ብቸኛ መንገድ ነው።

وَالْعَاقِبَةُ لِلتَّقْوَىٰ

«መልካም መጨረሻም ለጥንቁቆቹ ናት ! » ጣሀ 132

©ተንቢሀት

www.facebook.com/tenbihat

ህዝቦች ላይ ግዴታ የሆኑ የነቢዩ ﷺመብቶች

ኡማው ላይ ዋጂብ የሆኑ የነቢዩ ﷺመብቶች ብዙ ናቸው። ጥቂቶችን የሁሉም ነቢያት መብቶችን ስንጠቅስ በጥቅሉ የጠቀስን ቢሆን ከዚህ ርዕስ ስር ነቢዩን በተለየ መልኩ የሚመለከት መብቶቻቸውን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

1 በሳቸው ነቢይነት በዝርዝር በማመን የሳቸውን መልዕክት የቀድሞ መልዕክተኞችን ሁሉ በመሻር የተቀየሩ መሆኑን መቀበል። አላህ እንዲህ ይላል

{ فَآمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَالنُّورِ الَّذِي أَنْزَلْنَا } (التغابن : 8)

‹‹በአላህና በመልክተኛውም። በዚያም ባወረድነው ብርሃን እመኑ።›› ተጋቡን 8

{ فَآمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ النَّبِيِّ الْأُمِّيِّ الَّذِي يُؤْمِنُ بِاللَّهِ وَكَلِمَاتِهِ وَاتَّبِعُوهُ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ } (الأعراف : 158)

‹‹በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ። ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።» አል አዕራፍ 158

{ وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانْتَهُوا } (الحشر : 7)

‹‹መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።›› አል ሀሽር 7

2 ነቢዩ ﷺመልዕክትን እንዳደረሱ አደራን እንደተወጡና መልካም የተባለን ሁሉ በመጠቀምና ክፋትን ሁሉ በመከልከል መልካም ምክርን እንደለገሱ ማመን። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا } (المائدة : 3)

‹‹ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።›› አል ማኢዳህ 3

አቡዳርዳእ እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

«وأيم الله لقد تركتكم على مثل البيضاء ، ليلها ونهارها سواء »

“በአላህ እምላለሁ ነጭ በሆነና ሌሊቱና ቀኑ እንደ በሆነ በግልፅ መንገድ ላይ ነው የተውኳችሁ።” (ኢብኑ ማጀህ 5)

ነብዩ ﷺመልዕክታቸውን እንዳደረሱ ሰሃቦች ነቢያችን ﷺየመሰናበቻ ሀጇ ባደጉበት ታላቅ ስብሰባ ላይ መስክረውላቸዋል። በዚህ ስብሰባ ላይ ነቢዩ ﷺግዴታዎችንና ክልከላዎችን ዘርዝረው በቁርአን ከመከሩ በኃላ ሰሃቦችን እንዲህ አሏቸው “ስለ እኔ ስትጠየቁ መልሳችሁ ምን ይሆናል? እነሱም መልዕክቱን እንዳደረስ ኃላፊነትን እንደተወጡና እንደመከሩ እንመሰክራለን። አሉ” ነቢዩም ﷺአመልካች ጣታቸውን ወደ ሰማይ ጠቁመው ወደ ሰዎች በማውረድ ሶስት ጊዜ “ጌታዬ ሆይ መስክር” አሉ። (ሙስሊም 1218)
አቡዘር እንዲህ ይላሉ
“ሙሐመድ ﷺከእውቀት ምንም አላስቀሩብንም ወፍ እንኳን ክንፉን እያርገበገበ አዩር ላይ ሲበር ከሱ ጋር የተያያዘ እውቀት ያማውቁን ነበር።” (አህመድ 5/153)
በዚህ ርዕስ ከቀደምት አበዎች የተዘገቡ ዘገባዎች ብዙ አሉ።

3 ነቢዩን ﷺከማንም ፍጡር ላይ ከራስም ጭምር አስበልጦ መውደድ። ነቢያትን መውደድ በጥቅሉ ግዴታ ቢሆንም ነገር ግን ነቢዩን ﷺከሌሎች ነቢያት ፍቅር በበለጠ ከአጠቃላይ ህዝብ ከዘመድ አዝማድ ከራስም ጭምር አስበልጦ መውደድ ግዴታ ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{ قُلْ إِنْ كَانَ آبَاؤُكُمْ وَأَبْنَاؤُكُمْ وَإِخْوَانُكُمْ وَأَزْوَاجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَالٌ اقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَارَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَاكِنُ تَرْضَوْنَهَا أَحَبَّ إِلَيْكُمْ مِنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ وَجِهَادٍ فِي سَبِيلِهِ فَتَرَبَّصُوا حَتَّى يَأْتِيَ اللَّهُ بِأَمْرِهِ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْفَاسِقِينَ } (التوبة : 24)

«አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፣ መክሰራዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልክተኛው በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደኾኑ አላህ ትእዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ» በላቸው። አላህም አመጸኞች ሕዝቦችን አይመራም። (አል ተውባህ 24)

ቡኻሪና መስሊም ከአባስ በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

«لا يؤمن أحدكم حتى أكون أحب إليه من والده وولده والناس أجمعين »

“እናንተ ዘንድ ከወላጅ ከልጆችሁና ከሁሉም ሰው በላይ ተወዳጅ እስካልሆንኩ እምንታችሁ የተሰተካከለ አይሆንም።” (ቡኻሪ 15 መስሊም 49)

በአንድ ወቅት ዑመር ለነቢዩ ﷺ“የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እርሶን ከነፍሴ ብቻ አላስበልጦ እንጂ ከሁሉ ነገር በላይ እወዳታለሁ” ሲላቸው “በፍፁም ነፍሴ በእጇ ባለው እምላለሁ ከራስህ አስበልጠህ እስካልወደድከኝ ኢማንህ ገና ነው” አሉት ዑመርም **እንዲህ** *አላቸው “አሁን በአላህ እምላለሁ ከነፍሴ አስበልጬ እወዶታለሁ” ነቢዩም ﷺ“አሁን ገና ዑመር” አሉት።” (ቡኻሪ 6632)*

4 ነቢዩን ﷺማላቅና ማክበር። አላህ እንዲህ ይላል

{ لِتُؤْمِنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ وَتُعَزِّرُوهُ وَتُوَقِّرُوهُ } (الفتح : 9)

‹‹በአላህ ልታምኑ፣ በመልክተኛውም (ልታምኑ)፣ ልትረዱትም፣ ልታከብሩትም።›› ፈትህ 9

{ فَالَّذِينَ آمَنُوا بِهِ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَاتَّبَعُوا النُّورَ الَّذِي أُنْزِلَ مَعَهُ أُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ } (الأعراف : 157)

‹‹እነዚያም በእርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከእርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው።›› አል አዕራፍ 157

{ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تُقَدِّمُوا بَيْنَ يَدَيِ اللَّهِ وَرَسُولِهِ }

(الحجرات : 1)

‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልክተኛው ፊት (ነፍሶቻችሁን) አታስቀድሙ።›› ሁጅራት 1


{ لَا تَجْعَلُوا دُعَاءَ الرَّسُولِ بَيْنَكُمْ كَدُعَاءِ بَعْضِكُمْ بَعْضًا }

(النور : 63)

‹‹በመካከላችሁ የመልክተኛውን ጥሪ ከፊላችሁ ከፊሉን እንደ መጥራት አታድርጉት።›› ኑር 63

ሙጃሂድ ይህን አንቀጽ ሲያብራሩ “የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ብለው በዝግታና በስርአት እንዲጠ ሯቸዉ በማዘዝ አንተ ሙሐመድ ብለው እንዳይጠሯቸው ከለከለ። ሰሃቦች ነቢዩን ﷺበማክበር ተመሳሌት እንደነበሩ የኢማም ኢብን ሸሪክ ንግግር ይጠቁማል “አንድ ጊዜ ወደ ነቢዩ ﷺሰሄድ በዙሪያቸው ሰሃቦች ራሳቸው ላይ ወፍ እንዳለ ሆነው ተቀምጠው አገኘሁ።”

ነቢዩን ﷺማላቅ በህይወቱ እያሉ ግድ እንደሆነ ሁሉ ከሞቱም በኃላ እሳቸውን ማክበር ግዴታ ነው። ቃዲ ዒያድ እንዲህ ይላሉ “የነቢዩን ﷺክብር መጠበቅና የላቀ አክብሮት መለገስ ከሞቱም በኃላ ቢሆን በህይወት ሳሉ ግድ እንደሆነው ሁሉ ግዴታ ነው። ከሞቱ በኃላ እሳቸውን ማክበር የሚገልፀው እራሳቸው በሚወሱበት ጊዜ፣ ሀዲስና ሱናቸው ሲነገር፣ ስማቸውና ታሪካቸው በሚደመጥ ጊዜ ነው። እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውን፣ ባልደረቦቻቸውንና ዘራቸውንም ማክበር ለአክብሮታቸው መገለጫ ነው።”



5 እሳቸው ላይ አብዝቶ ሰላትና ሰላም ማውረድ። አላህ እንዲህ ይላል፡-

{إِنَّ اللَّهَ وَمَلَائِكَتَهُ يُصَلُّونَ عَلَى النَّبِيِّ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا صَلُّوا عَلَيْهِ وَسَلِّمُوا تَسْلِيمًا } (الأحزاب : 56)

<<አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ የማክበርንም ሰላምታና ሰላም በሉ>> አል አህዛብ 56

አብደላህ ኢብን አምር ኢብኑል ዓስ በአስተላለፉት ሀዲስ ﷺእንዲህ ብለዋል

« من صلى علي صلاة صلى الله عليه بها عشرا »

"እኔ ላይ አንድ ጊዜ ሰላት ያወረደ አላህ እሱ ላይ አስር ጊዜ ያወርዳል።" (ሙስሊም 384)

ዓሊይም በአስተላለፉት ሀዲስ ነቢዩ ﷺእንዲህ ይላሉ

« البخيل الذي من ذكرت عنده فلم يصل علي »

"ስስታም ማለት እርሱ ዘንድ ስሜ ተነስቶ ሰላት የማያወርድብኝ ነው።" (ቲርሚዚይ 3546)

ሰላትና ሰላም በሁሉም ነቢያት ላይ ተገቢ ቢሆንም ነገር ግን ነቢያችን ﷺላይ ይበልጥ ተፈላጊ ነው። እንዲያውም አንዳንድ ዑለማዎች እንዳሉት እሳቸው ላይ ሰላትና ሰላም ማውረድ ዑለማዎች የሚስማሙበት ግዴታ ነው። ቃዲ ኢያድ እንዲህ ይላል "ነቢዩ ﷺላይ ሰላት ማውረድ ጊዜ ሳይወሰን በጥቅሉ ግዴታ ነው። ምክንያቱም አላህ ያዘዘው ተግባር በመሆኑና የዑለማዎችም የተስማሙበት ጉዳይ ስለሆነ።"

6 ለነቢዩ ﷺተገቢ በሆኑ ደረጃዎችና መለያዎችን ማመን። ከላይ የተጠቀሱ የነቢዩን ﷺየላቁ ማዕረጎችን ማመን ማወደስ፣ ለሰዎች ማሰራጨትና ለህግናትም ማስተማር።

7 ነቢዩ ﷺላይ ድንበር ከማለፍ መጠንቀቅ። አላህ ለነቢዩ ﷺህዝቦችን እንዲህ እንዳሉ ያዛል።

{ قُلْ إِنَّمَا أَنَا بَشَرٌ مِثْلُكُمْ يُوحَى إِلَيَّ أَنَّمَا إِلَهُكُمْ إِلَهٌ وَاحِدٌ فَمَنْ كَانَ يَرْجُوا لِقَاءَ رَبِّهِ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَالِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِ أَحَدًا } (الكهف : 110)

«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጢያችሁ ሰው ብቻ ነኝ። የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ። በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው። *(አል ከህፍ 110)*

{ قُلْ لَا أَقُولُ لَكُمْ عِنْدِي خَزَائِنُ اللَّهِ وَلَا أَعْلَمُ الْغَيْبَ وَلَا أَقُولُ لَكُمْ إِنِّي مَلَكٌ إِنْ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَى إِلَيَّ } (الأنعام : 50)

«ለእናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልልም። ሩቅንም አላውቅም። ለእናንተም እኔ መልአክ ነኝ አልልም። ወደእኔ የሚወርድልኝን እንጅ ሌላን አልከተልም» በላቸው። *(አል አንዓም 50)*

በዚህ አንቀፅ አላህ ነቢዩ ነቢይነታቸውን ብቻ እንዲያፀድቁና ከአላህ ጌትነትና ስልጣን የጋራ እንዳልሆኑ ግልፅ እንዲያደርጉ ያዛል።

ነቢዩም ﷺእሳቸውን በማወደስና በማሞካሸት ድንበር እንዳይታለፍባቸው አስጠንቅቀዋል።

ኢማም አል ቡኻሪ ከኡመር ኢብኑል ኸጣብ እንዳስተላለፉት ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል

«لا تطروني كما أطرت النصارى ابن مريم فإنما أنا عبده ، فقولوا : عبد الله ورسوله »

"ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ ኢሳን በማወደስ ድንበር እንዳለፉበት እኔንም በማሞካሸት ወሰን አትለፉ።" (ቡኻሪ 3445)

ኢብኑ አባስ እንዳሉት "አንድ ሰው ወደ ነቢዩ ﷺጋር በመምጣት በአንድ ጉዳይ ካወራቸው በኃላ አላህና እርሶ የፈለጉት ሆነ ሲላቸው እሳቸውም
"የአላህ ቢጤ አደረከኝ አንዴ አላህ ብቻ የፈለገው ሆነ በል አሉት።" (ሙስነድ አህመድ 1/214)

ነቢዩ ﷺከሚገባቸው ደረጃ በማሳለፍ እሳቸው ላይ ድንበር እንዳይታለፍ በመከልከላቸው በየትኛውምም የወሰን ማለፍ አይነት እሳቸው ላይ ድንበር ማለፍ የተከለከለ ነው። ነቢዩ ﷺላይ ወሰን ከማለፍ አይነቶች ለምሳሌ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ እንዲህ አድርጉልኝ ፣ ይህን ፊዕሙልኝ በማለት ለመለመን ከልክል ነው። ይህ ድርጉት ድዓዕ በመሆኑ ዱዓን ዱዓን ከአላህ ውጭ ማድረግ አይፈቀድም። እንዲሁም ለነቢዩ ﷺማረድ ስለት ማቅረብ፣ በቀብራቸው ዙሪያ ጠዋፍ ማድረግ ወይም ወደ ቀብራቸው ዞሮ መስገድ እነዚህ ሁሉ ከልክል የሆኑ የድንበር ማለፍ አይነቶች ናቸው። አላህ እንዲህ ይላል

{ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ }{ لَا شَرِيكَ لَهُ وَبِذَلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ } { (الأنعام : 162 ، 163)

«ሰግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል። «ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)።
(አል አንዓም 162-163)

8 ከነብዩ ﷺመብቶች ውስጥ የርሳቸውን ሰሃቦች ቤተሰቦቻቸውንና ባለቤቶቻቸውን ማክበር አንዱ ነው። አላህ ሰሃባችን እንድናከብርና ምህረትንም እንድለምንላቸው ስላዘዘ እነሱን ከመጥላትና እነሱ ላይ ነውርን ከመፈለግ መጠንቀቅ ግድ ነው።

አላህ ሙሃጂሮችንና አንሳሮችን ከጠቀሰ በኃላ ከነሱ ቀጥሎ የሚመጣ ትውልድ ለነሱ ምህረትን እንዲጠይቅና ልቡ ላይ የነሱን ጥላቻ እንዳይሰፍርበት እንዲለምን እንዲህ በማለት ያዛል።

{ وَالَّذِينَ جَاءُوا مِنْ بَعْدِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَا اغْفِرْ لَنَا وَلِإِخْوَانِنَا الَّذِينَ سَبَقُونَا بِالْإِيمَانِ وَلَا تَجْعَلْ فِي قُلُوبِنَا غِلًّا لِلَّذِينَ آمَنُوا رَبَّنَا إِنَّكَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ } (الحشر : 10)

እነዚያም ከበኋላቸው የመጡት «ጌታችን ሆይ! ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምሕረት አድርግ። በልቦቻችንም ውስጥ ለእነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ። ጌታችን ሆይ! አንተ ርኅሩህ አዛኝ ነህና» ይላሉ። (ሀሽር 10)

ከነቢዩ ﷺቤተሰቦች መብት ዙሪያም አላህ እንዲህ ይላል

{ قُلْ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا الْمَوَدَّةَ فِي الْقُرْبَى } (الشورى : 23)

«በእርሱ (መልክቴን በማድረሴ) ላይ በዝምድና ውዴታን እንጅ ዋጋን አልጠይቃችሁም» በላቸው። (ሹራ 23)

የዚህን አንቀጽ ትርጉም ሲናገሩ ዑለማዎች እንዲ ብለዋል "ለአማኝ ተከታዮችህ ለእኔ ይዜላችሁ ለመጣሁት ምትክ ቤተሰቤን እንድትወዱ እንጂ ደሞዝ አልፈልግም" በላቸው ማለት ነው።

ሙስሊም ከዘይድ ኢብን አርቀም እንደአስተላለፉት ነቢዩ ﷺእንዲህ ብለዋል "እናንተ ሰዎች ሆይ እኔ ሰው እስከሆንኩ የጌታዬ መልዕክተኛ መጥቶብኝ ምላሽ ልሰጥ እችላለሁ (መሞቴ አይቀርም) ስለዚህ ለእናንተ ሁለት ታላላቅ ነገሮችን እተዋለሁ አንደኛው መመሪያና ብርሃን ያለው መፅሐፍ (ቁርአን) ይህን የአላህ መፅሐፍ አጥብቃችሁ ያዙ" በማለት ስለቁርአን ብዙ ካነሳሱ በኃላ "ሁለተኛው በቤተሰቦቼ አላህን አውሱ በቤተሰቦቼ አላህን አውሱ በቤተሰቦቼ አላህን አውሱ።"

የነቢዩ ﷺቤተሰቦች የተከበሩና ለነቢዩ ﷺየቀረቡ በመሆናቸው እንዲናከብራቸውና ደረጃቸውን እንዲንጠብቁላቸው አዘዙ። እንዲሁም ሰሃባዎችን እንድናከር እነሱን ከመስደብና ከማዋረድ እንድንጠነቀቅ እንዲህ ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

« لا تسبوا أصحابي فلو أن أحدكم أنفق مثل أحد ذهبًا ما بلغ مد أحدهم ولا نصيفه»

"ሰሃቦቼን አትስደቡ እናንተ የኡሁድ ተራራ አምሳያ ወርቅ ብትለቅሱ እንኳን የሰሃቦች አንድ እፍኝ እንደውም ግማሹንም አይስተካከልም።" (ቡኻሪ 3673 ሙስሊም 2541)

ሰሃቦችንና የነቢዩ ﷺቤተሰቦች ማክበርና መውደድ የሱና ተከታዮች መለያ የሆነ ዋና መሰረት ሲሆን እነሱን መጥላትና ማውረድ የጥመት መለያ ነው።

ኢማም አቡ ዘርዓህ እንዲህ ይላሉ :-
"አንድ ሰው ሰሃቦችን ሲያነውር ከገጠመህ መናፍቅ መሆኑን እወቅ።"

ኢማም አህመድም እንዲህ ይላሉ :-
"አንድ ሰው የአላህ መልዕክተኛ ሰሃቦችን በክፉ ሲያነሳ ከገጠመህ እስልምናውን ተጠራጠር።"

ከላይ የተጠቀሱት ለነቢዩ መብት መፈፀም ካለባቸው ተግባራት የተወሰኑት ናቸው።

ለ እህቶች

ሴት ልጅን የተመለከቱ አንዳንድ ህግጋት !

አይንን ሰበር ማድረግ

አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ከላይ እንዳሳለፍነው እንዲህ ብሏል።

" وَقُل لِّلْمُؤْمِنَاتِ يَغْضُضْنَ مِنْ أَبْصَارِهِنَّ

" ለምእመናትም ንገራቸው አይኖቻቸውን ይከልክሉ (ሰበር ያድርጉ) "

መቼም እንደሚታወቀው እይታን አለመቆጣጠር በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ለሚደረግ ህገ ወጥ ግንኙነት ቀዳሚው መግቢያ በር ነው። "የማያውቁት ሃገር አይናፍቅም" እንዲሉ አፍጥጦ የባጥ የቋጡን ከመመልከት እይታን መቆጣጠር ከተቻለ የጥፋቱ ሰለባ ከመሆን መትረፍ ይቻላል ።በተቃራኒው ግን አፍጥጦና አትኩሮ መመልከት ለዝሙት ከሚጋብዙ መንድርደሪያዎች አንዱ ነው። ስለዚህም ነው አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ዝሙትን ሲከለክል አትስሩት ሳይሆን አትቅረቡት በሚል እርም ያደረገው ።

وَلَا تَقْرَبُوا الزِّنَا ۖ إِنَّهُ كَانَ فَاحِشَةً وَسَاءَ سَبِيلًا [١٧:٣٢]

«ዝሙትን አትቅረቡ እርሱ በርግጥም መጥፎ ስራ ነው ።መንገድነቱም ከፋ» (አል ኢስራእ : 32)

እንግዲህ በዚህ መሰረት ሙስሊሟ ሴት አይኖቿን ሰበር የምታደርግና እይታዋን የምትቆጣጠር ነች። በሂጃብ ተደብቂያለሁ ብላ የአላህን ክልከላት አሻፈረኝ በማለት አይኖቿ ዙሪያ ጥምጥሙን የሚያማትሩ አይደለችም። በዘመናችን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መስኮት የሚቀርቡ ባእድ ወንዶችንም አፍጥጦ መመልከት እዚህ ውስጥ ይገባል ። ከኡሙ ሰለማ በተወራው ሃዲስ ላይ ኡሙ ሰለማ ረዲየለሁ ዓንሃ እንዲህ ብላለች። እኔና መይሙና ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ዘንድ ነበርን። ኢብን ኡሙ መክቱም ወደኛ መጣ ። ይህም በሂጃብ ከታዘዝን በኋላ ነበር። ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ። "} "احتجبا منه!ከእርሱ ተሸፈኑ} ። እኛም አንቱ የአላህ መልእክተኛ ሆይ እርሱ የማያየንና የማያውቀን አይነስውር አይደለምን? አልናቸው። እርሳቸውም "

أفعمياوان أنتما ألستما تبصرانه؟ "

{ ታድያ እናንተም አይነስውር ናችሁን ትመለከቱት የለ?} ። አሉ።

[አቡ ዳውድ 4112 ቲርሚዚ 2778። (አልባኒ ደኢፍ ብለውታል ኢርዋእል ገሊል ሊልአልባኒ 6)211)]

እዚህ ጋር እንግዲህ አማኟ ሴት የነቃች መሆን አለባት። ምክንያቱም ድሮ ድሮ ለሴት ልጅ ፈታኝነትም ይሁን መፈተን የሚፈራው መውጣቷ ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን ይህ ፍርሃት በቤት ውስጥም ሁኗልና አማኟ ሴት ይህን በአጽኖ ልትረዳው ይገባል። እዚህ ጋር አንድ የሚጠቀስ አባባል አለ ።እርሱም አላህ ይዘንለትና የኢብኑ ሲሪን ንግግር ነው። እንዲህ ይላል ፦ "በአላህ ይሁንብኝ በህልሜ አንዲት ሴት አይና የማትፈቀድልኝ (እጅጉብይ) በመሆኗ አይኔን ሰበር እደርጋለሁ" ታሪኽ ባግዳድ 5/336 ። ሱብሃነላህ እርሱ በህልሙ ይህን ካደረገ እኛስ በእውናችን ምን ላይ ነው ያለነው?

በጫማ መሬትን መምታት (አጉል እርምጃዎች)

አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ብሏል።

وَلَا يَضْرِبْنَ بِأَرْجُلِهِنَّ لِيُعْلَمَ مَا يُخْفِينَ مِن زِينَتِهِنَّ

"ከጌጣቸውም የሚሸፍኑት ይታወቅ ዘንድ በእግሮቻቸው (መሬትን) አይምቱ") ኑር 31)

እንደሚታወቀው በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለው ስሜት ግለትና ተነሳሽነቱ ረቂቅ በሆነ መንገድ ነው : : ታዲያ አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) የፈጠረውን አዋቂ ነውና በዚህ በረቀቀ መልኩ እንኳ ሳይቀር ተቀስቅሰው ወደ ውድመት ሊወስዱ የሚችሉ በሮችን ሁሉ ዘጋግቷል : : ከዚህም ውስጥ ሴትን ልጅ ወንዱን ለማማለልና እይታውን ለመሳብ በምትራመድበት ጫማ ላይ የምታደርገው የእየኝ ጥሪ ድምጽን እንዳታደርግ መከልከሉ ነው : : አዎ! አላህ (ሱብሃነሁ ወተዐላ) ከዚህ ድርጊት እንድትታቀብ አዟታል። እርሷም ይህንን ያለ ድርድር ፈጻሚ መሆን ይጠበቅባታል : : የአላህን ትእዛዝ አሻፈረኝ ብለው ስሜታቸውን ከሚከተሉት አመፀኞች መመደብ የለባትም : : እነርሱ በየቀኑ ለዚህ ከንቱ አላማ የሚሆናቸውን ጫማ ለመግዛት በየሱቁ ሲንከራተቱ ይስተዋላሉ : : ኧረ አሁን አሁንማ አንዳንድ ሴቶች የሚጫሙት ጫማ እርዝመት በሜትርም ሳይለካ የሚቀር አይመስልም። ይህን ተጫምተው በሚራመዱበት ሰአት ደግሞ ፍጹም ተወዛዋዥ ዳንሰኛ እንጂ ከቱም ተራማጅ አይመስሉም : : ይገርማል እኮ : : ከአላህም ጋር ተጣልተው በገዛ ገንዘባቸውም በሽታን ሸምተው : : ምክንያቱም በህክምናውም ጥናት እንደተደረሰበት ተረከዙ የረዘመ (ታኮ) ጫማ መጫማት የሰውነት ክብደት ቀጥታ የሚያርፈው እርሱ ላይ ስለሆነ ኩላሊት ለመታመምና መሰል በሽታዎች ይጋለጣሉ : : አላህ ይጠብቀን : :

ድምጽ

አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) ለምእመናን እናቶች እንዲሁም ከእነርሱ በኋላ ለሚመጡት አማኝ ሴቶች እንዲህ ብሏል፤ -

يَا نِسَاءَ النَّبِيِّ لَسْتُنَّ كَأَحَدٍ مِّنَ النِّسَاءِ ۚ إِنِ اتَّقَيْتُنَّ فَلَا تَخْضَعْنَ بِالْقَوْلِ فَيَطْمَعَ الَّذِي فِي قَلْبِهِ مَرَضٌ وَقُلْنَ قَوْلًا مَّعْرُوفًا [٣٣:٣٢]

«የነብዩ ሴቶች ሆይ ከሴቶች እንደማናቸውም አይደላችሁም። አላህን ብትፈሩ (ትበልጣላችሁ) በልቡ ውስጥ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል በንግግር አትለሳለሱም። መልካም ንግግርን ተናገሩ» (አል አህዛብ : 32)

ድምጽ በተቃራኒ ጾታዎች መካከል ባለው ግንኙነት ከፍተኛ የሆነ ሳቢነትና ማግኔታዊ ሀይል አለው። አንዱን ወደሌላው ጠልፎ የሚይዝ ልዩ ወጥመድ ነው : : አላህ (ሱብሃነሁ ወተአላ) አማኝ ሴትን መልካምና ቁም ነገር ንግግሮችን መናገር እንጂ ድምጽን በማለሳለስና በማቅለስለስ ወንዶችን ከማማለል እንድትታቀብ አዟታል ።ምክንያቱም ይህ ሁኔታ በአድማጯ ልብ ውስጥ በሽታን ይፈጥራልና ነው።አዎ! ዝሙትን ያስናፍቃል። ለእርሱም ያነሳሳል ይገፋፋል። እዚህ ጋር የድምጽን የአቀያየር ስልት በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን ።

ንግግሩን ራሱ መቀየር ፡- ይህም ማለት አንዲት ሴት ተቃራኒ ፅወታዋን በምታናግርበት ሰአት የተለያዩ የማቆላመጫ ቃላቶችን በመጠቀም ማናገር ነው : : ምሳሌ፡-እከልፌ ስሙን ጠርታ ፣ፍቅሬ ፣ህይወቴና ወዘተ . . . ይህ ሁኔታ በቀጥታ መርዝ ነስናሽ አውዳሚ ነገር ነው : :

በንግግሩ ውስጥ መለሳለስ ፡- ይህ ደግሞ አንዲት ሴት ከተቃራኒ ፆታ ጋር መልካምና ቁም ነገር እያወራች ነገር ግን በውስጡ የምትጠቀማቸው የማለስለስ ፣የመጮተትና የመስለምለም ገጽታዎች ናቸው ፡:

ለማንኛውም አንዲት አማኝ ከየትኛውም የፈተና ሙከራዎች አላህን (ሱብሃነሁ ወተአላ) ፈርታ እራሷን ልታቅብ ይገባል።ምስጋና ለአላህ ተገባው። አትናገሪ አላላትም : : ነገር ግን ድምጿን ተገንና ግርዶ አድርጋ ወንዶችን የፈተናዋ ሰለባ እንዳታደርግ በአፅንኦ ከልክሏታል። በቃ እጥር ምጥን ቀልጠፍ ቆፍጠን ብሎ መልካምና ቁም ነገሮችን መናገር። ዛዛታና እሰጣ ገባ አለመፍጠር : : ሙሳ (ዓለይሂ ሰላም) ዘንድ የመጣችውን እንስት ሁኔታ እስኪ እናጢን። አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ሲል ገልፆታል።


فَجَاءَتْهُ إِحْدَاهُمَا تَمْشِي عَلَى اسْتِحْيَاءٍ قَالَتْ إِنَّ أَبِي يَدْعُوكَ لِيَجْزِيَكَ أَجْرَ مَا سَقَيْتَ لَنَا

" ከሁለቱ አንደኛይቱም ከእፍረት ጋር የምትሄድ ሆና መጣችው።አባቴ ለኛ ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠራሃል አለችው።" አል ቀሰስ 25።

ሌላው ቁም ነገር ደግሞ እስኪ አንቺ ውዲቷ እህቴ አስተውይ!። አላህ እኮ ይህን የከልከላውን ህግጋት መጀመሪያ ያወረደው አጼብ ድንቅ የነብዩ (ﷺ) ሚስቶችና የአማኞች እናት በሆኑት እንስቶች ላይ ነው።ታዲያ እኔና አንቺስ በምን መልኩ ነው መሆን የሚገባን??? እራስን መሸንገል አያዛልቅም : : ይልቁንም ያሉ ግድፈቶችንና መጥፎ ዝንባሌዎችን አርሞ ማስተካከል የብልህ ሰዎች መገለጫ ነው : : አደራ እህቴ ነቃ በይ ። አታላይ ሰዎች ሊሸነግሉሽ አይገባም።

ድብቅ አላማቸውን ለማራመድ ሲሉ አንዷ በአናሺዱ አንዷ በመንዙማው ድምፅሽ ሲስረቀረቅ ማጣጣም ይሻሉ። ኧረ ዛሬ ዛሬማ ቅልጥ ባለ ክላሲካል ሙዚቀኛም አድርገው የመለመሏቸው ለቁጥር ታክተዋል፤። የራዲዮናቸው ፤ የሰልፋቸው፤ የቲቪያቸው ማሟሟቂያ ያደረጓቸው ቀላል የሚባሉ አይደሉም። እናም እህቴ ነቃ ልትይ ይገባል። አላህ እውነቱን ከሃሰቱ ይግለፅልሽ። በኢስላም ውስጥ ሴት ልጅን የሚመለከቱ ዳሰሳዎችን እንደቀጠልን ነው : : አሁንም ከእርሷ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ብይኖች (አህካሞች) ከዚህ በታች ለማየት እንሞክራለን ።

በኡሙ ዐብደላህ ሙሐመድ



ለ እህቶች

የወር አበባ ጅማሬና መጨረሻ ጊዜ

ሴት ልጅ ዘጠኝ አመት እድሜ ሳይሞላት የወር አበባ ደም ሊኖርባት አይችልም። ምክንያቱም የትኛዋም ሴት ከዚህ እድሜ በፊት የወር አበባ ገጥሟት አያውቅም። ከዓኢሻም የሚከተለው ንግግራቸው ተዘግቧል "ልጃገረድ ዘጠኝ አመት ከሞላት ደረሰች ማለት ነው።" (ቲርሚዚይና በይሐቂይ)

በአብዛኛው ደግሞ ከሀምሳ አመት በኋላ የወር አበባ ደም አይኖርም። ከዓኢሻ እንደተዘገበው "አንድ ሴት ሀምሳ አመት ከሞላት የወር አበባ ጊዜዋን አልፋለች።" (አልሙጊ 1\406)

አነስተኛውና አብዛኛው የወር አበባ ጊዜ

ከውለማዎች አቋም ትክክለኛው ለወር አበባ ብዙ ትንሽ ቀነ ገደብ አለመወሰን ነው። ምክንያቱም ይህ በሴቶች ተለምዶ የሚወሰን ነው።

የተለመደው የወር አበባ ጊዜ

በተለምዶ በአብዛኛው ጊዜ የወር አበባ የሚቆየው ስድስት ወይም ሰባት ቀናት ነው። ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋል "የወር አበባሽን እስከ ስድስት ወይም ሰባት ቀን ጠብቂውና ታጥበሽ ሀያ ሶስት ወይም ሀያ አራት ቀናት ስገጂ።" (አቡዳውድና ቲርሚዚይ)

በወር አበባና በወሊድ ደም ወቅቶች የሚከለከሉ ነገሮች

በብልት ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፦

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

فَاعْتَزِلُوا النِّسَاءَ فِي الْمَحِيضِ ۖ وَلَا تَقْرَبُوهُنَّ حَتَّىٰ يَطْهُرْنَ البقرة: ٢٢٢

<<ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው። ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው።>>

(አል በቀራህ 222)

ነብዩም (ﷺ)ይህ አንቀፅ የወረደ ጊዜ ሲያብራሩት እንዲህ ብለዋል "ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጪ ሁሉን ነገር መፈፀም ትችላላችሁ።" ብለዋል:: (ሙስሊም ዘግበውታል)

የፍቺ ስነስርዓት፡- አላህ እንዲህ ብሏል፡-

إِذَا طَلَّقْتُمُ النِّسَاءَ فَطَلِّقُوهُنَّ لِعِدَّتِهِنَّ وَأَحْصُوا

الْعِدَّةَ الطلاق: ١

<<ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለዒዳቸው ፍቱዋቸው።>> (አል ጠላቅ 1)

የዑመር ልጅ ዓብደላህ ሚስታቸው የወር አበባ ላይ እያለች ፈተዋት ስለነበር ነብዩ ለዑመር እንዲህ "ሚስቱን እንዲመልሳት እዘዘው...." አሉት:: (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ሰላት መስገድ፡- ነብዩ (ﷺ)ለፋጢማ ቢንት ጀህሽ "የወር አበባሽ ሲመጣ ሰላት አቁሚ" ብለዋታል:: (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

መፆም፡- ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋል "ሴት ልጅ የወር አበባዋ በሚመጣ ጊዜ አትሰግድም አትፆምም" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ካዕባን ጠዋፍ ማድረግ፡- ዓኢሻ የወር አበባዋ ሲመጣ ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋታል "እስክትፀጂ ድረስ ካዕባን ጠዋፍ ከማድረግ ውጭ የተቀሩትን የሀጅ ስራዎች ሁሉ ፈፅሚ።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

ቁርአን ማንበብ፡-

ይህ የአብዛኞች ሰሃባዎች፣ ታቢዕዮችና ከነሱም ቡኋላ የመጡ ዑለማዎች አቋም ነው። ሆኖም ግን ለምሳሌ ቁርአንን በቃሏ የሸመደደች ሆኗ ለማስታወስ ወይም አስተማሪ ሆና ለተማሪዎች ለማስቀራት ለመሳሰሉ ጉዳዮች ቁርአን መቅራት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘችው ማንበብ ትችላለች። ይህ ካልሆነ ግን አንዳንድ ዑለማዎች እንዳሉት ባታነብ ይመረጣል።

ቁርአን መንካት፡- አላህ እንዲህ ብሏል

لَّا يَمَسُّهُ إِلَّا الْمُطَهَّرُونَ الواقعة: ٧٩

<<የተጥራሩት እንጅ ሌላ አይነካውም።>> (አል ዋቂዓ 79)

መስጂድ ውስጥ መቀመጥ፡-

ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋል "መስጂድን ጀናባና የወር አበባ ላለባቸው አልፈቅድም" (አቡዳውድ ዘግበውታል)

እንዲሁም "ዓኢሻ የወር አበባ ላይ ሆና ነብዩ (ﷺ)ከመስጂድ ወደ ክፍልዋ ራሳቸውን አስገብተውላት ታበጥርላቸው ነበር።" (ቡኻሪ ዘግበውታል)

መስጂድ ውስጥ በመንጠባጠብ የሚበክል ከሆነ ማለፍም አይፈቀድላትም። ይህ ካልሆነ ገን አትከለከልም።

የወር አበባ የሚያስገድዳቸው ነገሮች

ገላ ትጥበት፡-

ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋል "የወር አበባ የሚቆይብሽን ጊዜ ያህል ሰላት አቁሚና ከዚያ ታጥበሽ ስገጂ።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

አቅመ ሄዋን መድረስ፦ ነብዩ (ﷺ)እንዲህ ብለዋል " የወር አበባ የምታይ ሴት ያለ ሻሽ ሰላት ብትሰግድ አላህ አይቀበላትም።" (አቡዳውድ ቲርሚዚይና ኢብኑ ማጃህ)

በዚህ ሀዲስ ላይ የወር አበባ የምታይን ሴት ሂጃብን አስገድደዋታል። ግዴታ ደግሞ የሚጀምረው ለአቅመ ሄዋን በመድረስ ነው። ስለዚህ የወር አበባ መምጣት የመድረስ ምልክት ነው ማለት ነው።

ቀን ቀጠሮን በወር አበባ መቁጠር፡- የወር አበባ የምታይ ሴት ባሏ ከፊታት ሁለተኛ ሌላ ከማግባቷ በፊት የምትቆየውን ጊዜ መቁጠር ያለባት በወር አበባዋ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

وَالْمُطَلَّقَاتُ يَتَرَبَّصْنَ بِأَنفُسِهِنَّ ثَلَاثَةَ قُرُوءٍ البقرة: ٢٢٨

<<የተፈቱ ሴቶችም ነፍሶቻቸውን (ከማግባት) ሦስትን ቁርእ ይጠብቁ።>> (አል በቀራህ 228)

የማህፀን መጥራት የሚወሰነው በወር አበባ በመቁጠር ነው።

ማሳሰቢያ፦

ሴት ልጅ ከወር አበባዋ ወይም ከወሊድ ደም ፀሐይ ከመጥለቁ በፊት ከፀዳች የዕለቱን ዙህርና አስር ሰላት ቀደ መስገድ ሲኖርባት ጐህ ከመቅደዱ በፊት ከፀዳች ደግሞ የሌሉቱን መግሪብና ዒሻ ሰላቶች ቀደ መስገድ አለባት። ምክንያቱም ችግሮች በሚገጥሙ ጊዜ የሁለተኛው የሰላት ወቅት ለአንደኛው ይሆናል። ይህ የማሊክ ሻፊኢይ አህመድና የአብዛኞች ዑለሞች አቋም ነው።

አብዛኛው ና አነስተኛው የወሊድ ደም ጊዜ

ለአነስተኛ የወሊድ ደም ጊዜ ገደብ ስለሌለው ያለው ሁኔታ ይወስነዋል። አንዳንዴ በዝቶ ሌላ ጊዜ ደግሞ አንሶ ይገኛል። ብዙን ግን አርባ ቀን ነው። ቲርሚዚይ እንዲህ ብለዋል "የወሊድ ደም ያለባት ሴት ለአርባ ቀን ሰላት እንደምታቆም ዑለማዎች ተስማምተዋል። ነገር ግን ከዚያ በፊት ከፀዳች ታጥባ መስገድ ይኖርባታል።" ኡሙ ሰለማ ባስተላለፉትም ሀዲስ "በነብዩ (ﷺ) ዘመን የወሊድ ደም ያለባት አርባ ቀን ድረስ ሰላት ከመስገድ ትታቀብ ነበር።" (አቡዳውድ ቲርሚዚይና ኢብኑ ማጃህ ዘግበውታል)



ለ እህቶች

የበሽታ ደም

የወር አበባን ጊዜ የማይጠብቅ ከደም ስር መበጠስ የሚፈስ ደም ሲሆን ከወር አበባ ጋር በአይነትም ሆነ በሽረዓዊ ብይናቸው ይለያያሉ።

ይህ ደም በመፍሰሱ ጠሃራ ከመሆኗ የማትወገድ በመሆኗ ሰላት ፆምም ሆነ ህጋዊ ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም አትከለከልም። ለዚህ ማስረጃው ፋጢማ ቢንት አቢጀህሽ ያስተላለፉት ሀዲስ ነው። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኔ የወር አበባ ደም ሳያቋርጥ ይፈሰኛልና ሰላት መተው አለብኝ? በማለት ስትጠይቃቸው እንዲህ በማለት መለሱላት "አይ ይህማ የወር አበባ ሳይሆን የተበጠሰ የደም ስር ነው የተለመደው የወር አበባሽ ሲመጣ ሰላት አቁሚና ሲሄድ ደምሽን አጥበሽ ስገጅ።" (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)

የተለመደው የወር አበባ ጊዜዋ ሲያበቃ ገላዋን መታጠብ ግዴታዋ ሲሆን ለበሽታ ደሙ ደግሞ ሀፍረተ ገላዋን አጥባ የደም መውጫውን እንደ ጥጥ መሰል ነገር በመጠቀም አሽጋ ደም እንዳይፈስ ማድረግ አለባት። ወቅታዊ የሆነውን "ሞደስ" ብትጠቀምም የተሻለ ነው። ከዚያ ለእያንዳንዱ የሰላት ወቅት ውዱእ እያደረገች ትሰግዳለች።

የበሽታ ደም የምታይ ሴት ሶስት አይነት ሁኔታዎች ይኖራታል፡-

አንደኛ፦

የወር አበባ መምጫ ጊዜዋ እርሷ ዘንድ የታወቀ ሊሆን ይችላል። ይህ ከሆነ በተለመደው ጊዜ የሚመጣውን ደም የወር አበባ አድርጋ ትቆጥረውና ሰላትና ፆምን ታቆማለች ይህ ጊዜዋ ሲያበቃ ደግሞ ታጥባ ትሰግዳለች። ከዚህ ውጪ ያለውን ደም እንደ በሽታ ደም ትቆጥራለች። ለዚህ ማስረጃው ነብዩ (ﷺ)ለኡሚ ሀቢባ እንዲህ በማለት የተናገሩት ሀዲስ ነው "የወር አበባሽ የሚቆይብሽን ጊዜ ያህል ሳትሰግጂ ቆይና ከዚያ ታጥበሽ ስገጅ።" (ሙስሊም ዘግበውታል)

ሁለተኛ፦

የተለመደ ጊዜ ከሌላትና ነገር ግን የወር አበባዋን ከበሽታ ደም የምትለይ ከሆነ ለምሳሌ የወር አበባዋ ጥቁር ወፍራም ሽታ ያለው ሆኖ የወር አበባን ባህሪ የያዘ ከሆነና የበሽታ ደሟ ደግሞ ቀይ ቀጭን ሽታ የሌለው ሆኖ የሌሎችን ደም ባህሪ የያዘ ከሆነ እንዲህ አይነቷ ሴት ሁለቱን በመለየት ትጓዛለች። ለዚህ ማስረጃው ነብዩ (ﷺ)ለፋጢማ ቢንት አቢ ሁበይሽ እንዲህ ያሏት ነው " የወር አበባ ደም ከሆነ ጥቁር ሽታ ያለው ነው ይሄኔ ሰላት ከመስገድ ተቆጠቢ ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን ውዱእ አድርገሽ ስገጅ ምክንያቱም ይህ ከደም ስር መበጠስ የሚመነጭ ነው።" (አቡዳውድና ሃኪም ዘግበውታል)

ሶስተኛ፦ የተለመደ ጊዜ ከሌላትና ደሞችንም መለያ ከሌላት የአብዛኞች ሴቶችን ተለምዶ በመውሰድ ስድስት ወይም ሰባት ቀናት ሰላትና ፆምን ታቆምና ከዚያ ታጥባ ሰላተና ፆሚን ትቀጥላለች። ለዚህም ማስረጃው ነብዩ (ﷺ)ለሀምና ቢንት ጀህሽ እንዲህ ያሏት ነው "ይህ የሸይጧን እርግጫ ነው የወር አበባሽን ስድስት ወይም ሰባት ቀናት አድረጊውና ከዚያ ስትፀጂ ሰላትና ፆምሽን ቀጥይ ይህ ለአንቺ በቂ ነው።"

(አቡዳውድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል)



መራቆት ስልጣኔ ከሆነ
እንሰሳቶች ቀድመውን
ስለተራቆቱ በስልጣኔ እንሰሳቶች
በልጠውናል ማለት ነው።

ሙስሊሟ ሴት ከጌታዋ ጋር

አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ነብዩን (ﷺ)ከመላኩ በፊት የነበረው የሰው ልጆች ሁኔታ ከመኖራቸው ይልቅ አለመኖራቸው የሚመረጥበት የጨለመና የዘቀጠ ነበር:: ያ ዘመን በተለየ መልኩ ደግሞ ለሴት ልጅ የነበረው ገጽታ ብእርሮች ቢጨመቁ ቃላቶች ቢቀመሙ እንኳ ዘግናኝና አሳዛኝ ሁኔታውን መግለጽ ይሳናቸዋል። ሙሉ ለሙሉ የወንድ ልጅ ባሪያ የነበረች በገዛ ንብረቷ ቀርቶ በገዛ እርሷነቷ ላይ እንኳ የመብት እንጥፍጣፊ የማያውቃት የበታችና ተረጋጭ ነበረች:: ስብእናዋን ሳይቀር የሚጠራጠር ሰው ነች ወይስ? የሚል ሙት ማህበረሰብ ውስጥ ለተአምር የምትኖር ነበረች። የሰቀቀንና የሲኦል ጉዞዋ በዚህ አያበቃም:: ይልቁንም ይህ አሰቃቂ ጉዞዋ ህይወት ተብሎ እንዳታጣጥመው እንኳን የእግር እሳት የሆነበት ያ አመጸኛ ሀብረተሰብ በእንስሳት ታሪክ እንኳን በውል ያልታወቀ የቅጣት ጅራፍን ከነህይወቷ በመቅበር አሳረፈባት ። አላህ {ሱብሃነሁ ወተዓላ} ይህን ሲናገር እንዲህ ብሏል።

" وإذا الموءودت سئلت (8) بأي ذنب قتلت9"

"ከነህይወቷ የተቀበረችውም ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ (8) በምን ወንጀል እንደተገደለች 9" (አተክዊር 8-9)

" وإذا بشر أحدهم بالأنثى ظل وجهه مسودا وهو كظيم 58 يتوارى من القوم من سوء ما بشر به أيمسكه على هون أم يدسه في التراب الا ساء ما يحكمون 59 "

"አንዳቸውም በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ እርሱ የተቆጨ ሆኖ ፊቱ ጠቁሮ ይውላል 58 በእርሱ ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት በውርደት ላይ ሆኖ ያያዘውን? ወይስ በአፈር ውስጥ ይደብቀውን? (በማለት እያምታታ) ከሰዎች ይደበቃል። ንቁ የሚፈርዱት (ፍርድ) ምንኛ ከፋ 59}" (አነህል 58-59)

ከዚህ በኋላ ግን እዝነትና ፍትህ መገለጫ ባህሪው የሆነው ታላቁ አምላክ (ሱብሃነሁወተዓላ) ይህን ህይወት ላለው አይደለም ለግኡዙ አካል እንኳ የማይበጀውን ከንቱ ትውልድ በዚህ የአረመኔነት ሜዳ እንዳሻው ሊቦርቅ አልፈቀደለትም:: ስለዚህም መሃይምነትን ሊያጠፋ እውቀትን ሊረጨ፣ ጭካኔን ሊገረስሱ እዝነትን ሊዘሩ ፣ጭቆናን ሊዋጉ ፍትህን ሊያነግሱ በጥቅሉ የሰው ልጆች ሲዋዥቁበት ከነበሩበት የፅልመት ጉዞ ወደ ብርሃን በአላህ ፍቃድ እንዲያወጡ ቁርአንን በማስያዝ ውዱ መልክተኛውን (ﷺ) አስነሳቸው:: አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ ይህን ሲናገር እንዲህ ብሏል።

الر ۚ كِتَابٌ أَنزَلْنَاهُ إِلَيْكَ لِتُخْرِجَ النَّاسَ مِنَ الظُّلُمَاتِ إِلَى النُّورِ بِإِذْنِ رَبِّهِمْ إِلَىٰ صِرَاطِ الْعَزِيزِ الْحَمِيدِ [١٤:١]

"አ ላ ራ (አሊፍ ላም ራ ይህ ቁርአን) ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አሸናፊ ምስጉን ወደሆነው ጌታ መንገድ ታወጣበት ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መፅሃፍ ነው" (ኢብራሂም 1)

ታዲያ ሙስሊሟ ሴት ይህን ጸጋ የቸራትን ነጻ ያወጣትን የተሟላና እንከን የለሽ ሃይማኖት የመረጠላትን ታላቁን ጌታዋን ከምንምና ከማንም በፊት አመስጋኝ ትሆናለች።ይህም የሚሆነው እርሱን በብቸኝነት በመገዛት ተውሂድ ይሆናል:: ስግደቷ ጾሟም ፍራቻ መመካቷም ተስፋ መከጀሏም ማረድ መሳሏም እንዲሁም ሌሎች ባጠቃላይ የአምልኮ ዘርፎች ፍጹም ለታላቁ ባለውለታዋ ልእሉ ፈጣሪዋ አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ብቻና ብቻ ነው የምታደርገው። በዚህ ላይ በርሱ አንድንም አካል አታጋራም ።መላኢካም ይሁን ነብይ ጋኔንም ይሁን ሷሊህ ዛፍም ይሁን ድንጋይ ፍጹም በራቁ ቁልፍ ነው:: አላህ (ሱብሃነሁወተዓላ) እንዲህ ይላል ፡-

قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ لَا شَرِيكَ لَهُ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُسْلِمِينَ

«ስግደቴም መገዛቴም ህይወቴም ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው በል ለእርሱ ተጋሪ የለውም በዚህም በማዋራት ታዘዝኩ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (አል አንዓም 162-163)

አዎ! ይህች እንቁ ሙስሊም ሴት አላህ (ሱብሃነሁ ወተዓላ) እና መልእክተኛው (ﷺ)ያዘዙትን በመታዘዝ የከለከሉትን በመከልከልና በመራቅ ትክክለኛ እጅ ሰጪነቷን አልያም ሙስሊምነቷን የምታረጋግጥ ናት:: አላህን (ሱብሃነሁ ወተዓላ) ስትገዛ መልእክተኛው ባስቀመጡትና በተገዙበት መንገድ ብቻ ነው::

የፈጠራ (ቢደዐህ) አባዜ ያልተጠናወታት ፍጹም መልእክተኛውን ተከታይ ናት:: በሁሉም የሂወት ዘርፏ አርአያ የምታደርገው እንቁ የሆኑትን ነብዩን (ﷺ)እና ውድ ባልደረቦቻቸውን (ሰሃባ)ን ብቻ ነው:: ቁርአንና ሱናን በሰሃቦች አልያም በሰለፎች ግንዛቤ ብቻና ብቻ ይዛ ነው የምትገዘው:: በየቀኑ ከዚህ ግንዛቤ ተቃራኒ ሆነው የሚፈለሰፉና የሚፈበረኩ የተዛቡ የሆኑ አመለካከቶችም ይሁኑ ስርጎ ገብ አንጃዎቹ ፍጹም አያፍረከርኳትም:: ምክንያቱም የማይሳሳት የማይሰረዝ የማይደለዝ የሆነውን የቁርአንና ሱና ብርሃንን ይዛ ስለምትጓዝ ነው::

በኡሙ ዑበደላህ ሙሐመድ

ሸሪዓዊ ፈውስ

ሩቃ

ሀ. ትርጉሙ፦

"ሩቃ" ሩቅያ ለተሰኘው የዓረብኛ ነጠላ ቃል ብዜት ሲሆን ሩቅያ ማለት በሽተኛን ለመፈወስ የሚነበነቡ ከቁርአንም ይሁን ከሀዲስ ጥቅሶች ማለት ነው።

ለ. ሸሪዓዊ ብይኑ፦

የተፈቀደ ነው። ከማስረጃዎች ውስጥ ዓውፍ ኢብኑ ማሊክ እንዳሉት

"በድንቁርና ዘመን በሽተኛ ላይ እናነብ ነበርና የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እንዴት ያዩታል? ብለን ጠየቅናቸው። እሳቸውም ምታነቡትን ግለፁልኝ፤ ማጋራት የሌለበት እስከሆነ ድረስ በሽተኛ ላይ ማንበብ ችግር የለውም አሉ" ሙስሊም ዘግበውታል

አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዲህ ብለዋል "የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ለቡዳ በሽታ፣ ለመነደፍና ቁስለት ሩቃ ማድረግ ፈቅደዋል" ሙስሊም ዘግበውታል

ጃቢር ኢብኑ ዐበደላህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል "ወንድሙን (ከህመሙ ለመፈወስ በመቅራት) መጥቀም የቻለ ያድርግ›› ሙስሊም ዘግበውታል

ከአዒሻ እንደተዘገበው የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ከኛ ውስጥ አንዱ ሲታመም በቀኝ እጃቸው እየዳበሱት እንዲህ ይሉ ነበር "የሰዎች ጌታ ሆይ! ጉዳትን አስወግድ፤ፈውሰው አንተ ፈዋሽ ነህ ከአንተ ሌላ ፈዋሽ የለም ህመምን በማያስቀር ፈውስ ፈውሰው" ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል

መ. መስፈርቶቹ፦

ሩቃ የሚፈቀደው ሶስት መስፈርቶች ሲሟሉ ነው:: እነሱም፥-

አንደኛ፥- ከአላህ ፈቃድ ውጭ ያድናል በሚል ሊታመን አይገባም። ከአላህ ፈቃድ ውጭ እንደሚጠቅም ማመን ሽርክ በመሆኑ የተከለከለ ነው።

ሁለተኛ፥- ሸሪዓን የሚጋጭ መሆን የለበትም። ለምሳሌ ከአላህ ሌላ መለመን ወይም ከጭንቅ እንዲገላግል ጋኔንን መጥራት የመሳሰሉት ከታከሉበት ሽርክ በመሆኑ ክልክል ይሆናል።

ሶስተኛ፥- ግልፅ የሆነ ትርጉም ያለው መሆን አለበት። ትርጉም የሌለው አተታ ከሆነ አይፈቀድም።

ኢማም ማሊክ እንዲህ በሚል ተጠየቁ "የታመመ ሰው ላይ መቅራት ይቻላልን? እሳቸውም እንዲህ በማለት መለሱ "በመልካም ቃላቶች ከሆነ ችግር የለውም።"

ሠ. ክልክል የሆነ ሩቅያ፥-

ከላይ የተጠቀሱ መስፈርቶች ያልተሟሉበት ሩቅያ በመሉ ክልክል ነው:: ለምሳሌ አንባቢው ወይም የሚነበብለት ሰው ሩቅያ ራሱን ችሎ ፈውስ ነው በሚል የሚያምን ከሆነ ወይም ሩቅያው የሽርክ የቢድዓ የመሳሰሉ ቃላቶችን ያቀፈ ከሆነ ወይም ደግሞ ትርጉም በሌለው አተታ ከሆነ አይፈቀድም።

ውድ አንባቢ ሆይ! ቁርአን ሁሉም መታከሚያ እንደሆነ ጥርጥር የለውም እንደዚሁም ለአማኞች መድሃኒት ነው። አላህ እንዳለው፥-

﴿ وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلْقُرْءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٌ وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ ۙ وَلَا يَزِيدُ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا خَسَارًا ﴿٨٢﴾ ﴾
الإسراء: ٨٢

"ከቁርአንም ለምእመናን መድሃኒትና እዝነት የኾነን እናወርዳለን፣ በዳዩችንም ኪሳራን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም"

(አል ኢስራእ 82)

በሌላም አንቀፅ እንዲህ ብሏል

وَلَوْ جَعَلْنَاهُ قُرْآنًا أَعْجَمِيًّا لَّقَالُوا لَوْلَا فُصِّلَتْ آيَاتُهُ ۖ أَأَعْجَمِيٌّ وَعَرَبِيٌّ ۗ قُلْ هُوَ لِلَّذِينَ آمَنُوا هُدًى وَشِفَاءٌ ۖ وَالَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ فِي آذَانِهِمْ وَقْرٌ وَهُوَ عَلَيْهِمْ عَمًى ۚ أُولَٰئِكَ يُنَادَوْنَ مِن مَّكَانٍ بَعِيدٍ [٤١:٤٤]

"በአጅምኛ የኾነ ቁርኣን ባደረግነው ኖሮ አንቀጾቹ « (በምናውቀው ቋንቋ) አይብራሩም ኖሯልን? (ቁርኣኑ) አጅምኛና (መልክተኛው) ዐረባዊ ይኾናልን?» ባሉ ነበር እርሱ ለእነዚያ ለአመኑት መምሪያና መፈወሻ ነው። እነዚያም የማያምኑት በጆሮዎቻቸው ውስጥ ድንቁርና ነው። (አይሰሙትም)። እነርሱም በእነርሱ ላይ እውርነት ነው። እነዚያ ከሩቅ ሰፍራ እንደሚጠሩ ናቸው።" (ፉሲለት 44)

በትክክለኛ ዘገባ የተወሩ መጠበቂያዎች፣ ሩቃና ጠቅላይ የዱዓ አይነቶች፥-

1 "የሰዎች ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ በሽታውን አስወግድልኝ ፣ አድነኝ አንተ አዳኝ ነህና። አንተ መድሃኒት ያደረገው ቢሆን እንጂ መድሃኒት የለም በሽታ የማያገኘውን መዳንን አድነኝ።" አህመድ ዘግበውታል

2 "ሙሉ በሆነው በአላህ ንግግሮች እጠበቃለው ከሁሉም ሰይጣናትናከእኩይ ሰው ተንኮል እንዲሁም ከመጥፎ ዓይን ሁሉ በአላህ እጠበቃለሁ።" የቡኻሪና የአህመድ ዘገባ

3 "ከተፈጠረ ተንኮል ሁሉ ሙሉ በሆነው በአላህ ንግግሮች እጠበቃለሁኝ" የአህመድ ዘገባ

4 "ከአላህ ቁጣ፣ ከቅጣቱ፣ ከባሮቹ ተንኮል፣ ከሰይጣን ጉትጎታና ሰይጣን እኔን ከመቅረብ ሙሉ በሆነው በአላህ ንግግሮች እጠበቃለሁ" አህመድ ዘግበውታል

5 "መልካሙም ሆነ ክፉውን የማያመልጣቸውና ምሉዕ በሆኑት የአላህ ቃላት ከፈጠረው ፍጡር ክፋት ከሰማይ ከሚወርድ ክፉ ነገር ከምድር ላይ ከተፈጠረም ክፉ ነገር ከርሷ ከሚወጣም ክፉ ነገር በለሊትም በቀንም ከሚከሰት ፈታኝ የሆነ ክፉ ነገር ከክፉ የለሊት ጎብኝም በመልካም የሚጐበኝ ሲቀር እንጠበቃለን እጅግ በጣም ሩህሩህ የሆንከው አምላክ ሆይ ፀሎታችንን ተቀበለን"

6 "በአላህ ስም አክምሃለሁ ከሚያስቸግርህ ነገር ሁሉ፣ ህይወት ካለው ተንኮል፣ ከምቀኛ አይን፣ አላህ ያድንህ፣ በአላህ ስም አክምሃለሁ" አህመድ ዘግበውታል

7 "አላህ ነፃ ያደርገሃል፣ ከሁሉም በሽታ ያድንሃል፣ ምቀኛ በተመቃኝ ጊዜ ከተንኮለኛ አይን ሁሉ።" ሙስሊም ዘግበውታል

8 "በአላህ ስም አክምሃለው፣ ከሚያስቀጣህ ነገር ሁሉ፣ ከምቀኛ ምቀኝነት፣ ከአይን ባልተቤት ሁሉ አላህ ያድንህ" አህመድ ዘግበውታል

9 በሽተኛው እጁን በሚያመው ሰውነት ላይ ያደርጋውና እንዲህ ይላል "ቢስሚላህ" ሶስት ጊዜ ከዚያም "በአላህና በችሎታው ከሚሰማኝ ህመም እጠበቃለሁ" የሚለውን ሶስት ጊዜ ይላል።



ጀነትን በዱንያ

የአኼራዋን ጀነት ለማግኘት የዱንያዋን ጀነት እንፈልጋት። ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ፤ «በዱንያ ላይ ጀነት አለችህ ሊገባባት ያልቻለ የአኼራዋን ጀነት መግባት ይሳነዋል» ብለዋል።

ከቀደምት ሰለፎች አንዱ ሰለዚህ የዱንያ ላይ ጀነት ሲናገሩ፤ «እኛ ያለንበትን ደስታና የልብ መረጋጋት ንጉሶች እና ልዑሎች ቢያውቁት ኖሮ፤ በሰይፍ በተፋለሙን ነበር» አላህ እንዳለው፤

[الَّذِينَ آمَنُوا وَتَطْمَئِنُّ قُلُوبُهُمْ بِذِكْرِ اللَّهِ الا بِذِكْرِ اللَّهِ تَطْمَئِنُّ الْقُلُوب] الرعد:28

[እነዚያ ያመኑ፥ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረጉ ናቸው፤ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ]

አል-ራዕድ 28

በዱንያም ሆነ በአኼራ ደስተኛ ለመሆን ከፈለግን፤ ከጌታችን ጋር ያለን ትስስር ጠበቅ አናድርግ። አትጠራጠር! የአላህን ውዴታ ማግኘት ከቻልክ እውነትም ደስተኛ እና የተረጋጋህ ነህ! ጀነትን በዱንያ ማለት ይኸው!

ሸሪዓዊ ፈውስ

ሩቃ

ድግምተኛ ሰይጣናትን ለመጥራትና ድግምትን ለመስራት የሚጠቀምባቸው መሰረተቢስ ፅሁፎችና ሰይጣናዊ መጠበቂያዎች

ነብዩላህ ሱለይማን u አላህን ከለመኑት በኃላ አንድም ግለሰብ ጋኔንን (ጂንን) በቁጥጥር ስር ሊያውለው ወይም አገልጋይ ሊያደርገው አይችልም።

﴿ وَلَقَدْ فَتَنَّا سُلَيْمَٰنَ وَأَلْقَيْنَا عَلَىٰ كُرْسِيِّهِۦ جَسَدًا ثُمَّ أَنَابَ ﴿٣٤﴾ قَالَ رَبِّ ٱغْفِرْ لِى وَهَبْ لِى مُلْكًا لَّا يَنۢبَغِى لِأَحَدٍ مِّنۢ بَعْدِىٓ ۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلْوَهَّابُ ﴿٣٥﴾ فَسَخَّرْنَا لَهُ ٱلرِّيحَ تَجْرِى بِأَمْرِهِۦ رُخَآءً حَيْثُ أَصَابَ ﴿٣٦﴾ ﴾ ص: ٣٤ - ٣٩

<<ሱለይማንንም በእርግጥ ፈተንነው። በመንበራም ላይ አካልን ጣልን። ከዚያም በመጸጸት ተመለሰ። ጌታዬ ሆይ! ለእኔ ማር። ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባንም ንግሥና ስጠኝ። አንተ ለጋስ አንተ ብቻ ነህና» አለ። ነፋሰንም በትእዛዙ ወደፈለገበት ሰፍራ ልዝብ ኾና የምትፈስ ስትኾን ገራንለት። ሰይጣናትንም ገንቢዎችንና ሰጣሚዎችን ሁሉ (ገራንለት)።ሌሎችንም በናንጀች ተቀራኞችን (ገራንለት) ።ይህ ስጦታችን ነው፡ ፡ያለ ግምት ለግስ ወይም ጨብጥ አልነው፡ ፡ > > (ዐድ 34 - 39)

ነብያችን ﷺ ከእለታት አንድ ቀን ለመስገድ በቆሙበት "አዑዙ ቢለሂ ሚንከ" ማለትም "ከአንተ በአላህ እጠበቃለሁ" አሉ ከዚያም "አል አኑከ ቢለእኒቲሂ" ማለትም በአላህ እርግማን እረግማሃለሁ" ሶስት ጊዜ ካሉ በኃላ የሆነ ነገር እንደሚቀበሉ እጃቸውን ዘረጉ። ሰላቱን በጨረሱ ጊዜ ሰሃባዎች እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ከዚህ በፊት ሰምተንህ የማናውቀውን በሰላት ውስጥ የሆነ ነገር ስትል ሰማንህ እጅህንም ስትዘረጋ ተመለከትንህ" አሏቸው እሳቸውም "የአላህ ጠላት ኢብሊስ የእሳት ችቦ በፊቴ ላይ ሊጥለው ይዞ መጣ ሶስት ጊዜ ከአንተ በአላህ እጠበቃለሁ አልኩኝ ከዚያም ሊይዘው ፈለኩኝ። በአላህ እምላለው የወንድሜ ሱለይማን ፀሎት (ዱዓ) ባይኖር ኖሮ የታሰረ ሲሆን የመዲና ህፃናት ይጫወቱበት ነበር።" ሙስሊም ዘግበውታል

በቡኻሪና በሙስሊም እንደተዘገበው አቢ ሁረይራ ከነብያችን ﷺ እንዳወራው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ "ሰይጣን ሰላቴን ለማቋረጥ በሀይለኛው ታገለኝና አላህ ረድቶኝ አንቄ ያዝኩት እናንተ ታዮት ዘንድ በምሶሶ ላይ ላስረው አሰብኩኝና "ከእኔ በኃላ ለአንድም የማይገባንም ንግስና ስጠኝ" የሚለውን የሱለይማንን ንግግር አስታወስኩኝ አላህ I ሰይጣንን የተዋረደ ሲሆን መለሰው።

እውነታው ይህ ከሆነ በደጋሚዎችና በሰይጣን መህከል ያለው ግንኙነት ምስጢሩ ምን ይሆን? የጅን ሰይጣናት በመጥፎ ነገር ላይ ደጋሚዎችን እንደሚያግዙ የታወቀ ነው። በመጥፎ ነገር ላይ ይታዘዟቸዋል ከጉዳያቸው የሚፈልጉትን ነገሮች ያስፈፅሙላቸዋል። ከሰይጣናት ጋር ያላቸውን ግንኙነት ታላቁ ምሁር አልቃዲ በድሩ አልዲን አቢ አብደላህ መሐመድ ቢን አብደላህ አልሸበሊ አልሀነፊ "አካሙ አልመረጃን ፊ አህካሚ አልጀን" በተባለው መፅሐፋቸው በአርባ ስምንተኛው ምዕራፍ ላይ ሲያብራሩ እንዲህ ይላሉ፡ - "ከሀዲያን ጂኖችና ሰይጣናት ከህደትን በአላህ ላይ ማጋራትንና በአላህ ላይ ማመፅን ይመርጣሉ። ኢብሊስና ከሰይጣን የሆኑ ሰራዊቶቹ እርኩስ ተግባርን ይፈልጋሉ። ተንኮልንም ይሰሩበታል ያሳድዱታልም ተግባራቸው ለቅጣት የሚዳርጋቸው እና የሚያጠሙትንም አካል ለቅጣት ቢዳርገውም እርኩስ ነፍሶቻቸው በምትፈልገው መሰረት በእነርሱ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ።

ኢብሊስ እንዳለው፡ -

﴿قَالَ فَبِعِزَّتِكَ لَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ () إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ الْمُخْلَصِينَ ﴾ ص: ٨٢ - ٨٣

"እርሱም አለ በአሸናፊነትህ ይሁንብኝ በመላ አሳስታቸዋለሁ ከእነርሱ ምርጥ የኾኑ ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ" (ሷድ 82 - 83)

﴿ قَالَ أَرَءَيْتَكَ هَٰذَا ٱلَّذِى كَرَّمْتَ عَلَىَّ لَئِنْ أَخَّرْتَنِ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ لَأَحْتَنِكَنَّ ذُرِّيَّتَهُۥٓ إِلَّا قَلِيلًا ﴿٦٢﴾ ﴾ الإسراء: ٦٢

<<እንዲህም አለ "ንገረኝ ይህ ያ በእኔ ላይ ያበለጥከው ነውን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስሀተት በእርግጥ አስባቸዋለሁ አለ።" (አል አስራእ 62)

አላህ እንዲህ አለ፡ -

﴿ وَلَقَدْ صَدَّقَ عَلَيْهِمْ إِبْلِيسُ ظَنَّهُۥ فَٱتَّبَعُوهُ إِلَّا فَرِيقًا مِّنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٢٠﴾ ﴾ سبأ: ٢٠

"ኢብሊስም በእነሱ ላይ ምኞቱን በእርግጥ ፈፀመ ከአመኑትም የኾኑት ቁፍሮች በስተቀር ተከተሉት።" (ሰባእ 20)

የሰው ልጅ ልቡ ወይም አእምሮው ከተበላሸ የሚጐዳውን ነገር መፈለግና በእርሱ መደሰት ይፈልጋል። እንደውም አእምሮውን፣ ሃይማኖቱን፣ ስነምግባሩን፣ አካሉንና ገንዘቡን የሚያበላሽ ነገርን በጣም ይናፍቃል። ሰይጣን እርኩስ መንፈስ ያለው ሲሆን የመድሃኒትና የእጣ ባለቤት የሆነው ወደእርሱ ለመቃረብ የጅኖችን ስም በመፃፍና የሚወዱትን እንደክህደት፣ በአላህ ላይ ማጋራትን እንደጉቦ በመስጠት ጉዳያቸውን እንዲፈፅሙላቸው ያደርጋሉ። ሊገደልለት የሚፈልገው ግለሰብ እንዲገደልለት ወይም በወንጀል ላይ እንዲተባበር አልያም አብሮ እንዲሰራ ገንዘብን እንደሚሰጥ ግለሰብ። ስለዚህ አብዛኞቹ እነዚህ ነገራቶች የአላህን ንግግሮች በነጃሳ (በርክሰት) ነገር ይፅፋቸዋል። "ቁል ሁወላሁ አሀድ" የሚለውን አልያም ሌላ አንቀፆችን በነጃሳ (በርክሰት) ወይም በደም ወይም ከነጃሳ ውጪ በሆነ ነገር ነገር ግን ሰይጣን በሚወደው ነገር ይፅፋሉ።አልያም ሰይጣን በሚወደው ነገር ላይ ይናገራሉ: : ሰይጣን በሚወደው ነገር ከተናገሩ ወይም ከፃፉ በፈለጉት አላማ ላይ ይረዳቸዋል። አልያም ከባህር በአንዱ ውስጥ እንዲሰምጡ ያደርጓቸዋል ወይም በአየር ላይ ራቅ ወዳለ ቦታ ተሸክመው ይወስዷቸዋል አልያም ከሰው የሆነን ገንዘብ ይዘውላቸው ይመጣሉ።

ከአጭበርባሪዎች ገንዘብ እና የአላህ ስም ያልተወሳበትን ሰይጣናት እንደሚሰርቁትና ሌሎች ነገራቶችንም ይዘውላቸው ይመጣሉ።

ስለዚህ ያላቸው ግንኙነት በአላህ በመካድ ላይ የተገነባ ነው። ሰይጣናት ደጋሚዎች በአላህ ላይ እስካልካዱ ድረስ ፊፅሞ አያገለግሏቸውም አይታዘዟቸውም። እንደሰይጣናት ፍላጐትና እንደደጋሚው አፈፃፀም በአላህ የመካዱ አይነት ይለያያል። አንዳንድ ጊዜ የአላህን አንቀፆች በሽንትና በሰገራ (አላህ ይጠብቀንና) በመፃፍ አንዳንድ ጊዜ ቁርአኑን ከቀዳደዱ በኃላ በቆሻሻ ውስጥ ወይም በሽንት ቤት በመጣል አንዳንድ ጊዜ ከአምስቱ የሰላት ወቅት ሱብሂ ወይም አስርን ለእነርሱ ድርሻ አድርጐ በመስገድ፣ አንዳንድ ጊዜ ሱጁድን ለእነርሱ በማድረግና እነርሱን በማላቅ እንዲሁም ሌሎችንም የክህደት አይነት ይፈፅማሉ።

ይህ ክህደት ከደጋሚው የሚከፈል ዋጋ መሆኑ ነው።

አላህ እንደተናገረው፡ -

﴿وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّىٰ يَقُولَآ إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ فَلَا تَكْفُرْ ۖ ﴾ البقرة: ١٠٢

"እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም" (አል በቀራህ 102)

ይህ አምልኮ የሚደረግለት ሰይጣን ከትላልቆቹ ሞገደኞች መህከል ነው። ከደጋሚው ይህ አምልኮ ሲረጋገጥለት የድግምትን አፈፃፀምና በሌላው ላይ እንዴት ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችል ያስተምረዋል። አላህ እንዳለው፡ -

﴿وَمَا كَفَرَ سُلَيْمَٰنُ وَلَٰكِنَّ ٱلشَّيَٰطِينَ كَفَرُوا۟ يُعَلِّمُونَ ٱلنَّاسَ ٱلسِّحْرَ ﴾ البقرة: ١٠٢

"ሱለይማን አልካደም (ድግምተኛ አልነበረም) ግን ሰይጣናት ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲኾኑ ካዱ" (አል በቀራህ 102)

ይህ ሁሉ ተግባራዊ የሚሆነው በመሰረተቢስ ፅሁፍና በሰይጣናዊ መጠበቂያ ሲሆን ደጋሚው ይህን ትምህርት ከትልቁ ሞገደኛው ይማርና በሰይጣናት ላይ ተፅእኖ በማሳደር የድግምቱን ስራ ይፈፅማል: : መሰረተ ቢስ የሆነው ፅሁፍና ሰይጣናዊ መጠበቂያ የተለያዩ አይነትና የተለያዩ ተግባራት ያላቸው ሲሆን ከፍተኛ ተፅእኖ የማድረግ ሀይል አላቸው። አንዳንድ ጊዜ ከቁርአን አንቀፆች ጋር በማያያዝ ወይም "በስመላን" አልያም የአላህ ስም ወይም የመላኢካዎችን ስም በመፃፍ ያገናኛሉ: : ይህን የሚያደርጉት

1. ለማመሳሰልና ለማታለል ነው።

2. በነዚህ በመታገዝ መሰረተቢስ በሆነው ፅሁፍና በሌሎች ስሞች በእነዚያ ከሰይጣን በሆኑ በወዳጆቻቸው ስም የሽርክ ተግባራቸውን እውን ለማድረግ ነው።



የሴቶች ውርስ

የሴቶች ውርስ በኢስላም

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው። የተቃና ለሆነው ሃይማኖት ለመራን፣ ህግጋቱንና ጥበቡን በመፅሐፉ ውስጥ (በቁርአን) እና በታማኙ መልዕክተኛው አንደበት ላብራራልን ሰላትና ሰላም ለአለማት ቅናቻ መመራትና እዝነት ለተላኩት የአላህ መልዕክተኛ ላይ ይሁን።

በሴት ልጅ የአወራረስ ሂደት ዙሪያ የአላህ ዲን (ሃይማኖት) ጠላቶች ከሚያነሷቸው ማደናበሪያዎች ውስጥ አንዱ የውርስ ጉዳይ ነው። ይህ ንግግራቸው የሚጠቁመው አላዋቂነታቸውን በመሆኑ እውነታው በዚህ ፅሁፍ ለማብራራት እንሞክራለን።

የሴቶች ውርስ የአላህ መልዕክተኛ ከመላካቸው በፊት እና አሁን ባሉ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ ያለው ሁኔታ

1 የሴቶች ውርስ በአይሁዶች ዘንድ

የአይሁዶች የአወራረስ ስርአት የሚለየው ሴቶችን ከውርስ መከልከላቸው ነው። ይህቺ ሴት ለሚኛ እናት፣ እህት፣ ልጅ ወይም ሌላም ብትሆን ድርሻ የሚሰጣት ወንድ ወራሾች ከሌሉ ብቻ ነው። ለምሳሌ፣ - ሴት ልጅ የምትወርሰው ወንድ ልጅ (ወንድም) ከሌለ ብቻ ነው የኢስራኤል ነብዩ እንዲህ በማለት ተናግሯል።

“ማንኛውም ወንድ ቢሞትና ወንድ ልጅ የሌለው ከሆነ የሱ ንብረት ወደ ሴት ልጁ ይሻገራል።” 11-1 27

ሚስት ደግሞ ከሚች ባሏ በምንም አይነት ሁኔታ አትወርስም።

2 የሴቶች ውርስ በሮማኒያዊያን ዘንድ

በሮማኒያዊን ዘንድ ሴት የዝምድና ቅርበቷ ምንም አይነት ቢሆንም እንኳ ከወንድ ጋር እኳል ትካፈላለች። ነገር ግን ሚስት ከሚች ባሏ አትወርስም፣ እንደነሱ ንብቻ ለመወራረስ ምክንያት አይሆንምና ነው። ይህም ውርስ ወደሌላ ቤተሰብ እንዳይሻገር ይጠቅማል እንደነሱ ውርስ የሚያገለግለው የሚችን ንብረት በቤተሰብ ውስጥ ማስቀረትና እንዳይበታተን መጠበቅ ነው። እናት ብትሞት ከአባቷ አግኝታው የነበረውን ድርሻ ወደ እህቶቿ ይዛወርና እኩል ይካፈሉታል። ወንድ ልጆቿም ይሁኑ ሴት ልጆቿ አይወርሳትም።

3 የሴቶች ውርስ ባደጉት ህዝቦች ወይም በቀድሞ ምስራቃዊያን ዘንድ

እዚህ ላይ መጥቀስ የተፈለገው እና ሌሎች ምስራቃዊንን ሲሆን እነዚህ ህዝቦር ከኢሳ መወለድ በፊት የጎርፍ አደጋ ከተከሰተባቸው በኃላ በምስራቅ የሚኖሩ ህዝቦችን ይመለከታል።

እንደነሱ ውርስ የተመሰረተው የበኩር ልጅን በአባቱ ምትክ በመተካት ነው። የበኩር የሆነ ወንድ ከሌላ ሌላ ለቤቱ ትልቅ የሆነ ወንድ ልጅ ይተካል፤ እሱም ከሌለ የሚች ወንድሞች፤ ከሌሉ አጎቶች እያለ ይቀጥልና በስተመጨረሻ በወንድ በኩል ወዳሉ አማቾች ይዛወራል። ከዚህም በተጨማሪ የአወራረስ ስርአቱን ለየት የሚያደርገው ሴቶችንና ህፃናትን ከውርስ ሙሉ ለሙሉ መከልከላቸው ነው።

4 የሴቶች ውርስ በቀደምት ግብፃዊን ዘንድ

የቀደምት ግብፃዊያን ቅርሶች እንደሚያመለክቱት የውርስ ስርአቱ የሚችን የቅርብ ቤተሰቦች ሁሉ ያጠቃልላል። አባቶች፣ እናቶች፣ ሴት ልጆች፣ ወንድ ልጆችን ወንድሞች፣ እህቶች፣ የአባት ወንድሞች፣ የእናት ወንድሞች፣ አክስትቶች፣ ሚስት፣ ሁሉም ቀሪ ንብረቱን እኩል ይካፈላሉ። በትልቅና በትንሽ፣ በወንድና በሴት መሐከል ምንም አይነት ልዩነት አይደረግም።

5 የሴቶች ውረስ በአረቦች ዘንድ

የአላህ መልዕክተኛ ﷺከመላካቸው በፊት አረቦች ራሱን የቻለ ወይም ለየት ያለ የአወራረስ ስርአት አልነበራቸውም ማለት ይቻላል። የሚከተሉት የምስራቃዊያንን የአወራረስ ዘይቤ ነበር። በእነሱ ዘንድ ውርስ የሚገደበው የጦር መሳሪያ መሸከምና መመከት በሚችል ወንድ ብቻ ነው። ሴትንና ህፃናትን ውርስ አይመለከታቸውም ምክንያቱም የጦርና የዘመቻ ህዝቦች ነበሩና።

ከዚህም በተጨማሪ ሴቶች አስገድደው ይወርሱ ነበር። ለምሳሌ ወራሽ ይመጣና ልበሱን የሚች አባቱ ሚስት ላይ ጣለ አርጎ እንዲህ ይላል “የአባቴንን ገንዘብ እንደወረስኩት ሁሉ እሷንም ወርሻታለሁኝ።” ከዚያም ሊያገባት ከፈለገ ያለ መህር ያገባታል ወይም ለፈለገው ሰው ይድራትና መህሯን ራሱ ይቀበላል ወይም እገዳ ይጥልባትና አይድራትምም ለራሱም አያገባትም። ይህንን በደል የእስላም ሽሪዓ የሚከተለው የቁርአን አንቀፅ በወረደ ጊዜ ክልክል አድርጓታል

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا يَحِلُّ لَكُمۡ أَن تَرِثُواْ ٱلنِّسَآءَ كَرۡهٗاۖ وَلَا تَعۡضُلُوهُنَّ لِتَذۡهَبُواْ بِبَعۡضِ مَآ ءَاتَيۡتُمُوهُنَّ إِلَّآ أَن يَأۡتِينَ بِفَٰحِشَةٖ مُّبَيِّنَةٖۚ وَعَاشِرُوهُنَّ بِٱلۡمَعۡرُوفِۚ فَإِن كَرِهۡتُمُوهُنَّ فَعَسَىٰٓ أَن تَكۡرَهُواْ شَيۡـٔٗا وَيَجۡعَلَ ٱللَّهُ فِيهِ خَيۡرٗا كَثِيرٗا ١٩ ﴾ النساء: ١٩

"እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ሴቶችን ያስገደዳችሁ ኾናችሁ ልትወርሱና ግልፀነ መጥፎ ስራ ካልሰሩ በስተቀር ከሰጣችኃቸው ከፊሉን ልትወርስዱ ልታጉላሏቸውም ለእናንተ አይፈቀድም በመልካምን ተኗኗሩዋው ብትጠሉዋቸውም (ታገሱ) አንዳችን ነገር ልትጠሉ አላህም በእርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይቻላልና።" አል ኒሳእ 19

በጥቂት ሁኔታዎች ላይ ሴቶችን የሚያስወርሱም በመሐከላቸው ነበሩ። በድርሻ ከወንድ እኩል ያካፍሏቸዋል ልክ እንደቀደምት ግብፃዊያንና ሮማናዊያን : :

የሴቶች ውርስ ኢስላም

የአላህ መልዕክተኛ ﷺከመላካቸው በፊት ሴቶች የነበሩበትን የአወራረስ ሁኔታንና የእንደዚሁም በታላቅነት ሳይሆን በስስትና በስሜታዊነት ላይ የተመሰረተው የተበላሸ የውርስ ስርአትና ደንብ ያደረሰውን በደል ከተመለከትን በኃላ፣ ኢስላም ብርሃኑንና ፍትሃዊነቱን ይዞ ይደርስባት የነበረውን ግፍና በደል ሊያስወግድላት፣ እሷም እንደወንድ ሰው መሆኗን ሊያረጋግጥላት፣ እንደዚሁም ልትዘናጋበትና ችላ ልትለው የማይገባ ኃላፊነቶች እንዳሉባት ሁሉ ማንም ሰው ሊካው ወይም ሊቀንሰው የማይችል መብት እንዳላትም ሊያረጋግጥላት መጣ።

የሴቶችን የአወራረስ ስርአት በኢስላም ውስጥ እንዲሁም የቀደሞውና የአሁኑ የአወራረስ ስርአትንና ህግጋትን አጠር ባለ ንፅፅር ስንመለከት የምናገኘው ውጤት እንደሚከተለው ይገለፃል፦

1 በእስልምና ውስጥ የሚችን ቀሪ ንብረት የማከፋፈሉን ኃላፊነት የወሰደው የሰው ልጅ ሳይሆን አላህ ነው። በዚህም የተነሳ አላህ ባይመራቸው ኖሮ የሰው ልጆች ሊመሩ በማይታሰብበት መልኩ የአከፋፈል ሂደቱ ስርአታዊ፣ ረቂቅና ፍትሃዊ ሆኗል። አላህም በቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል


﴿ ءَابَآؤُكُمۡ وَأَبۡنَآؤُكُمۡ لَا تَدۡرُونَ أَيُّهُمۡ أَقۡرَبُ لَكُمۡ نَفۡعٗاۚ فَرِيضَةٗ مِّنَ ٱللَّهِۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمٗا ١١ ﴾ النساء: ١١

"አባቶቻችሁና ልጆቻችሁ ለእናንተ በመጥቀም ማንኛቸው ይበልጥ ቅርብ እንደኾኑ አታውቁም። (ይኸውም) ከአላህ የተደነገገ ነው አላህ አዋቂ ጥበበኛ ነውና።" አል ኒሳእ 11

2 ኢስላም ብዙ ኃላፊነት ያለበትን ግምት ውስጥ አስገብቷል፤ ትንሽ ከሚያስፈልገው ይልቅ ብዙ ለሚያስፈልገው የበለጠ ድርሻ ሰጥቷል። ለዚህም ነው የልጆችን ድርሻ ከአባቶች ያስበለጠው ምክንያቱም ልጆች ህይወታቸውን ወደፊት የሚጋፈጡ ሲሆኑ አባቶች ደግሞ ለህይወት ጀርባቸው ሰጥተዋታል። እንደዚሁም ለወንድ ልጅ የሴትን ልጅ እጥፍ ድርሻ ተደርጐለታል። ያለጥርጥር ብዙውን ጊዜ ያ ባል ለመሆን የሚጠብቀው ወንድ ልጅ ለሚስቱ የሚከፍለው መህር ያስፈልገዋል፤ ልጆቹንም እሷንም ለማስተዳደር ወጪ ይጠብቀዋል። ስለዚህም ከእህቱ መህሯን በእጇ ይዛ የሚንከባከባትና ወጪዋን የሚሸፍንላት ግን ባሏ ነው።

3 ኢስላም ውርስን በንብረት ላይ ብቻ ገድቦታል። የአላህ መልዕክተኛ ከመላካቸው በፊት እንደነበረው ወደ ሚስት አይሻገርም። እንዲያውም የጋብቻ ትስስርን አክብሮታል በባለ ትዳሮች መሐከል በህይወት ዘመናቸው ፍቅርና እዝነትን ሲያደርግ በሞት ጊዜ ደግሞ ጋብቻን ለመወራረስ ምክንያት አድርጓታል እንደ አንዳንድ ህግጋቶች አልተወውም።

4 ኢስላም በዝምድና ምክንያት መወራረስን አልተወም። እንዲያውም በሰውየውና በቤተሰቡ መሐል ያለውን ታማኝ ግንኙነት ግምት ሰጥቶታል። ዝምድና ጥርት ካለ ስሜትና ከተሟላ ዝምድና የመነጨ የተፈጥሮ መብት አላት። አንድ ግለሰብ የሚጠናከረው በዘመዶቹ ሲሆን በህይወት ዘመኑም በእሱ ይፅናናል በሱም የተነሳ የተቻለውን ስጦታ አልግሎትና እርዳታ ይሰጣል። ከእንከብካቤም የመጀመሪያ ደረጃ ይሰጠዋል።



የሴቶች ውርስ

5 በቀድሞው የግብፃዊያን ውርስ ህግጋት መሰረት እንደሚደረገው በዘመዶች መሐከል እኩል ውርስን መካፈልን ኢስላም አይቀበለውም። ምክንያቱም የዘመዶች ድርሻ ከፍፍል ለተወራሽ በዝምድና ከመቅረብና ከመራቅ ጋር ተያያዥነት ስላለው ነው። ልጅነት ከአባትነት ቅድሚያ አለው አባትነት ደግሞ ከወንድምነት ይቀድማል እያለ ይቀጥላል።

ፈረንሳዊያንና ሮማዊያን እንዳደረጉትት ኢስላም በወንድማማቾች መሐል ውርስን እኩል አላደረገም እንዲያውም ወንድምነትን በሶስት ደጃፎች ከፍሏል (በሁለቱም ወላጆች፣ በአባት ብቻ፣ በእናት ብቻ የሚገናኙ) ይህንንም የደረጀ ሂደት በእርግጥ ጠብቋል። የሚወርሰው ጠንካራና የቅርብ ዝምድና ያለው ነው።

6 ነብዩ ﷺከመላካቸው በፊት ዓረቦች እንደሚፈፅሙት እንዲሁም የቀድሞ ምስራቃዊያን ህግጋቶች እንደሚያደርጉት ታላቅ ወንድ ልጅን ከወንድሞቹ በውርስ ድርሻ ነጥሎ የመስጠትን መርህ ኢስላም አላፀደቀም።

7 በኢስላም ወንድ ልጅ የበኩር በመሆኑ የተነሳ ከሌሎች ልጆች ምንም አይነት ብልጫ አያገኝም። የአይሁዶች ህግ የሄደበት አቅጣጫ የበኩር የሆነ ወንድ ልጅ ሲኖር የሌሎቹን እጥፍ ይወስዳል።

8 ኢስላም ሴት ልጅ ከወንድ ልጅ ጋር የወላጆቿን ውርስ የመካፈል መብትን ዋስትና ወስዶላታል። አይሁዶች እንደሄዱበት አካሄድ አይነት በወንድ ልጆች አይታገዱም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿لِّلرِّجَالِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ مِمَّا قَلَّ مِنْهُ أَوْ كَثُرَ ۚ نَصِيبًا مَّفْرُوضًا ۝٧﴾ النساء: ٧

"ለወንዶች ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት (ንብረት) ፈንታ አላቸው ለሴቶችም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ከርሱ ካነሰው ወይም ከበዛው ፈንታ አላቸው የተወሰነ ድርሻ (ተደርጓል)።" አል ኒሳህ 7

ከላይ የተጠቀሱትን ንፅፅሮች ከተመለከትን በኃላ ጉልህ የሆነው እውነታ ግልፅ ይሆንልናል። ይኸውም ጠቅለል ባለ መልኩ የኢስላም የውርስ ስርአት በተለይም ከሴቶች ጋር ተያያዥነት ያለው ከፍል የሰውን ልጆች የሩጫ እንቅስቃሴና ፍላጎት የሚስማማ ብቸኛ ህግ ሆኖ እናገኘዋለን። በሴቷ እንቅስቃሴና ፍላጎት የተነሳ የሚገባት የሆነ ነገር ውስጥ ጣልቃ በመግባት እንቅፋት አይሆንም።

የሴቶች ውርስ ያደነጋገግ ጥበብ

የሴቶች ውርስ ያደነጋግ ሂደቱን በጥሞና ያስተዋለ ሰው ብዙ ጥበቦችን ይመለከታል። ከነዚህም ውስጥ የተወሰነ ለመጥቀስ ያህል፡-

1 ሴት የሰው ልጅ መሆኗንና የወንድ ከፊይ መሆኗን ያረጋግጣል። እንደዚሁም እንደወንድ ንብረት የማፍራትና የማከናወን መብት ያላትና የሚገባት መሆኗን ያረጋግጣል። ይህም በውስጡ ሴትን ማክበር አለበት።

2 አላህ የሰውን ልጅ በምድር ላይ ተተኪ አድርጓታል፣ አልቆታልም። ምድርን የመገንባትና መልካሙን ከእሷ የማውጣቱን ኃላፊነት ሰጥቶታል። ይህንን ኃላፊነት በተቻለው መጠን እንዲወጣ የሚያግዘውን ስንቅም ሰንቆታል። ታዲያ ይህ የሰው ልጅ የሚለው ቃል ወንድንም ሴትንም እኩል በሆነ መልኩ ይመለከታል።

3 አላህ የሰው ልጆችን ወንድም ይሁን ሴትን የፈጠረበትን የተፈጥሮ ጥሪ ምላሽ ይሰጣል። ይኸውም ገንዘብን በቁጥጥር ስር የማድረግ ፍቅር አላህም እንዲህ ብላል፡-

إِنَّ الْإِنسَانَ لِرَبِّهِ لَكَنُودٌ * وَإِنَّهُ عَلَىٰ ذَٰلِكَ لَشَهِيدٌ * وَإِنَّهُ لِحُبِّ الْخَيْرِ لَشَدِيدٌ العاديات: ٦ - ٨

" ሰው ለጌታው ብርቱ ከሐዲ ነው። እርሱም በዚህ ላይ መስካሪ ነው። እርሱም ገንዘብን ለመውደድ በጣም ብርቱ ነው።" አል አዲያት 6 - 8

وَتَأْكُلُونَ التُّرَاثَ أَكْلًا لَّمًّا * وَتُحِبُّونَ الْمَالَ حُبًّا جَمًّا الفجر: ١٩ - ٢٠

"የውርስንም ገንዘብ የመሰብሰብን አበላል ትበላላችሁ። ገንዘብንም ብዙን መውደድ ትወዳላችሁ።" አል ፈጅር 19 - 20

4 ኢስላም ሴትን የንብረት ባለቤት ማድረጉ ለሷ የሚያስፈልጋትን ጉዳይ እንድትወጣበት እገዛም ቄምር ነው።

5 ልክ እንደወንድ ሁሉ በተለያዩ በጎ ስራዎች ላይ ወጪ በማድረግ ገንዘቧ አላህን እንድትገዛው እድል መስጠትም ነው።

6 ውርስን በወንድ መገደቡ ሙሉ ለሙሉ ይሁን በከፊል የበላይነት እንዲሰማው ሊያደርገው ይችላል እንዲሁም ለእኔ ብቻ ማለትንና (ራስ ወዳድነት) የበላይነት ስሜትን በግልፅ በውስጣዝው ያሳድጋል። ይህም የሴቶችን መብት በማጉደል አሊያም የሚገባቸውን በመከልከል እነሱን በመበደል ውስጥ እንዲዘፈቅ ይዳርገዋል።

7 ሴት ልጅ ትልቅም ትሁን ትንሽ የውርስ መብት እንዳላት በአላህ መፅሐፍ (ቁርአን) ና ቸር በሆነው መልዕክተኛው ፈለግ (ሱና) ውስጥ ተጠቅሷል

8 ከሚች ጋር ባለ የዝምድና ቅርበት አንፃር ሴት ከወንድ ጋር እንድትወርስ መወሰኑ ንብረቱ እንዲከፋፈልና ብዙ ቁጥር ያላቸው ተተኪዎች ዘንድ እንዲሰራጭ ያደርጋል። ይህም በገንዘቡ ተጠቃሚን የሚያበዛ ሲሆን ንብረትን በአንድ ግለሰብ ወይም በተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ በመገደብ እንዳይከማች ይከላከላል።

የሴቶች የውርስ ሁኔታ

"የሴቶች የውርስ መብት በኢስላም" በሚል ዙሪያ በሀዲስ ከተጠቀሰው ማወቅ እንደምንችለው ውርሷ እንደ ሴቷ ሁኔታ መለያየቱን ነው። በዚህ ዙሪያ በአላህ ፍቃድ የተወሰነውን የአወራረስ ሁኔታ ልየነትን እንጠቅሳለን።

ሴት ከወንድ እኩል የምትወርስበት ሁኔታዎች

1 የወላጆች ውርስ (እናትና አባት) ሚችን የሚወርስ ልጅ ከመኖሩ ጋር ያ ልጅ ሴትም ይሁን ወንድ ወይም የወንድ ልጅ ልጅ ካለ ሴትም ይሁን ወንድ ወዘተ እያለ ወደታች በደረጃ ቢወርድም።

አባት እና እናት እኩል ድርሻ ያኖራቸዋል

አላህ እንዲህ ብሏል

وَلِأَبَوَيْهِ لِكُلِّ وَاحِدٍ مِّنْهُمَا السُّدُسُ مِمَّا تَرَكَ إِن كَانَ لَهُ وَلَدٌ

"ለአባትና ለእናቱም ለርሱ ልጅ እንዳለው ከሁለቱ ለእያንዳንዱ ከሰድስት አንድ አላቸው።" *አል ኒሳህ 11*

2 ከሚች ጋር በእናት ብቻ የሚገናኙ እህትና ወንድሞች ውርስ ወንዶች ብቻ ወይም ወንድና ሴት ቢሆኑም ከውርስ አንድ ሶስተኛ ወስደው እኩል ይካፈሉታል።

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

"ወላጅም ልጅም የሌለው በጎን ወራሾች የሚወርስ ወንድ ወይም ሴት ቢገኝ ለርሱም (ለሟቹ) ወንድም ወይም እህት (ከእናቱ በኩል ብቻ የሆነ) ቢኖር ከሁለት ለእያንዳንዳቸው ከስድስት አንድ አላቸው። ከዚህም (ከአንድ) የብዙ ቢሆኑ እነርሱ በሲሶው ተጋሪዎች ናቸው።" አል ኒሳህ 12

3 የሴት አያትና የወንድ አያት በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከውርስ አንድ ስድስተኛ ይወስዳሉ። ለምሳሌ ግለሰብ ቢሞትና የእናቱ እናት፣ የአባቱ አባት፣ ወንድ ልጁ በህይወት ቢኖሩ ለእናቱ እናት አንድ ስድስተኛ ሲደርሳት ለአባቱ አባትም አንድ ስድስተኛ ይደርሰዋል የቀረውን ደግሞ ወንደ ልጁ ይወስደዋል።

ሴት ከወንድ ያነሰ የምትወርስበት ሁኔታዎች

የሴትን የአወራረስ ሂደት ያስተዋለ ሰው እንደሚረዳው ጠቅለል ባለ መልኩ የሷ ድርሻ ከወንድ የሚያንስ ሲሆን አንዳንዴ የወንዱን ግማሽ ስትወርስ አንዳንዴ ደግሞ ከግማሽ ትንሽ አንሶ ወይም ከፍ ብሎ ያገኘዋል። በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ወንድ የሁለት ሴቶችን ድርሻ ይሰጠዋል።

1 ወንዱና ሴቷ በእኩል ደረጃ ላይ ያሉ ከሆነ ይህ ደረጃ ወደታች ቢወርድም እንኳ ግን ወደታች ሲወርድ በሴት በኩል መሆን የለበትም። እነሱም ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ (እህቱ) ጋር፣ የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ከወንድ ልጅ ሴት ልጅ ጋር ቁጥራቸው ብዙ ቢሆኑም እና የመሳሰሉት ነገር ግን የልጅ ልጅ የመጣችው በሴት በኩል ከሆነ አትወርስም ለምሳሌ የሴት ልጅና የሴት ልጅ ልጅ ወንድ ልጅ።

2 በአንደኛ ደረጃ ላይ ያሉ ብቻ ለምሳሌ በእናትም በአባትም የሚገናኙ እህት (ቶች) ከወንድም (ሞች) ጋር፣ በአባት ብቻ የሚገናኙ እህት (ቶች) ከወንድም (ሞች) ጋር ይህ ግን ወደ ልጆቻቸው አይወርድም (በልጆቻቸው አይሆንም)። ለምሳሌ በእናትም በአባትም የምትገናኝ እህት ልጅ (ወንድ) ከወንድሟ ወንድ ልጅ ጋር (በእናትም በአባትም የሚገናኝ) ወይም በአባት ብቻ የሚገናኙ እህት ልጅ (ወንድ) በአባት ብቻ ከሚገናኙ ወንድሟ ልጅ (ወንድ) ጋር ምክንያቱም እነሱ ያላቸው የማህፀን ዝምድና ነውና።

3 በወላጅ ደረጃነት ያሉ ለምሳሌ አባት ከእናት ጋር ይህ የሚሆነው ሟች ወንድም ይሁን ሴት ልጅ ከሌለውና ወላጆቹ ለውርስ ብቻቸውን ከመጡ ወይም ሟች ብዚ እህትና ወንድም ከሌሉት (ሁለትና ከዚያ በላይ) በዚህ ጊዜ አባት የእናትን እጥፍ ይወስዳል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል

فَإِن لَّمْ يَكُن لَّهُ وَلَدٌ وَوَرِثَهُ أَبَوَاهُ فَلِأُمِّهِ الثُّلُثُ

"ለእርሱም ልጅ ባይኖረውና ወላጆች ቢወርሱት ለእናቱ ሲሶ አላት" አል ኒሳህ 11

ማለትም ለአባት የቀረው ሁለት ሲሶዎች አሉት::

የሴቶች ውርስ

4 በባለ ትዳሮች መሐከል። ይህ የሚኖነው አንዳቸው ከሞቱና ሌላኛ ወራሽ ከሆነ ነው። ሚስት ቀድማ ብትሞት ባል ቢሞት ኖሮ እሷ ከምትወርሰው አጥፍ ይወስዳል። ሚስት ብትሞትና ልጅ ባይኖራት ባሏ የንብረቷን ግማሽ ይወስዳል። ነገር ግን ልጅ ከላት አንድ አራተኛ ይወስዳል። ሚስት ደግሞ የዚህን ግማሽ ትወስዳለች ባል ቢሞትና ልጅ ባይኖረው አንድ አራተኛ ትወስዳለች የግማሽ ግማሽ ማለት ነው ልጅ ካለው ደግሞ አንድ ስምንተኛ ይሳጣታል የአንድ አራተኛ ግማሽ ማለት ነው።

ሴት ከወንድ የበለጠ የምትወርስባቸው ሁኔታዎች

አንዳንድ ሰው ሊገረምና እንዲሁም ሴት ከወንድ የበለጠ የምትወርስበት ሁኔታ አርቆ ሊያስብ ይችላል። ነገር ግን ይህን ከሚመስክሩ ምሳሌዎች ውስጥ የተወሰነውን እንጠቅሳለን።

1 አንድ ሰው ቢሞትና ሚስቱ፣ ሴት ልጁ፣ እናቱ፣ ሁለት በእናት ብቻ የሚገናኛቸው እህቶቹና አንድ በእናትም በአባትም የሚገናኘው ወንድሙ በህይወት ቢኖሩ ክፍፍሉ የሚሆነው ንብረቱ 24 ቦታ ይከፈልና ለሚስቱ 3 ድርሻ፣ ለእናቱ 4ድርሻ፣ በእናትም በአባትም ለሚገናኘው ወንድሙ 5ድርሻ ይሰጣል። በእናት ብቻ የምትገናኝ እህቱ በሴት ልጁ ምክንያት ትከለከላለች (እንዳትወርስ ትታገዳለች)፣ ሴት ልጁ ደግሞ 12 ድርሻ ይሰጣታል። በዚህ ሁኔታ ሴት ልጁ ከወንድሙ የበለጠ ትወስዳለች እንደዚሁም በሴት ልጁ ፈንታ የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ወይም ወደታች ቢወርድም ይህ ሁኔታ አይቀርም። እንደዚሁም በወንድሙ ቦታ በአባት ብቻ የሚገናኘው ወንድም ቢሆን ወይ አባት ቢሆን ወይ የአባቱ ወንድም ቢሆን (በእናትም በአባትም የሚገናኙ) ወይ የአባቱ ወንድም ሆኖ ግን በአባት ብቻ የሚገናኙ ቢሆንም ክፍፍሉ አይቀርም። ለሚች ልጅ መሆን ወላጅ ከመሆን ወይም ወንድም ከመሆን ቅድሚያ ይሰጣል።

2 አንዲት ሴት ብትሞትና ባሏ፣ሴት ልጅ፣ እህቷ (በእናትም በአባትም የምትገናኘት) በአባት ብቻ የምትገናኘት እህቷ በህይወት ቢኖሩ ንብረቱ 4ቦታ ይከፈልና ለባሏ አንድ ድርሻ፣ ለሴት ልጇ ሁለት ድርሻ፣ ለእህቷ (በእናትም በአባትም ለምትገናኘት) አንድ ድርሻ ይሰጣል። በአባት ብቻ የምትገናኘት እህት ግን በእናትም በአባትም በምትገናኘው እህት ምክንያት ትታገዳለች። በዚህ ሁኔታ ባል ሴት ልጅ ከምትወርሰው ግማሽ ይወርሳል። በሴቷ ልጅ ቦታ የወንድ ልጅ ሴት ልጅ ብትሆን ወይም በደረጃ ወደታች ቢወርድም እንኳ ሁኔታው አይቀየርም። እንደዚሁም በእናትና በአባት የምትገናኘት ወይ በአባት ብቻ የምትገናኘት እህት ብትሆንና ከእሷ ጋር የአባት ወንድም (ከእናትና አባት የሚገናኝ ወይም በአባት ብቻ) ቢኖርና ሟች ወንድም ይሁን ሴት ልጅ ከሌላት ይህን ጊዜ ከባል ወይም ከአንት የበለጠ ይወርሳሉ።

3 አንዲት ሴት ብትሞትና ባሏ፣ የወንድ ልጅ ሁለት ሴት ልጆችና የወንድ ልጅ የልጅ ልጅ (ወንድ) በህይወት ቢኖሩ ንብረቱ 12 ቦታ ይከፈልና ለባሏ 3 ድርሻ፣ ለወንድ ልጅ ሴት ልጆች 8 ድርሻ (ለእያንዳንዳቸው 4 ድርሻ ማለት ነው) የቀረው አንድ ድርሻ ደግሞ ለወንድ ልጅ የልጅ ልጅ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ የወንድ ልጅ ሴት ልጆች ከወንድ ልጅ የልጅ ልጅ (ወንዶች) ድርሻ የበለጠ ወስደዋል ምክንያቱም በደረጃ ከፍ ስለሚሉ ሲሆን የነሱ ድርሻም ከባል ድርሻ ይበልጣል።

ወንድ ሳይወርስ ሴት ብቻ የምትወርስበት ሁኔታ

1 ለምሳሌ አንድ ግለሰብ ቢሞትና፣ እናቱ፣ ሁለት ሴት ልጆቹ፣ ሁለት በአባት ብቻ የሚያገኛቸው እህቶች እንደዚሁም አንድ በእናት ብቻ የሚገናኘው ወንድሙ በህይወት ቢኖሩ ንብረቱ 8 ቦታ ይከፈልና ለእናት 2 ድርሻ፣ ለሴት ልጆቹ ለእያንዳንዳቸው አራት አራት ድረሻ ይሰጣቸዋል ለሁለት እህቶቹ (በአባት ብቻ የሚገናኙ) 2 ድርሻ ይቀርላቸዋል (ለእያንዳንዳቸው 1 ድርሻ ማለት ነው) በእናት ብቻ የሚገናኘው ወንድም በአባት ብቻ የሚገናኘው ወንድም ምክንያት ይታገዳል። እዚህ ላይ ወንድምም (በእናት ብቻ የሚገናኝ) ሳይወርስ ሴቶቹ ሁሉም ይወርሳሉ።

2 እድለቢስ አሰባ ባለበት ሁኔታ

ለምሳሌ አንዲት ሴት ብትሞትና፣ ባሏ፣ ሴት ልጇ፣ የወንድ ልጇ ወንድ ልጅ፣ የወንድ ልጇ ሴት ልጅ፣ አባቷና እናቷ በህይወት ቢኖሩ ንብረቱ 12 ቦታ ይከፈልና ለባሏ 3 ድርሻ፣ ለሴት ልጅ 6 ድርሻ፣ ለአባት አንድ ድርሻ ለእናት ደግሞ 2 ድርሻ ይሰጣታል። ለልጅ ልጆች ግን የሚተርፍ ምንም ነገር አይኖርም በዚህ ሁኔታ ታዲያ ሴት ልጅ ከባልም ከአባትም የበለጠ ወርሳለች እሷ እየወረሰች የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ ግን አልወረሰም። እናት እየወረሰች የወንድ ልጅ ወንድ ልጅ አልወረሰም።

3 በተጨማሪም ማንም የማህፀን ዝምድና ያለው ወንድ (ዝመድናው በሴት በኩል የመጣ) በቁጥር ውርሳቸው የተገደበላቸው ሴቶች ካሉ አይወርስም። ይህ ግን ሚስትን አያካትትም እንደዚሁም ውርሳቸው በቁጥር ያልተገደበላቸው ሴቶችም ካሉ አይወርሱም።

4 አንድ ወንድ ውርሱ በቁጥር የተገደበለትም ሆነ ያልተገደበለት ወራሽ ቢሆንና ውርስን ከሚያስከለክሉ ሁኔታዎች አንዱ እሱ ላይ ቢከሰት። ለምሳሌ ሆን ብሎ ወይም ሆን ብሎ ያደረገው በሚያስመስልበት ሁኔታ ተወራሽን ቢገድል እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት ለቆ ቢወጣ ይህን ጊዜ ለውርስ የምትገባዋ ሴት ያለ ወንዱ ትወርሳለች።

በጥቅሉ ጥርጣሬን በሚያስይዝ መልኩ ባለ ማስረጃ የጠቀስናቸው ምሳሌዎች የሚያስረዱት ውርስን በተመለከተ የአላህ ድንጋጌዎች አንድን ፆታ ከሌላኛው ፆታ እንደማያስበልጡና እንዲያውም ወንድንም ሴትንም ግምት ውስጥ ያስገባ፣ እውነትን፣ ሎጂክንና ፍትሃዊነትን የሚያስፈርድ ነው።

በሴቶች ውርስ ዙሪያ የተረጨው ብሽታና ለሱም የተሰጠ ምላሽ

በኢስላምና በፍትሃዊነቱ ዙሪያ ከተሰራጩ ብሽታዎች መሐከል በውርስ ላይ የሴትን መብት በመጠበቅ ከወንድ እኩል ማድረግ የሚለው ይገኝበታል።

ኢስላም በሁሉ የህይወት ዘርፍ ወንድንና ሴትን አንድ አይነት መሆን አለባቸው የሚለው ጉዳይ በትክክለኛ እውቀት ወይም ጉዳዩን በጥልቅ በመመልከት የተወሰደ አይደለም። በተለይ በዋነኝነት የሚችን ቀሪ ንብረት የማከፋፈሉ ሂደት ከባድ አለመሆኑን (በኢስላም) እውነት ለፈለገ ወይም በቦታው ተገኝቶ ጆሮውን ጣል ላደረገ የሚደበቅ አይሆንም። ኢስላም ከሚለይባቸው ነገሮች ትልቁ በእያንዳንዱ የውርስ አከፋፈል ሂደት ግልፅና ነባራዊውን ሁኔታ የጠበቀ መሆኑ ነው። ሁሌም ቢሆን ተፈጥሮን ግምት ውስጥ ያስገባ እንጂ ከተፈጥሮ የሚዘናበል ወይም የሚጋጭ አይደለም።

ኢስላም በአሁን ጊዜ ሰዎች ባህሪያቸውን እንዲያስተካክሉና እየተጣራ በዚህም ወደ ናሙና እና አርአያ ወደመሆኑ ሰዎች እንዲደርሱ ማድረግ ነው። ጥሪ የሚያደርገው የሰዎችን ተፈጥሮ ለመቀየር አይደለም በዚህም የተነሳ ተፈጥሮን መቀየር ይቻላል ብሎ አያገምትም ቢቻልም እንኳን በሰዎች ህይወት ወስጥ ጥቅምን ያስገኛል ብሎም አያምንም። ኢስላም የሚያምነው ከተፈጥሮ ጋር ተስማሚ ሆኖ በሚጓዝ መልኩ ከስተካከለ በኃላ በተቻለው መጠን የሰው ልጅ ወደ መልካም እንዲደርስ ማድረግ ነው። እንደዚሁም በወንድና በሴት ጉዳይ ላይ ነባራዊውን ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ መጓዝ ይኸውም ሰላማዊና ትክክለኛ የሆነ ተፈጥሮዋዊ አስተሳሰብ እኩል ሊያረጋቸው በሚችል ቦታ እኩል ማድረግ እንዲሁም በሚለያያቸው ቦታ መለያየት።

በኢስላም ውስጥ ያለው የአወራረስ ስርአት ጥበባዊ ከመሆኑም ባሻገር ፍትሃዊ ነው። በህጉ መሰረት እነማን እንደሚወርሱ ግልፅ አድርጓል። የአወራረስ ደረጃቸውንም ከሟች ጋር ባላቸው ቅርበትና በህይወት ውስጥ ሀብረተሰቡ የሚሰጣቸው ቦታ ግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን ይህም ቦታ ልክ የሚችን ንብረት እንደወረሱ ሁሉ የሱን ኃላፊነትና መዘዝ መሸከፍ የሚያስገድዳቸው ነው።

ይህም እውነታ ገሀድ የሚወጣበት ጊዜ ቅርብ ነው። በውርስ ላይ እኩልነትን ሲያፀድቁ ወጥቶ መሰራትና የማስተዳደር ወጪንም እኩል አካፍለዋታል፤ መሸከም ከምትችለው በላይ አሸክመዋታል። እሷ ቤት ውስጥም ትሰራለች እሱ ግን አይሰራም፣ ልጆቷን ትንከባከባለች እሱ አይንከባከብም በተጨማሪም ወጥታ ትሰራለች፣ ለራሷና ለምታስተዳድረው ወጪ ታደርጋለች። ታዲያ በዚህ ሂደት ውስጥ ያለው ነገር ሴትን መበደል ነው ያውም ለስራ ሳትወጣ የሚደርስባትን ችግርና መጠቀሚያ መመሆንን ግምት ውስጥ ሳናስገባ። ተጨባጩ ሁኔታ ይህ ለመሆኑ እኔ ዘንድ ያለው ማስረጃ ብዙና በቂ ነው።

የሴቶች ውርስ

ኢስላም ለሴት የወንድን ግማሽ እንዲሰጣት ሲወሰን የማስተዳደርንና ወጥታ በመስራቷ የሚደርስባትን ችግር አንስቶላት ነው። በየትኛውም ሁኔታ ይህንን ኃላፊነት አላሸከማትም እንዲያውም ጣጣዋን የሚሸፍንለት ተደርጓላታል የራሷ ገንዘብ ቢኖራትም እንኳ። ያቺ ሴት ልጅ ብትሆን ወይም እህት ወጪዋን መሸፈን በአባቷ ወይም በወንድሟ ወይም በሚያስተዳድራት ወንድ ላይ ግዴታ ነው። እናት ከሆነች ደግሞ በባሏ ወይም በወላጆቿ ላይ ግዴቴ ነው።

ታዲያ ኢስላም በእርግጥ ሴትን ከብዙ የኢኮኖሚ ጫናና የማህበራዊ ግዴታዎች ጠብቋታል ወንዱን ደግሞ የዚህን ኃላፊነትና ግዴታ አብዛኛውን ተሸካሚ አድርጎታል። በአጭሩ ወንድ ይሰጣል ሴት ትቀበላለች ስለሆነም ሰጪና ተቀባይ መሐከል ልዩነቶች አሉ።በዛ ያለ የኢኮኖሚ ኃላፊነት ላለበት ሰው በዛ አድርጎ መስጠት ፍትሃዊነትና እኩልነት የሚያስገድደው ነው።

ነገሩ የወንድንና የሴትን የህይወት ኃላፊነት በማመዛዘን ላይ እንጂ አንድን ፆታ ከሌላኛው በማሰበለጥ ላይ አይደለም። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው ወንድን ከሴት በውረስ ማስበለጡ በሁኔታዎች ሁሉ የሚከሰት አይደለም። በእርግጥ ሴት ከወንድ እኩል የምትወርስበት አጋጣሚዎች አሉ ለምሳሌ በእናት ብቻ የሚገናኙ እህትና ወንድሞች፣ እናትና አባት እንደዚሁም ሴት አያትና ወንድ አያት። እነዚህ የተዘረዘሩት በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ እኩል ይካፈላሉ።

አላህ በእናት ብቻ ስለሚገናኙ እህትና ወንድሞች እንደዚህ ብሏል

“ወላጅም ልጅም የሌለው በጎን ወራሾች የሚወርስ ወንድ ወይም ሴት ቢገኝ ለርሱም (ለሚቹ) ወንድም ወይም እህት (ከእናቱ በኩል ብቻ የሆነ) ቢኖር ከሁለቱ ለእያንዳንዳቸው ከስደስት አንድ አላቸው። ከዚህም (ከአንድ) የበዙ ቢሆኑ እነርሱ በሲሶው ተጋሪዎች ናቸው።” አል ኒሳህ 12

ስለ ወላጆች ውርስ ደግሞ እንዲህ ብሏል፡-

“ለአባትና ለእናቱም ለእርሱ ልጅ እንዳለው ከሁለቱ ለእያንዳንዱ ከስድስት አንድ አላቸው” አል ኒሳህ 11

እነዚያ ስም ለማጥፋት የሚጠባበቁ የሆኑ የኢስላም ጠላቶችና እነሱን በጭፍን የሚከተሉ አላዋቂ ሙስሊሞች እየተቀባበሉ በኢስላም ላይ የሚረጩትን ብዥታ፣ ጊዜያዊ ንፋስ የቀሰቀሰው አዋራ መሰል አድርገ እንጂ ከዛ ባለፈ ግምት አንሰጠውም።



ሸይኽ ዑሰይሚን (ረሒመሁላህ) እንዲህ ብለዋል፦

“ዲን ያሳትን ሴት ስግባ!
ምክንያቱም መቸም ቢሆን መብትህን ስትነፍገህም፣ ሚስጥርህን ስታወጣም፣ ንብረትህንም ሆነ ልጆችህን በምርጥ ሁኔታ ትንከባከብልሃለች።”

[ሸርሑ ሰልዱ ኻይ ኒካሕ :2]

ማጠቃለያ

1 እንደ ኢስላም የሴትን የውርስ መብት በመጠን፣ በዝርዝር፣ በፍትሃዊነት እንዲሰጣት ያበረታታና ያነሳሳ ህግ ወይም መርህ የለም። ይህንን ማበረታታት ከሚገልፁ ማስረጃዎች ውስጥ አንደኛ በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ የሚደርሳት የውርስ መጠን በተከበረው ቁርአን መጠቀሱና እንደዚሁም ለሰው ልጆች ሳይተውላቸው በዝርዝር በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰ ብቸኛ እውቀት መሆኑ ነው።

ይህም የሆነበት ምክንያት አደገኛ ከሆኑ ርዕስ ጋር ከመያያዙም ባሻገር የሰውን ልጅ ሊያሳስትና በስሜቱ መረብ ውስጥ እንዲወድቅ ሊያደርግ ስለሚችል ነው። ነፍስ ደግሞ በመጥፎ አዛዥ ናትና በተለይ በገንዘብ ጉዳይ የሰው ልጅ ለገንዘብ ፍቅር አለው ልጆች ሲጨመሩበት ደገሞ የቅርቢቱ አለምም ጌጥ ይሆናሉ። ይህም በመሆኑ ላቅ ያለው ጉብያዊ ፈለግ በጣም ጥቂት የሆነን በቁርአን ያልተብራራን ነገሮች አብራርቷል።

2 በአጠቃላይ የሴትን አወራረስ ስንመለከት ግልፅ የሚሆንልን የዚችን ወይም የዛችን ሴት ድርሻ መወሰን በህብረተሰቡ ውስጥ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ መሰረት መሆኑን ነው። የውርስ ጉዳይ “ለወንድ የሁለት ሴቶችን ድርሻ” በሚል ደንብ ብቻ የተመሰረተ አይደለም። ጉዳዩ የስሌት ጉዳይ እንጂ የእዝነት ቦታ አይደለም። ፍትሃዊነት የሚባለው ለሁሉም እንደአስፈላጊነቱ ሲሰጥ ነው። ይህንን እውነታ የሚያጠናክሩ ብዙ ምሳሌዎችን ጠቅሰናል ። እናም ያለ ምንም ምክንያት ሴት በመሆኗ ብቻ ተበድላለች በማለት ኢስላምን በዚህ መልኩ ለመቅረፅ ለሞከሩ ሁሉ ቁርጥ የሚያደርግ ምላሽ ሰጥቷል።

ኢስላም ሴት በመሆኗ የተነሳ ወይም ከዚህ በፊት የሴቶች ውርስ የአላህ መልዕክተኛ ከመላካቸው በፊት በምዕራባዊያንና በሌሎች ዘንድ በሚል በጠቀስነው ምክንያቶች የተነሳ ሴትን ከውርስ መከልከል የሚለውን መርህ ተፋልሟል። እንዲያውም በሁሉ ሁኔታ ድርሻዋን ወስኖላታል። ከኢስላም በመውጣት ወይምም ተወራሽን በመግደል ወይም ከዚህ በፊት በዝርዝር በጠቀስናቸው ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ድርሻዋን መነፈጓን ከልክሏል። እነዚህ ምክንያቶች ደገሞ ወንድንም ከውርስ የሚያግዱ ሲሆኑ ከዚህ ውጭ በሆነ ሰበብ እሷን የሚከለክል ግን በመጪው አለም ጠንካራ ቅጣት እንደሚጠብቀው አላህ ቃል ገብቷል።

የሮማኒያዊያን ህግና የነሱን ፈለግ የተከተሉት እንዳደረጉት ሴትን በውርስ ድርሻ ልቅ በሆኑ መልኩ ከወንድ እኩል ማድረግን ኢስላም ተቋውማል። ምክንያቱም ይህ ከዚህ በፊት እንዳመላከትነው ፍትሃዊነትን ይቃረናል። እንደ አይሁዳዊያን ወንድና ሴት ወራሾች በተገኙ ጊዜ ወንድን ብቻ በውርስ መለየትንም ይቃወማል እንደዚሁም ታላቅ ነው በማለት ወንድን ብቻ ከሴት ሁሌም መነጠልን ተቋውሟል።

ኢስላም ለውርስ ከሱ መውጣት የማይቻል የሆነን ህግጋት፣ መሰረታዊ ደንቦችንና ሚዛንን አስቀምጧል።

✍በመቱላህ



በማህበራዊ ገፃች ትምህርቶችን ይከታተሉ

www.fb.com/nesiha.org

ኢብኑ መስዑድ ኢስላሚክ ሴንተር

www.nesiha.com

ዌብ ሳይታችንን ይጎብኙ



www.fb.com/emnetihintebiq

www.emnetihintebiq.blogspot.com

☞እምነት ነክ ጉዳዮችን ሁሉ በመረጃ ማብራራት

☞ተዉሂድ እና ሸርክን በማብራራት የነብያትን ተልዕኮ ማስገንዘብ ለብዥታዎች በቂ ምላሽ መስጠት



www.fb.com/asmaewesifat

www.asmaewesifat.blogspot.com

☞በሰላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ የሰህሱናን አቋም መግለጽ

☞በተለያዩ የቢድዓ አራማጆች ስሚነሱ ጭዝንብሮች በቂ ምላሽ ማቅረብ



www.fb.com/nosihr

www.nosihr.blogspot.com

☞ስለ ሲህር እና መሰል ነገሮች ግንዛቤን ማስጨበጥ

☞ምልክቶች፣ መከላከያዎች እና መፍትሄዎችን መጠቆም



www.fb.com/easyfiqh

www.easyfiqh.blogspot.com

☞ፊቅህን በቀላል አቀራረብ ማቅረብ

☞ቁርዓን እና ሱንን መሰረት ባደረገ መልኩ ከሰለማዎች አቋሞች ለመረጃ የቀረበዉን መለየት

www.nesiha.com

تنبيهات

ዳዒል ሀዲስ የዓረብኛ ቋንቋ እና የሸሪዓ ትምህርቶች ኢንስቲትዩት

- የቁርኣን ሂፍዝ ትምህርት
- የዓረብኛና የሸሪዓ የሰርተፍኬትና የዲፕሎም ፕሮግራም
- የቤተ-መጻህፍት አገልግሎት
- የሴቶች በሴቶች ዳዕዋ
- ቤተሰባዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አገልግሎት
- ሺፋዕ ቤተሰባዊ የምክር አገልግሎት

ስልክ፡- 011 2 73 89 59/13

ኢ-ሜል፡- nesiha.org@gmail.com

ለሴቶች ልዩ ትኩረት የሰጠ
የት/ት ተቋም!

አድራሻ፡- ከጦር ሀይሎች ወደ 18 ማዞሪያ አደባባይ ሲመጡ ከ100 ሜትር በፊት በቀኝ በኩል



